# እግዚአብሔር ምን ይሻል?

ማይክል ኤስ. ሐይዘር

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት፣ የኢትዮጵያ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር 1954 ዓ.ም ካሳተመው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትርጉም እንዲሁም የዓለም አቀፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በ1993 ዓ.ም. ካሳተመው የአዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው።

ISBN-13: 978-0692199046 (Blind Spot Press)
ISBN-10: 0692199047
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

ሽፋን ሥዕል፡ ሞሊ ጆይ ሐይዘር

ትርጉምና አርታኢ፡- ዮሐንስ መሐመድ ሰኢድ
አለሙ ሺማሎ ሱላሞ

## በደራሲው የተጻፉ ሌሎች መጻሕፍት

*Supernatural: What the Bible Teaches about the Unseen World and Why it Matters*

*The Unseen Realm: Recovering the Supernatural Worldview of the Bible*

*Angels: What the Bible Really Teaches About God's Heavenly Host*

*Demons: What the Bible Really Teaches About the Powers of Darkness*

*I Dare You Not to Bore Me with the Bible*

*The Bible Unfiltered: Approaching Scripture On Its Own Terms*

*Reversing Hermon: Enoch, the Watchers, and the Forgotten Mission of Jesus Christ*

*Brief Insights on Mastering Bible Study (The 60-Second Scholar series)*

*Brief Insights on Mastering the Bible (The 60-Second Scholar series)*

*Brief Insights on Mastering Bible Doctrine (The 60-Second Scholar series)*

*The Façade* (fiction)

*The Portent* (fiction)

## የብሉይና የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ምኅጻረ ቃላት

ብሉይ ኪዳን

ኦሪት ዘፍጥረት (ዘፍ)
ኦሪት ዘፀአት (ዘፀ)
ኦሪት ዘሌዋውያን (ዘሌ)
ኦሪት ዘኁልቊ (ዘኁ)
ኦሪት ዘዳግም (ዘዳ)
መጽሐፈ ኢያሱ (ኢያ)
መጽሐፈ መሳፍንት (መሳ)
መጽሐፈ ሩት (ሩት)
1-2 ሳሙኤል (1-2 ሳሙ)
1-2 ነገሥት (1-2 ነገ)
1-2 ዜና መዋዕል (1-2 ዜና)
መጽሐፈ ዕዝራ (ዕዝ)
መጽሐፈ ነህምያ (ነህ)
መጽሐፈ አስቴር (አስ)
መጽሐፈ ኢዮብ (ኢዮ)
መጽሐፈ ምዝሙር (መዝ)
መጽሐፈ ምሳሌ (ምሳ)
መጽሐፈ መክብብ (ምክ)
ማሕልየ መሓልይ (ማሕ)
ትንቢተ ኢሳይያስ (ኢሳ)
ትንቢተ ኤርምያስ (ኤር)
ሰቆቃወ ኤርምያስ (ሰቆ)
ትንቢተ ሕዝቅኤል (ሕዝ)
ትንቢተ ዳንኤል (ዳን)
ትንቢተ ሆሴዕ (ሆሴ)
ትንቢተ ኢዩኤል (ኢዩ)
ትንቢተ አሞጽ (አሞ)
ትንቢተ አብድዩ (አብ)
ትንቢተ ዮናስ (ዮና)
ትንቢተ ሚክያስ (ሚክ)
ትንቢተ ናሆም (ናሆ)
ትንቢተ ዕንባቆም (ዕን)
ትንቢተ ሶፎንያስ (ሶፎ)
ትንቢተ ሐጌ (ሐጌ)
ትንቢተ ዘካርያስ (ዘካ)
ትንቢተ ሚልክያስ (ሚል)

አዲስ ኪዳን

የማቴዎስ ወንጌል (ማቴ)
የማርቆስ ወንጌል (ማር)
የሉቃስ ወንጌል (ሉቃ)
የዮሐንስ ወንጌል (ዮሐ)
የሐዋርያት ሥራ (ሐሥ)
ሮሜ (ሮሜ)
1-2 ቆሮንቶስ (1-2 ቆሮ)
ገላትያ (ገላ)
ኤፌሶን (ኤፌ)
ፊልጵስዩስ (ፊል)
ቆላስይስ (ቆላ)
1-2 ተሰሎንቄ (1-2 ተሰ)
1-2 ጢሞቴዎስ (1-2 ጢሞ)
ቲቶ (ቲቶ)
ፊልሞና (ፊሞ)
ዕብራውያን (ዕብ)
ያዕቆብ (ያዕ)
1-2 ጴጥሮስ (1-2 ጴጥ)
1-2-3 ዮሐንስ (1-2-3 ዮሐ)
ይሁዳ (ይሁ)
የዮሐንስ ራእይ (ራእ)

## አበርክቶት

በኢየሱስ ያለውን የእምነት ጉዞ ለጀመሩ፣ እንዲሁም ቀደም ብለው ጀምረው፥ መንገዱ ላይ ቈመው እንደቀሩ ለሚሰማቸው ሁሉ።

*ማውጫ*

*መቅድም*

*መግቢያ*

ክፍል አንድ፤ ታላቁ ታሪክ

ምዕራፍ አንድ፤ እግዚአብሔር ቤተ ሰብን ፈለገ

ምዕራፍ ሁለት፤ እግዚአብሔር አሁንም ቤተ ሰብን ይፈልጋል

ምዕራፍ ሦስት፤ እግዚአብሔር በቤተ ሰቡ ተከዳ

ምዕራፍ አራት፤ እግዚአብሔር ሰብአዊ ቤተ ሰቡን ተቀላቀለ

ምዕራፍ አምስት፤ እግዚአብሔር ቤተ ሰቡን ተከታተለ

ምዕራፍ ስድስት፤ እግዚአብሔር ለዘላለም ከቤተ ሰቡ ጋር ሆነ

*ማጠቃለያና ቅድመ እይታ*

ክፍል ሁለት፤ ወንጌሉ

ምዕራፍ ሰባት፤ ወንጌል ምንድን ነው?

ክፍል ሦስት፤ ኢየሱስን መከተል

ምዕራፍ ስምንት፤ ደቀ መዝሙርነት ምንድን ነው?

ምዕራፍ ዘጠኝ፤ ደቀ መዝሙር ምን ያከናውናል?

*አስፈላጊ ስሞችና ቃላት (የቃላት መፍቻ)*

*የልዕለ ተፈጥሮአዊ ቃላት ማጠቃለያ*

## መቅድም—አትለፉኝ

መቅድሙ አትኩሮታችሁን እንደሳበው ተስፋ አደርጋለሁ። መቅድሞችን ማንበብ ወረፋ የመጠበቅን ያህል፥ ወይም አሰልቺ የፓርላማ ንግግርን የመስማት ያህል፥ እንዲሁም መኪና እየነዳን ሳለ መንገድ ተዘግቶ የመቆምን ያህል አሰልቺ ነው። ይህ መቅድምም አስደናቂ ነው ብዬ ቃል አልገባም፤ ግን አስፈላጊ ነው።

ይህ መጽሐፍ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ስለተጻፈበት እውነተኛ ዓላማ የሚናገር መንደርደሪያ መጽሐፍ ነው፤ ይህም ስለ እግዚአብሔር ፍቅር፣ ከእግዚአብሔር ጋር የዘላለም ሕይወት እንዴት እንደሚኖረን፣እግዚአብሔር እነዚህን ሁለት ነገሮችንም ሌሎች እንዲማሩ እንድንረዳ መፈለጉን የሚናገር ነው። በጣም ቀላል... ምናልባትም በዚህ ዓይነት መልኩ ያልተለመደ መረዳት ነው። ይህ “የክርስትና ሀ ሁ” ወይም የተለመደው የክትትል ትምህርት አይደለም። ከዚህ በፊት ያልሰማችሁትን ነገሮች ይዳስሳል፣በጣም ለተለመዱት ነገሮችም የተለየ አተያይ ይኖረኛል።

ሁለት ዐይነት አንባቢዎችን ታሳቢ አድርጌያለሁ። የመጀመሪያው፥ በቅርብ ጊዜ ኢየሱስን ወደማመን የመጡትን ነው። ያ ሰው ከሆናችሁ፣ ምናልባትም መጽሐፍ ቅዱስ ያስፈራችሁ ይሆናል። በውስጡም እንግዳ የሚመስሉና ለመረዳትም አስቸጋሪ የሆኑ ጉዳዮችን የያዘ ነው። እምኑኝ፣ ስሜታችሁ ይገባኛል። ኢየሱስን ያመንኩት በአሥራዎቹ ዕድሜዬ ነበር፤ ስለ መጽሐፍ ቅዱስም የማውቀው ምንም ነገር አልነበረም። ስለ ኢየሱስ፥ ስለ ኖህ፥ ስለ አዳምና ሔዋን ሰምቻለሁ። ዕወቀቴ ያ ብቻ ነበር። ወንጌልን ከተቀበልኩ በኋላ ይህን መጽሐፍ የሚሰጠኝ ሰው ምነው በኖረ ብዬ ተመኝቻለሁ፤ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክና በጣም አስፈላጊ የሆኑ ጽንሰ ሐሳቦችን እንድረዳ ይረዳኝ ነበርና። ለእናንተም ይህንን ያደርጋል ብዬ አምናለሁ።

የማስባቸው ሁለተኛ ተደራሲያን ኢየሱስን ላወቁ ነገር ግን “ወደፊት መራመድ እንዳቃታቸው” ለሚሰማቸው ነው። በኢየሱስ አምናችኋል፥ ለጥቂትም ሆነ ለብዙ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተሳትፋችኋል። ነገር ግን፥ ከዚህ የሚበልጥ ነገር መኖር አለበት የሚል ጎትጓች ሥሜት በውስጣችሁ አለ–እስካሁን ካወቃችሁት የላቀ ነገር መጽሐፍ ቅዱስ ሊኖረው ይገባል የሚል። አንዳንድ ጊዜ ኢየሱስን የመከተል እውነተኛ ትርጉም ምንነት ግራ ይገባችኋል። መቼም፥እሁድ ከማምለክ፥ ከክርስቲያን ጓደኞች ጋር ህብረት ከማድረግ፥ ወይም በቤተ ክርስቲያን ባሉት ትናንሽ ቡድኖች ከመሳተፍ ያለፈ መሆን አለበት። ይህን እንድታውቁ እፈልጋለሁ፥ እነዚህ ውስጣዊ ስሜቶቻችሁ ትክክል ናቸው። ይህ መጽሐፍም ወደ ፊት እንድትራመዱ ይረዳችኋል።

ተቃርኖ ቢመስልም፥ ይህ መጽሐፍ፥ የተወሰኑ መሠረታዊ ወይም አስፈላጊ የሆኑ ሐሳቦችን፥ ለአስተዋይ ሰዎች ለማስተዋወቅ ( ምናልባትም በድጋሚ ለማስተዋወቅ) የታለመ ነው። አንባቢዎቼ አስተዋዮች እንደሆኑ ሁልጊዜ አስባለሁ። ለአንዳንዶቻችሁ፥ ይህ መጽሐፍ አንዳንድ ጉዳዮችን በአዲስ መልኩ እንደገና እንድትማሩ ይረዳችኋል። ለሌሎች ደግሞ፥ ይህ የመጀመሪያችሁ ይሆናል፤ ሁላችንም የሆነ ቦታ መጀመር ይኖርብናል። እነሆ ከዚህ እንጀምራለን።

ይህ መጽሐፍ፥ የጻፍኳቸውን ሌሎች መጻሕፍት እንዲያነቡ አንባቢዎችን ያዘጋጃል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ይህን መጽሐፍ ከጨረሳችሁ በኋላ፣ *"ልዕለ ተፈጥሮአዊው፡- መጽሐፍ ቅዱስ ስለማይታየው ዓለም የሚያስተመረው አስተምህሮና ፋይዳው"* የሚለውን መጽሐፍ እንድታነቡ አበረታታለሁ። ለእንግሊዘኛ አንባቢዎች፥ ይህን መጽሐፍ ከ Amazon.com ወይም ከአሳታሚው ከሌክሳም ልታገኙ ትችላላችሁ። በዚህ መጽሐፍ ያሉትን ጽንሰ ሐሳቦች የማስረዳበትን የተለያዩ ቪድዮዎች በድረ ገጾች ላይ በነጻ ይገኛሉ። ሌሎች ቋንቋዎችን ለምታነቡ፥ ይህን መጽሐፍ በነጻ ከhttps://www.miqlat.org/translations-of-supernatural.htm ማግኘት ትችላላችሁ።

*ልዕለ ተፈጥሮአዊውን* ካነበባችሁ በኃላ፣ አንባቢዎች፣ ስለ መጽሐፍ ቅዱስና ስለ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ከሰማናቸው በላይ ልንማር እንደምንችል ለማሳየት የጻፍኩዋቸውን ሌሎች መጽሐፍት እንደምታነቡ ተስፋ አደርጋለሁ ለምሳሌ፡ *I dare You Not to Bore Me with the Bible; The Bible Unfiltered: Approaching Scripture on Its own Terms;* and *The Unseen Realm: Recovering the Supernatural Worldview of the Bible.*

ሁላችሁም ደግሞ የ *Naked Bible Podcast* ሰሚዎቼ እንደምትሆኑ ተስፋ አደርጋለሁ። ስሙ እንደሚያሳየው፥ ዓላማዬ መጽሐፍ ቅዱስን ከሐይማኖታዊ ድርጅቶች ማጥለያና በምእራባዊ አሳቤ ከተቃኘው ዘመናዊ አስተሳሰብ ነጻ በሆነ መልኩ በተጻፈበት በራሱ ጥንታዊ ዐውድ ለአድማጮቼ ማቅረብ ነው። ግድ የሚለኝ ብቸኛ ነገር፥ መጽሐፍ ቅዱስ በራሱ ዐውድ ስለሚለው ነገር እንጂ ትውፊት ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው አይደለም። በየወሩ፥ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ አድማጮች መጽሐፍ ቅዱስን ለመጀመሪያ ጊዜ በድጋሚ ማንበብን ተምረዋል። አዲስ ነገርን በማወቅ ውስጥ ያለውን ደስታ፥ እያንዳንዱ አማኝ ቋሚ በሆነ መልኩ ሊለማመደው ይገባል። እኔም የማደርገውን የማደርግበት ምክንያት ይህ ነው።

ይህን ስላነበባችሁ አመሰግናለሁ!

# መግቢያ

እግዚአብሔር ምን ይሻል?

ቀላል ጥያቄ ይመስላል ነገር ግን ይበልጥ ካሰባችሁበት በእርግጥ ቀላል አይደለም።

ለምን? ለመጀመር ያህል፥ ጠያቂው ማን እንደሆነ ልታውቁ ይገባል። ሰዎች ይህን ጥያቄ በተለያየ ምክንያት ይጠይቃሉ። በሥቃይ ካለ ሰው የሚመነጭ የቁጣ ጩኸት ነውን? ምናልባት ከጥልቅ ሐዘን የሚወጣ ለሆሳስ ድምጽ ቢሆንስ? ለማውቅ ካለ ፍላጎት የተነሣ የተጠየቀ ይሆን? ወይስ ጥልቅ ሐሳቦችን ለማብሰልሰል ባለ ፍላጎት ግፊ የተጠየቀ ይሆን? ትክክለኛው መልስ፥ ጥያቄው ለምን ተጠየቀ በሚለው ላይ የተመሰረተ መሆኑን መመልከት አስቸጋሪ አይደለም።

ጥያቄውን ያነሳሁት እኔ ስለሆንኩ፥ ይህን መመለስ ቀላል ነው። ነገር አስቀድሜ ያላነሳሳኝን ነገር ልንገራችሁ። ጥያቄውን የምጠይቀው መልሱን ስለማላውቅ አይደለም። በእርግጥ አውቀዋለሁ። እንዲያውም፥ እግዚአብሔር ራሱ ለሁላችንም የሚመልስልን መልስ ስለሆነ እኔም በእርግጠኝነት ለእያንዳንዳችሁ ያለውን መልስ አውቃለሁ። የምጠይቀበትም ምክንያት ይህ ነው። አንኳር የሆኑ ጉዳዮችን ታስቡ ትችሉ ዘንድ ለመርዳት እጠይቃችኋለሁ። "እግዚአብሔር ምን ይሻል?" ብዬ ስጠይቅ፥ *የሰው ዘር ለሆነ ለእያንዳንዱ ሁሉ እግዚአብሔር ምን ይፈልጋል*? እያልኩ ነው። እኔና ሕይወቴን በተመለከተ፣እናንተንና ሕይወታችሁን በተመለከተ ምን ይፈልጋል?

ወደ መመለስ ከመሄዴ በፊት፥ ጥያቄው ሐይማኖታዊ መሆኑ ግልፅ ነው። እግዚአብሔርን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ብዙውን ጊዜ የሚመደቡበት ክፍል ሐይማኖት ነው። ጥያቄውን ያነሳሁበትም የምመልስበትም ምክንያት የእግዚአብሔር ነገር ግድ ስለሚለኝ ነው። ለቤተ ክርስቲያን ግድ የማይላቸው፥ እግዚአብሔርን የሚፈልጉ ብዙዎች አሉ። ይህ ችግር አይፈጥርም ምክንያቱም ስለ እግዚአብሔር ለማውራት የግድ ስለ ቤተ ክርስቲያንን ማንሳት አይኖርብንም። እኔ መጋቢም ሆነ ካህን አይደለሁም፣ ነገር ግን ሥራዬ መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት ላይ የተመሰረተ ነው (አዎን፥ ሥራዬ ነው)። ጠያቂው እኔ ስለሆንኩ መልሴም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ ነው። ያም ትኩረታችንን በተወሰነ መልኩ ይገድበዋል። ግቤ መጽሐፍ ቅዱስ "እግዚአብሔር ምን ይፈልጋል?" የሚለውን ጥያቄ እንዴት እንደሚመልሰው ማብራራት ነው።

አሁን ወደ መልሱ እንሂድ። መልሱ ቀላል ነው። እግዚአብሔር *እናንተን* ይፈልጋል።

ያ ሊያስደንቃችሁ ይችላል። ልትጠራጠሩትም ትችላላችሁ። ችግር የለውም። ነገር ግን ትክክለኛው መልስ እርሱ ነው። እውነት ለመናገርም ያህል፣ መልሱ ብቻውን *በቂ* አይደለም። የመልሱንም አስደናቂነትና ጥልቀት ከተጻፈው አንድ ዓርፍተ ነገር ላታገኙት ትችላላችሁ። ከመልሱ በስተጀርባ ያለውን ፍቅር ለማድነቅ የተወሰነ ዐውድ ማወቅ ግድ ያላል።ከመልሱ በስተጀርባ ትልቅና አስደናቂ *ታሪክ* አለ።

ጉዳዩ ያ ስለሆነ፣ ይህ መጽሐፍ እግዚአብሔር ስለሚፈልገው ብቻ ሳይሆን *እግዚአብሔር እንድናውቃቸው ስለሚፈልጋቸውም ነገሮች* ጭምር ነው። *አዎን፣ እናንተን ይፈልጋል*፣ ይህ እንዲያስደቃችሁ፣ ስለ እግዚአብሔርም ተመሳሳይ ስሜት እንዲሰማችሁ፥ ጥቂት ዐውድ ማወቅ ያስፈልጋችኋል።

ያን ማስረዳት በእርግጥ *ሥራዬ* ነው። ከእግዚአብሔር ታሪክ እንጀምራለን። ታሪኩ ብዙ አሳዛኝ ነገሮችን የያዘ ቢሆንም የቱም ጉዳይ እግዚአብሔር ስለ እናንተ (እፎይ ስለ እኔም) ያለውን ሐሳብ እንዲለውጥ አላደረገውም። ታሪኩን ነገሬ ከጨረስኩ በኋላ (ጉጉ አንባቢ ላልሆናችሁት ይህ ዕድል ነው፣ ምክንያቱም መላው መጽሐፉ ስለ ታሪኩ አያወራም)፣ በታሪኩ ውስጥ በሚገኙት በጣም አስፈላጊ በሆኑት ጉዳዮች ላይ ብቻ ትኩረት አደርጋለሁ። ታሪኩን የሚናገረውን ክፍል ብቻ ካነበባችሁ፥ የተነሣንበትን ጥያቄ መልስ ታገኛላችሁ። ነገር ግን፥ ከዛ አልፋችሁ ለማንበብ እንደምትሹ እገመታለሁ፥ ተስፋም አደርጋለሁ፤ መልካም ነገርም ታገኙበታላችሁ።

ከመጀመራችን በፊት አንድ ነገር አስቀድሜ ላርዳችሁ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ከኖራችሁ፥ ታሪኩን ዐውቃለሁ ብላችሁ ታስቡ ይሆናል። በእርግጥ የተወሰነውን ክፍል ታውቃላችሁ፥ ነገር ግን እመኑኝ፥ የምትደነቁበት ብዙ ነገር ታገኛላችሁ። በሚያሳዝን ሁኔታ፣ የታሪኩን አስደናቂነት እንዳናይ በመንገድ ደንቃራ ሆኖ የሚቆመው ሐይማኖት ነው። አንዳንዴ ቤተ ክርስቲያንና የሐይማኖት ቡድን ምርጫዎቻችን ከታሪኩ ይበልጥ ገዝፈው ይታዩናል። በዚህ መጽሐፍ ግን ያ አይሰራም።

የተወሰኑ አንባቢዎቼ መጽሐፍ ቅዱስን እንደሚያውቁ ብገምትም፣ አዳዲስ እውነቶችና ጥንታዊ እውነቶችን በአዲስ መልኩ ማስብ የሚያስችላቸውን ነገር እንደሚያገኙበት እርግጠኛ ነኝ። ቤተ ክርስቲያን ለማታዘወትሩና ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያልሰማችሁ አንባቢዎች ግን እጅግ ተፈላጊዎች ናችሁ። ለእናንተ በድጋሚ የምትማሩት ወይም የተማራችሁትን ለማስጣል የሚደርግ ጥረት አይኖርም። ሁሉ ነገር ትኩስ ነው። በየትኛውም መንገድ ይሁን፣ እግዚአብሔር ምን (እና ለምን) እንደሚፈልግ በማወቅ ውስጥ ያለውን ጥልቅ ስሜት ትለማመዳላችሁ ብዬ አስባለሁ።

# ክፍል አንድ፡- ታላቁ ታሪክ

## ምዕራፍ አንድ

## እግዚአብሔር ቤተ ሰብን ፈለገ

አስቀድሞ ስለ እግዚአብሔር የነበረኝ እሳቤ በሰማይ ያለ የማይታይ አባት አልነበረም። እግዚአብሔር ፈጣሪና ሩቅ ኀይል ነበር። ስለ እኔና ስለ እያንዳንዱ ሰው እንደሚያውቅ እገምት ነበር፤ ነገር ግን ስለ እኔ እና በዓለም ላይ ስላለው ሕዝብ ምን እንደሚያስብ (ያስብ ከሆነ) ወደ አእምሮዬ መጥቶ አያውቅም። ልክ በጣራዬ በታች እንዳለ ዓይነት ህለዎት ባይሆንም፥ እንዳለ አልጠራጠርም ነበር ። በዚህ ፈንታ፣ እግዚአብሔር፥ የሩቅ ተመልካች፥ ከጊዜ ወደ ጊዜ ምናልባትም በችግር ውስጥ ስሆን የሚያየኝ ይመስለኝ ነበር። አስቡት፥ እግዚአብሔር ሊቀጣኝ የሚፈልግ ወይም የሚጠላኝ እንደሆነ አላስብም። እኔን በተመለከተ፥ እግዚአብሔር እውን እንደሆነ አምን ነበር፤ እንደ ጠላት አስበው ዘንድ ምክንያት አልነበረኝም። “ከዐይን የራቀ ከልብ የራቀ” እንዲሉ፣ዐውቅ የነበረው ያን ብቻ ነው።

ስለ እግዚአብሔር መማር ነበረብኝ። እፈልገው ስላልነበር፥ የሚፈልገኝ አይመስለኝም ነበር። ሰው ጠይቆኝ ቢሆን ኖሮ፥ እግዚአብሔር ከዚህ የተሻለ ሌላ ሥራ አለው ብዬ የምመልስ ይመስለኛል። ግምቴ፥ የማደርገው በጎም ሆነ ክፉ ምግባር ያን ያህል ትኩረት የሚገባው እንዳልነበረ ነው።

ተሳስቼአለሁ። እኔ አላውቅም እንጂ እግዚአብሔር አየፈለገኝ *ነበር*። እኛን መፈለግ ባሕሪው በመሆኑ፥ እኔን ይፈልግ እንደነበር አሁን አውቄያለሁ። እርሱ፥ ለእኛ *ታማኝ* ነው።

ስለእግዚአብሔር የምንላቸውን እነዚህን ነገሮች እንዴት እናውቃለን?(ይህን ጥያቄ ከአንድ ጊዜ በላይ የምጠይቀው ነውና አስተውሉት)። ራሳችንን እንደ ምሳሌ ወስደን እንጀምር። በጥልቀት አስበን ስለ ሠራናቸው ወይም የተለየ ትጋትን ለጠይቁን ሥራዎቻችን ግድ ይለናል፤ ይህ የተለመደና የተፈጥሮአችን አንዱ ክፍል ነው። አንድ ግለሰብ ደረስንበት ያልነውን ወይም አስቀድመን ያሰብናቸውን ነገሮች የኔ ናቸው ቢል፥ የሠራናቸውን ነገሮች ቢያቃልል፥ቢያጠፋና ቢያፌዝባቸው፥ መቆጣታችንና መበሳጨታችን አይቀሬ ነው። ይህ ስሜት ከሌለን፥ ደህንነታችን ጥያቄ ውስጥ ይገባል።

ለተሰማን ስሜት መነሻ ተፈጥሮአዊ ማንነታችን ነው። እኛ ራስ-ዐወቅ ፍጥረቶች ነን። ሁላችን ወስጠታዊ ሕይወት ማለትም አመክኖአዊ ሕይወት አለን። አእምሮአችንን የምንጠቀመው ለምንፈልገውና ደስታን ለሚያመጣልን ነገር እንጂ ለሚያሳምመንና ኪሣራ ለሚያደርስብን አይደለም። በዓላማ ቢስነት ወይም በአጋጣሚ ሳይሆን፣ አስበን እናደርጋለን። በምክንያትና በህሊና እንመራለን።

ይህ እውነት እንደሆኑ የሚያሳዩ ምሳሌዎች ብዙ ናቸው። ብዙ ጥቅም የላቸውም ብለን የምናስባቸው ነገሮች እንኳ፥ በምክንያት፥ ሆን ተብለው የሚደረጉ ናቸው። ጥርሳችን እንዳይበላሽና አፋችን እንዳይሸት፥ ጥርሳችንን እንፍቃለን። ሥራችንን ላለማጣት ስንል፥ ጠዋት እንነቃለን (ሥራችንንም የምንወድ ከሆነ እሰየው)። የምንሄድበት ቦታ ስላለ፥ ግራውን ትተን ወደ ቀኝ እንታጠፋለን። ግብታዊ ሊባሉ የሚችሉ ነገሮችን እንኳን ስናደርግ (ለምሳሌ፥ በማህበራዊ ድረ ገጽ ላይ የሆነን ግለሰብ፥አየውም አላየውም፥ ስናበሳጭ) ምክንያታችን የምንፈልገውን ውጤት ለማየት ነው ( የተሻልን ሆነን ለመታየት ወይም "ልናስተምራቸው")። ደስ የማይል ነገር እንኳ ስናደርግ፥ ድርጊታችን በሆነ መንገድ ለኛ መልካም ነገር ያመጣልናል በሚል እሳቤ ነው። የምንበላውን ለምን እንቆጣጠራለን? በተፈጥሮ በዓላማ የምንቀሳቀስ፥ ዓላማ–የለሽ ፍጡሮች ስላልሆንን ነው።

እደግመዋለሁ፤ ከእነዚህ ነገሮች ውጭ መሆን የአእምሮ ወይም የስሜት መታወክ ምልክት ሊሆን ይችላል።

የመጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔርም ይህ ገጽታ አለው። እግዚአብሔር የሚያደርገውን የሚያደርገው በሥራው ለመደሰት ነው። እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው፥ እጦት ስለነበረበት አይደለም። ብቸኛም አልነበረም፤ጐዶሎም አልነበረም፤ጓደኛም አያስፈልገውም ነበር። እግዚአብሔር ምንም አይጐድለውም ...አዎን... እርሱ እግዚአብሔር ነው። ነገሮችን የፈጠረበት ምክንያት በእጆቹ ሥራ ለመደሰት ነው እያልን ነው። በጣም የሚጠነቀቅላቸውና ግድ የሚሉት ነገሮች ደግሞ፥ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው፥ እርሱን እንዲመስሉ፥ "በመልኩ" የፈጠራቸው ናቸው (ዘፍ 1፥26)። እነዚያም እናንተ እና እኔ ነን።

*የታሪካችን ጅማሮ*

ታሪካችን፥እግዚአብሔር ለምን እንደሚፈልገን የሚናገረው ታሪክ፥ የሚጀምረው እግዚአብሔር ሠሪያችን ነው ከሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐሳብ ነው። ይህንን ሐሳብ ሙሉ በሙሉ መረዳት ባንችልም፣ መሠረታዊው ነጥብ፥ እኛ እዚህ ያለነንበት ምክንያት እግዚአብሔር እዚህ እንድንሆን ስለፈለገ ነው የሚል ነው። እርሱ በዓላማ ይሠራል። እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር፣ ጐዶሎነቱን ለመሙላት እየሞከረም አይደለም፤ እርሱ የሚጎድለው የለምና ። ሳናስፈልገው እንደፈጠረን ካመንን፥ ለምን ፈጠረን ለሚለው ጥያቄ አንድ ብቸኛ ምክንያታዊ ማስረጃ አለ። እግዚአብሔር እንድንኖር የፈለገበት ምክንያት በእኛ ይደሰት ዘንድ ነው ( እኛም በምላሹ በእርሱ እንድንደሰት)።

እግዚአብሔር ስለፈጠረን፥ መጽሐፍ ቅዱስ እርሱን “አባታችን” ሲለው፥ ከአዳም ጀምሮ ያሉትን ሁሉ ደግሞ ልጆቹ ይላቸዋል።[1] መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ያለውን ግንኙነት ለመግለጽ ቤተሰባዊ ቋንቋንም የሚጠቀምበት ምክንያት ይህ ነው፤ በአጋጣሚም አይደለም።

ትንሽ ቀደም ያልኩ ይመስለኛል። የመጽሐፍ ቅዱስን የቤተ ሰብ-ተኮር ቋንቋ ዐውድ ለመረዳት፥ እግዚአብሔር ምድርንና የሰውን ዘር ከመፍጠሩ በፊት ወደነበረው ጊዜ መሄድ ይኖርብናል። ሊያስደንቃችሁ ይችል ይሆናል፥ ያኔ እግዚአብሔር ብቻውን አልነበረም። ያም እግዚአብሔር ከብቸኝነቱ ለመፈወስ እንዳልፈጠረን እርግጠኛ እንድንሆን የሚያሳይ ሌላ ምክንያት ነው።

እግዚአብሔር እኛን ከመፍጠሩ በፊት፣ ሌሎች ብልህ (አምክንዩአዊ) ፍጡሮችን እንደፈጠረ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን ፍጡሮች “የእግዚአብሔር ልጆች” ይላቸዋል። እኛ መላእክት እንላቸዋለን። በብሉይ ኪዳን የሚገኘው የኢዮብ መጽሐፍ፥ እግዚአብሔር የምድርን መሠረት በጣለ ጊዜ፥ የእግዚአብሔር ልጆች “እልል” እንዳሉ ይነግረናል (ኢዮ 38፥4-7)። ያኔ ነበሩ፥ ይመለከቱም ነበር።[2]

“የእግዚአብሔር ልጆች (sons of God)” የሚለውን ሐረግ አስቡ። “ልጆች (sons)” ተብሎ የተተረጐመው የእብራይስጥ ቃል፥ ሌሎችንም በሚያጠቃልል መልኩ “ልጆች (children)” ተብሎ መተርጐምም ይችላል።[3] ይህ ከሆነ፥ “የእግዚአብሔር ልጆች” የሚለው ሐረግ ምንን ያመለክታል? ቤተ ሰብን።

ስለቤተ ሰብ ሲወራ፥ “ልጆች” የሚለውን ቃል እንጠቀማለን። በኢዮብ 38፥4-7 ላይ ያለው ቤተ ሰብ ሰማያዊ ወይም ልዕለ ተፍጥሮአዊ ነው። እግዚአብሔር ለፈጠራቸው፥ በማይታየው ዓለም ለሚኖሩት ብልህ ፍጥረቶች፥ አባት ነው።

እግዚአብሔር ልዕለ ተፈጥሮአዊ ቤተ ሰብ እንደነበረው ማውቃችን፥ በዘፍጥረት ትረካ ውስጥ የምናገኛቸውን የመጀመሪያ ሰዎች፥ አዳምንና ሔዋንን፥ የፈጠረበትን

---

[1] ኢሳ 63፥16፤ 64፥8፤ ሉቃ 3፥38፤ ሐዋ 17፥28-29፤ ሮሜ 1፥7፤ 1ቆሮ 1፥3።
[2] አዲሱ መደበኛ ትርጉም “የእግዚአብሔር ልጆች” በሚለው ምትክ በዚህ ስፍራ “መላእክት” የሚለውን ይጠቀማል።
[3] ዘፍ 3፥16፤ 30፥26፤ 31፥43። የእንግሊዘኛው መጽሐፍ ቅዱስ ልጆች ለሚለው ቃል “sons” እና “children” የሚሉትን ቃላት ይጠቀማል። የመጀመሪያው የወንድ ጾታን ሲያመለክት፥ ሁለተኛው ደግሞ ለሁለቱንም ጾታዎች ይውላል። የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ግን በቋሚነት ልጆች “children” የሚለውን ይጠቀማል። ጾታን ለመግለጽ ሌሎች ቅጽሎችን፥ “ወንድ ወይም ሴት” የሚለውን ይጠቀማል።

ምክንያት እንድንረዳ ይረዳናል። እግዚአብሔር ከልዕለ ተፈጥሮአዊ ቤተሰቡ በተጨማሪ ሰብአዊ ቤተ ሰብን ፈለገ። በሚያስደንቅ ሁኔታ፣ የዔድን ታሪክ የሚያሳየው እግዚአብሔር እነዚህ ሁለቱ ቤተ ሰቦች በፊቱ አብረው እንዲኖሩ መፈለጉን ነው። ይህ ማለት፣ ልክ እንደ መላእክት፥ ሰዎች በመጀመሪያ የተፈጠሩት በእግዚአብሔር ህልውና ፊት መኖር እንዲችሉ ተደርገው እንደነበረ ነው።

ያን ሁሉ እንዴት እናውቃለን? (በድጋሚ ጠይቅኩ አይደል)። አብረን እንመልከት።

የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ፥ኦሪት ዘፍጥረት፥ ስለ ፍጥረት በመተረክ ይጀምራል። ትረካው አዳምና ሔዋን ጋር ከመድረሱ በፊት እግዚአብሔር ብዙ የመፍጠር ሥራን አከናውኗል። ታሪኩ እግዚአብሔር ዕፅዋትን፣ ነፍሳትን፣ በራሪ ፍጥረታትንና በምድር ላይ የሚርመሰመሱ እንስሳትን ሲፈጥር ይጀምራል። እነዚህ ፍጥረታት ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ማድረግ አይችሉም። ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር አይችሉም፤ ሐሳባቸውንም ሆነ ለእርሱ ያላቸውን አድናቆት ሊገልጹለት አይችሉም። የቤተ ሰብ አባላት እርስ በእርሳቸው ስሜታቸውንና ሐሳባቸውን ይገልጻሉ፤ በጓደኝነትም ይጣመራሉ። ምንም ያህል ውብ ቢሆኑም፥ ተክሎችና እንስሳት የልጆችን ሚና መጫወት አይችሉም። ቤተ ሰብም አይደሉም። እግዚአብሔር የፈለገው ደግሞ ቤተ ሰብ ነው። ስለዚህ እርሱን የሚመስል ነገር መፍጠር አስፈለገው።

## የእግዚአብሔር መልክ አንጸባራቂዎች (*Imagers of God*)

እግዚአብሔር ምድርን በዕፅዋትና በእንስሳት ከሞላ በኋላ የሚቀረው ሌላ ሥራ ነበረ። እግዚአብሔር አዲስ ፍጥረቶቹን "በመልኩ" እና "በአምሳሉ" ለመሥራት ወሰነ (ዘፍ 1፥27)፤ ምድራዊ ቤተሰቦቹም ይሆናሉ።

የ"እግዚአብሔር መልክ" በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አስፈላጊ ጽንሰ ሐሳብ ነው። ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲመስሉ ተድርገው ተፈጥረዋል። የእግዚአብሔር "መልክ" የሚለውን ቃል እንደ ግሥ ከወሰድን፥ ሐሳቡን ለመረዳት ትክክለኛው ጐዳና ላይ ነን። እግዚአብሔርን ልንመስለው ተፈጥረናል፣ እርሱን ለማንጸባረቅና ለመወከልም ተፈጥረናል።

የእግዚአብሔር መልክ መሆን ምን ማለት ነው? ዘፍጥረት 1፥27-28 መልሱን ይሰጠናል።

> እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው፡-ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ግዙአትም፥ የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው።

እግዚአብሔር የራሱን ምድር በሚገባ መንከባከብ ይችል ነበር። እርሱ እግዚአብሔር ነው። ከእርሱ አቅምም በላይ ምንም ነገር የለም። ግን በምትኩ ምድራዊ ቤተ ሰብን ፈጠረ። ፍጥረቱን የመንከባከብና የማስተዳደር ድርሻ ለልጆቹ ተሰጠ፤ ወኪሎቹና አብረውት የሚሠሩም ሆኑ። የእግዚአብሔር መልክ መሆን ማለት እግዚአብሔርን በምድር ላይ መወከል ማለት ነው። እግዚአብሔር እራሱ ሊሠራው የሚችለውን ሥራ ለሰዎች ሰጠ፤ ልጆቹ እንዲሳተፉ ፈለገ። የእግዚአብሔርም ሥራ የቤተ ሰብ ሥራ ሆነ። ዔድን የእግዚአብሔር መኖሪያ ብቻ ሳትሆን፥ የእግዚአብሔር የቤት ቢሮም ሆነች። ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ ለመሥራት ተፈጠርን።

እግዚአብሔር ሰዎችን ሲፈጥር፥ መልኩን የማሳየት ሥራን በምድር ላይ መፈጸም እንዲችሉ አድርጕ ነው። ባሕርያቱን ማለትም ጠባዩንና ችሎታውን ለሰዎች አካፈለ፡-ለምሳሌ ብልህነቱንና የፈጠራ ችሎታውን። መጽሐፍ ቅዱስ፥ ሰዎች ከእግዚአብሔር የሚያንሱ፥ ግን እርሱን የሚመስሉ ፍጡሮች እንደሆኑ ይነግረናል። የፈጠረውን አዲስ ዓለም፥ አብረነው እንድንገዛና እንድንከባከብ፥ ራሱን አስመስሎ ሠራን።

የእግዚአብሔርን መልክ ማንጸባረቅ ከብዙ ምክንያቶች የተነሣ አስፈላጊ ጽንሰ ሐሳብ ነው። ለእያንዳንዳችን ጥልቅና የተደላደለ ማንነትን ይሰጠናል። የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ዕቅዱ፥ እያንዳንዱ ሰው የእርሱ ልጅና ሽሪክ እንዲሆን ነበር። እግዚአብሔር ሰዎችን የሚመለከተው *እንደዚያ* ነው። እኛም ስለ ሰዎች ልናስብ የሚገባን እንዲሁ ነው። እግዚአብሔር፥ እያንዳንዳችን፥ ሰዎችን እንደ እህትና እንደ ወንድም እንድናስብ ይፈልጋል። ሁላችን እግዚአብሔር በቤተ ሰቡ የሚፈልገን፥ መልኩንም የማንጸባረቅ እኩል ሥፍራ ያለን ነን። ዘረኝነት፥ ዐመጽ፥ ሌሎችን መጠቀምና በኃይል ማስገደድ፥ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ባለው ዕቅድ ውስጥ ድርሻ የላቸውም። እነዚህ የዐመጽና የኀጢአት እኩይ ውጤቶች ናቸው። ኀጢአት *እግዚብሔር በሚወዳቸው* ሰዎች ላይ ያመጣውን ነገር፥ እግዚአብሔር ይጠላል። የራሳችንን የሞራል ውድቀትና የሌሎችንም ስናስብ ይህን አብረን ማሰብ ይኖርብናል።

መልኩን ማንጸባረቅ ዓላማን ይሰጠናል። ተልዕኮ አለን። ትንሽ፥ ደካማ፥ አጭር እድሜ ያለን ብንሆን እንኳ በሌላው ሰው ሕይወት የምንጫወተው ሚና አለ።

እግዚአብሔርንና መልኩን የሚያንጸባርቁትን የሚያከብር፥ ከልብ የምንሠራው ማንኛውም ሥራ መንፈሳዊ ጥሪያችን ነው። በእግዚአብሔር ሐሳብ፥ የመጋቢ፥ የአገልጋይ ወይም የካህን ሚና ከሌላው ጥሪ ብልጫ ያለው አይደለም። አኗኗራችን፥ አብረውን መልኩን የሚያንጸባርቁትን፥ ከእግዚአብሔር ጋር በሕብረት መኖር ምን እንደሚመስል በማስታወስ የሚባርክ አሊያም የሚረግም ነው። ድርጊታችን ወሳኝ ነው—ብዙውን ጊዜ ትንሽና ተራ ቢመስልም።

ይህ ሁሉ፥ ምዕራፉን የጀመርኩበትን ጥያቄ ለምን በመለስኩበት መንገድ እንደመለስኩት ያሳያል። እግዚአብሔር ምን ይሻል? እናንተን ይፈልጋል። ቤተ ሰብን ይፈልጋል። አብሮ ሰራተኛን (ሸሪክን) ይፈልጋል። ማን እንደሆናችሁና ህይወታችሁ ለእርሱ ዋጋ ያለው እንደሆነ እንድታውቁ ይፈልጋል።

ግን፥ ገና ጅማሮ ላይ ነን። ታሪኩን በተመለከተ የሚቀር ብዙ ጉዳይ አለ። በዓለማችን ያለው ሕይወት፥ ምናልባትም በቤታችን ያለውም ኑሮ፥ ከዚህ ከእግዚአብሔር ራእይ ጋር አብሮ አይገጥምም። ሁሉን ነገር ያበላሸ አንድ ነገር ተከሰቷል። ልብ ማቁሰሉ ከባድ ከመሆኑ የተነሣ፥ እግዚአብሔር በሰው ላይ ተስፋ እንዲቆርጥ ሊያስወስነው የነበረ ጉዳይ ነው።

## ምዕራፍ ሁለት

## እግዚአብሔር አሁንም ቤተ ሰብን ፈለገ

ባለፈው ምዕራፍ፣መልኩን በምድር ላይ እንዲያጸባርቁ ሰዎችን እንዳስታጠቀ ጠቅሻለሁ። ይህንንም ያደረገው ባሕርዩንና ችሎታውን ለሰዎች በማካፈል ነው። ያ ምንም ያህል አስደናቂ ቢሆንም፥ ነገሮች አሰገራሚም አስፈሪም የሚሆኑት እዚሁ ላይ ነው። አንዱ የእግዚብሔር ባሕርይ ነጻነት ነው—ብዙውን ጊዜ ነጻ ፍቃድ የምንለው። እኩይ በዓለም ላይ ለምን ተከሰተ ብለን ለምንጠይቅ ሁሉ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ መልስ ይኸው ነው።

*ዐመፅ#1*

እግዚአብሔር ባሕርያቱን ለልጆቹ ለማካፈል ሲወስን፥ ምን ማለት እንደሆነ ያውቃል። እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ያውቃል፤ ስለዚህም ምን እንደሚከሰት በግልጥ ተረድቷል። ሰማያዊ ቤተ ሰቡንም የፈጠረ ጊዜ፥ እግዚአብሔር ይህንኑ ውሳኔ አስቀድሞ ወስኗል። ሰማያዊ ቤተ ሰቡም፥ ጥበብና ነጻነት አላቸው። ከፈጣሪያቸው ያገኟቸው ስጦታዎችም ናቸው።

የኋላ ኋላ፥ ስጦታዎቹን ሰዎች ያለአግባብ ወይም መልካም ላልሆነ ነገር ሊጠቀሙባቸው እንደሚችሉ እግዚአብሔር ያውቃል። በሰማይም ሆነ በምድር ያሉት ልጆቹ፥ እርሱን ቢመስሉም፥ *እርሱን እንዳልሆኑ* እግዚአብሔር በሚገባ ያውቃል። ከእርሱ *ያንሳሉ።* እርሱ ፍጹም ሲሆን እነርሱ ግን ፍጹማን አይደሉም። የሆነ ጊዜ፣ ከልጆቹ ውስጥ አንዳቸው ወይም አብዛኛው፥ አሳፋሪ ስህተት እንደሚፈጽሙ ወይም ግብታዊ ከሆነ ራስ ወዳድነት ተነስተው፥ እግዚአብሔር እንዲሆን በሚፈልገው ወይም በማይፈልገው ነገር ላይ ማመጻቸው አይቀሬ ነው።

በዔድን የአትክልት ሥፍራ የሆነውም በዐጭሩ ይህ ነው። አዳምና ሔዋን ዐመፁ። እግዚአብሔር እንዳይበሉ ካዘዛቸው የገነት ዛፍ ፍሬ በመብላት ትእዛዙን ተላለፉ። ኀጢአትንም አደረጉ፤ በእግዚአብሔርም ህልውና ያለውን የዘላለም ሕይወት አጡ። ከዚያ በኋላ የተወለዱ ሰዎች ሁሉ ከዔድን ውጭ የተወለዱ፥ ከእግዚአብሔርም የተለዩ ናቸው። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን እንዲህ በማለት በሚገባ ይገልጸዋል፡ “የኀጢአት ደመወዝ ሞት ነውና” (ሮሜ6፥23)።

ይህ አሳዛኝ ክስተት የመጣው ከዚህ ቀደም ብሎ በተፈጸመ ዐመፅ ነው። ከእግዚአብሔር ልዕለ ተፈጥሮአዊ ልጆች አንዱ፥ የእግዚአብሔርን ምድራዊ ቤተ ሰብ ፍለጋ ውሳኔ በመናቅ፥ እግዚብሔርም አዳምንና ሔዋንን ያጠፉ ዘንድ በማሰብ

ሔዋንን ፈተናት። በእባብ ተመስሎም ወደ ሔዋን መጣ (ዘፍ 3፥1-7)። መጽሐፍ ቅዱስ፥ ይህንን እባብ ሰይጣንና ዲያቢሎስ ብሎ ይጠራዋል (ራእ 12፥9)። ሔዋን ኀጢአትን እንድትሠራ በማድረግ ተከናወነለት፣ ነገር ግን ሰውን በቋሚነት የማስወገድ ጥረቱ አልተሳካለትም።

እዚህ ጋር ብዙ ጥልቅ እውነቶች አሉ፤ አንደኛው፥ በሕይወታችን የሆነ ወቅት እያንዳንዳችን የምንጠይቀውን፥ "በምድር ላይ ክፉ ለምን ይኖራልን?" ጥያቄ ይመልሳል። ክፉ የሚኖርበት ምክንያት እግዚአብሔር እርሱን የሚመስሉ ፍጡሮችን ለመፍጠር በመወሰኑ ነው። እግዚአብሔር እኩይ ጎን አለው እያልኩ አይደለም። ያልኩት፥ እግዚአብሔር ሰውን፥ የተባለውን እንደሚፈጽም ኮምፒውተር ወይም ሥጋ ለበስ ሮቦት አድርጎ መፍጠር አልፈለገም ነው።

የመጨረሻው ነጥብ አስፈላጊ ነው። እርሱን መምሰላችን እውነተኛ መሆን አለበት። እውነተኛ ውሳኔዎችን ለመወሰን እውነተኛ ነጻነት ከሌለን፥ በዐጭሩ እግዚአብሔርን መምሰል አንችልም። እግዚአብሔር ሮቦት አይደለም፥ እኛም እርሱን እንድንመስል ሆነን ተሰርተናል። ያለ እውነተኛ ነጻ ፈቃድ፣ እግዚአብሔርን የእውነት መውደድና መታዘዝ አንችልም። ውሳኔዎቻችን ቀድመው የተወሰኑ ከሆኑ፣ እውነተኛ ውሳኔዎች አይደሉም። ፍቅርንና መታዘዝን የሚመለከቱ ውሳኔዎቻችን እውነተኛ እንዲሆኑ ከተፈለገ፥ የግድ ሊመረጡ ከሚችሉ፥ እውነተኛ ተቃራኒ ምርጫዎች አንጻር የሚደረጉ ሊሆኑ ይገባል።

ሰዎች፥ የእግዚአብሔርን አስደናቂ የነጻነት ስጦታ ለራስ ደስታ፥ ለበቀል እንዲሁም ለራስ-ገዝነት ህልም በመጠቀማቸው እኩይ መጣ። ስጦታን ያላግባብ መጠቀም በዔድን ተጀመረ።

እግዚአብሔር በዚህ አልደነገጠም። ክፉ እንደሚመጣ አስቀድሞ ጠብቋል። ምን እንደሚሆን አስቀድሞ ስላየ፥ አስቀድሞ ዕቅዶ ነበር። እግዚአብሔር፥ የሰው ልጆቹን፥ ከአመጻቸው የተነሣ አላጠፋቸውም። ይልቁንም፥ ይቅር ሊላቸውና ሊቤዣቸው ፈለገ። እግዚአብሔር የሚመጣውን ነገር አስቀድሞ እንዳየ፥ ዐመጹ ከመደረጉ በፊት የይቅርታንና የድነትን ዕቅድ ማዘጋጀቱን መጽሐፍ ቅዱስ "ዓለም ሳይፈጠር በፊት" በማለት በግልጥ አስቀምጧል (ኤፌ 1፥4፤ ዕብ 9፥26-10፥7፤ 1ጴጥ 1፥20)።

በመጨረሻም፥ የድነት ዕቅድ የእግዚአብሔር ሰው መሆንን ግድ ይላል። ይህን ታሪክ፥ በኋላ በሚገባ እናያለን። ያ ትልቁ ክስተት ከመሆኑ በፊት፥ በዔድን ስለሆነው የሚከፈል ክፍያ አለ። እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን (ልጆቻቸውንም ያጠቃልላል) ከሕልውናው አባረራቸው። ዔድን አልተገኘችም። ከአባታቸው ከእግዚአብሔር ጋር በዘላለም ሕይወት በመኖር ፈንታ፣ ሰዎች ሞትን መጠባበቅ

ጀመሩ (ሮሜ 5፥12)። ከሕይወት ምንጭ፥ ማለትም ከእግዚአብሔር መለየት በመጨረሻ የሚያስከፍለው ይህ ነው።

በዚህም ጠንቅ፥ እግዚአብሔር ልጆቹን ከቤቱ አባረረ። እባቡ ይፈልገው ከነበረው፣ ማለትም ከሰው ልጆች ጥፋት፣ ይህ የተሻለ ነበር። እግዚአብሔር ምድራዊ ቤተ ሰብ እንዲኖረው ያሰበውን ዕቅድ አልተወውም፤ ነገር ግን ዐመፅ ዋጋን ያስከፍላል። እግዚአብሔር ሰይጣንንም ቀጣው። ወደ እግዚአብሔር ምድር ሞትን በማምጣቱም፥ በኋላ ሲኦል ተብሎ ለሚታወቀው የሙታን ግዛት ጌታ ሆነ።

*ተጠባባቂ ዕቅድ የለም*

በአሁኑ ሰዓት፥ እግዚአብሔር የምድራዊ ቤተ ሰብ እንዲኖረው ማቀዱን፥ *ሙሉ በሙሉ ለምን አልተወውም* ብለን እንገረም ይሆናል። ለነገሩ፥ እግዚአብሔር ነጻ ፍቃድን ሲሰጥ፥ ወደ ኀጢአትና ከዐመጽ፥ ከራስ ወዳድነት፥ የሰው ልጆችም እርስ በእርስ ከሚፈጽሙት ክፉ ምግባር ከሚወለድ፥ በሺዎች ዓመታት ሊቆጠር ወደሚችል ሥቃይ እንደሚመራ እያወቀ ነው። ምናልባትም እያለፋችሁበት ያለው ወይም በዙሪያችሁ የምታዩት መከራ፥ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ቢያጠፋ ብላችሁ እንድትመኙ እድርጓችሁ ይሆናል።

አመናችሁትም አለመናችሁትም፥ እግዚአብሔር ያ ስሜት ይገባዋል። የምታዩትንና ከምታዩት በላይ ያለውን ክፋት እርሱ ያያል። እንዲህ እንዲሆንም የእርሱ ፍላጎት አልነበረም። ግን፥ እንዴ! እርሱ እኮ *አምላክ* ነው፣ እነዚህን ሁሉ መሻር አይችልምን? ትሉ ይሆናል። ጉዳዩ ያን ያህል ቀላል አይደለም። አስቡት። እግዚአብሔር ክፉን ከምድር ላይ ማስወገድ የሚችለው ክፉን የሚያደርጉትን ሁሉ ካስወገደ ነው። በሌላ አባባል፥ እግዚአብሔር ክፉን ማስቆም የሚችለው እኛን ሁሉ ካጠፋ ብቻ ነው። ሁሉም ኀጢአትን አድርገዋል (ሮሜ 3፥10-12)፤ መጽሐፍ ቅዱስም እንደሚለው፣ "የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል" (ሮሜ 3፥23)። በእርግጥ እግዚአብሔር ያንን ማድረግ ይችል ነበር። ነገር ግን አላደረገውም። እግዚአብሔር የሰው ልጅን እጅግ ከመውደዱ የተነሣ፥ ሰውን ማጥፋት ምርጫው አልነበረም።

ይህ ወደ አንድ አስደናቂ እውነት ይመራናል፦እግዚአብሔር እኛን በእርሱ አምሳል መፍጠሩ ወዴት እንደሚመራ ቢያውቅም፣ *ውጤቱ ምድራዊ ቤተሰብን ከማጣት ይልቅ ተመረጠ*። ። እግዚአብሔር በምድር ላይ ያለውን ኀጢአትና ሥቃይ ያያል፥ መንስዔውንም ያውቃል። ይህ ይጎዳዋል። እግዚአብሔር በሰው ልጆች ፍቅር የተያዘ በመሆኑ፥ *መጀመሪያ* ከነበረው ዕቅድ አላፈገፈገም። ሌላም ሁለተኛ አማራጭ ዕቅድ የለም። የመጀመሪያው ዕቅድ ብቻ ነው ያለው። እግዚአብሔር በዔድን የሚመጣውን ዐመጽ፥ እንዲሁም የሚከተሉትን ውድቀቶችና ኀጢአት—

የእኛንም ጭምር—አስቀድሞ ቢያይም፣ እግዚአብሔር ምድራዊ ቤተ ሰብ እንዲኖረው እስከ አሁን ይናፍቃል።

በዔድን የተፈጸመው ገና የታሪኩ ጅማሬ ነው። እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ከቤቱ አባረራቸው (ዘፍ 3፥22-24)። እባቡንም ረገመው (ዘፍ 3፥14-15) ከህልውናውም አባረረው (ኢሳ 14፥12-15፤ ሕዝ 28፥16)። መልእክቱ ጠንካራም ቀላልም ነው:-ዐመፅ መቀጣት አለበት። ይህን ሰው ሁሉ ይረዳል ብላችሁ ታስቡ ይሆናል። በፍጹም። ነገሮች ይበልጥ እየከፉ ሄዱ።

*ዐመፅ# 2*

መጽሐፍ ቅዱስ፥ እኩይ በምድር ላይ የመጣበት ምክንያት የሰው ልጅ በዔድን የአትክልት ሥፍራ በመውደቁ ነው፥ የሚል ትምህርት እንዳለው ሰምታችሁ ይሆናል። ያ ግማሽ እውነት ነው። በዔድን ከተፈጠረው አሳዛኝ ክስተት በኋላ የሰው ልጅን ጥልቅ ወደ ሆነ ብክለትና ውጥንቅጥ የከተቱ፥ ሁለት ተጨማሪ ድርጊቶች ተፈጥረዋል።

የመጀመሪያው በዘፍ 6፥1–4 የሚገኝ ሲሆን፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም እንግዳ ከሚባሉ ትረካዎች አንዱ ነው። (እመኑኝ፥ ወጥ የሆኑ መጽሐፍት በጉዳዩ ጽፌያለሁ)። ትረካውም፥ አንዳንድ የእግዚአብሔር ልዕለ ተፈጥሮአዊ ልጆች (“የእግዚአብሔር ልጆች”) *እነርሱን የሚመስሉ* የሰው ልጆችን በመውለድ እግዚአብሔርን ለመኮረጅ መሞከራቸው ነው። ለዓላማቸውም ሴቶችን(“የሰውን ሴቶች ልጆች”) ተጠቀሙ። ይህ በሰማዩ አባታቸው ላይ ጠላት አደረጋቸው። እግዚአብሔር ሰውን የቤተ ሰቡ አባል ማድረግ በመፈለጉ ከመደሰት ይልቅ፥ ራሳቸው በወለዷቸው ሰዎች ላይ ጌትነትን ፈለጉ። ያ የእግዚአብሔር ዕቅድ አልነበረም። እግዚአብሔር የፈለገው ቤተ ሰብን እንጂ ባሮችን አልነበረም።

እነዚህ “ኀጢአትን [ያ]ደረጉ መላእክት” (2 ጴጥ 2፥4) በሰማይና በምድር መካከል ያለውን ድንበር ጣሱ። እነርሱ፥ “መኖሪያቸውንም የተዉ[ትን]. . . የራሳቸውን አለቅነት ያልጠበቁ[ትን] መላእክት” ናቸው (ይሁዳ 6)። ከዚህ የተነሣም፥ እግዚአብሔር ወደ ሲዖል ጣላቸው (2 ጴጥ 2፥4–5፤ ይሁዳ 6)፤ ግን ድርጊቱ በመፈጸሙ፥ ትልቅ ጥፋት ተከተለ። ይህን ዐመፅ የሚተርኩልንን ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ቁጥሮች እንመልከት:-

> እግዚአብሔርም የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደ በዛ፥ የልቡ አሳብ ምኞትም ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደ ሆነ አየ። እግዚአብሔርም ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፥ በልቡም አዘነ። (ዘፍ 6፥5–6)

አስቡት፤ በእያንዳንዱ ሰው ልብ ውስጥ ያለው እያንዳንዱ አሳብ ሁል ጊዜ ክፉ ብቻ ሆነ። እግዚአብሔር ሰውን በመፍጠሩ ተጸጸተ፤ ልቡም ሐዘን ገባው።

የብክለትም ሆነ የሚያስከትለው ሐዘን ትርጉም ይህ ነው። የመጀመሪያው ልዕለ ተፈጥሮአዊ ዐመጽ፥ የሰው ልጅን ከእግዚአብሔር ጋር ካለ የዘላለም ሕይወት አጕደለው (ይህ እጅግ መጥፎ ነገር ነው)። ይህ ዐመጽ፥ የኀጢአትን ውጤቶች ከፍ ወደ አለ ደረጃ በመውሰድ፥ የሰውን ልጅ እራሱን በራሱ እንዲበላ (እንዲያጠፋ) አደረገ። ነገሮቹ በዚህ መንገድ መሄዳቸው፥ እግዚአብሔርን ጥልቅ የሆነ ጸጸት እንዲሰማው አደረጉት።

መጽሐፍ ቅዱስ፥ እግዚአብሔር የጥፋትን ውሃ ልኮ ሰውን ከምድር ላይ ከማስወገድ ውጭ ሌላ መፍትሔ እንዳላገኘ ይነገረናል (ዘፍ 6፥17)። የጥፋት ውሃ ትረካ፥ እግዚአብሔር ተቆጣ እንደማይል ማስተዋል ያስፈልጋል። በሆነው ነገር፥ ልቡ በሐዘን እንደተመታ ብቻ ይነገረናል። እግዚአብሔር ወስኖ ለሰዎች ነጻነትን ሰጥቷል። ነጻነታቸውን መልሶ ቢወስድ፥ እርሱን ስለማይመስሉና ሙሉ ሰው መሆናቸው ስለሚያበቃ፥ ነጻነታቸውን ሊወስድ አልቻለም። ያለው ብቸኛ ምርጫ፥ ዐመጸኞቹ የእግዚአብሔር ልጆች ያደረጉትን አጥፍቶ፥ ሁሉን እንደ ገና መጀመር ነው።

በእግዚአብሔር ዐይን ፊት የነበረው ጻድቅ ሰው ኖኅ ብቻ ነበር (ዘፍ 6፥9)። ቢያንስ አንድ ሰው ተገኘ። እግዚአብሔርም ያንኑ ሰው ተጠቅሞ፥ የሰው ቤተ ሰብን የማግኘት ዕቅዱን ገፋበት።

የኖኅ ቤተ ሰብና ብዙዎች እንስሶች ከጥፋት ውሃ ይተርፉ ዘንድ፥ እግዚአብሔር ኖኅን ትልቅ መርከብ ይሥራ ዘንድ አዘዘው። ምንም እንኳ የሰው ብልሹነት ጥልቅ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር የሰው ልጆቹ ከእርሱ ጋር ይሆኑ ዘንድ መፈለጉን አልተወም። ከምሕረቱም የተነሣ፥ ኖኅ ለጥፋት ውሃ ይዘጋጅ ዘንድ 120 ዓመታትን ሰጠው (ዘፍ 6፥3)፤ ከጥፋትም ተመልሰው ይቅር ይባሉ ዘንድ ሊመጣ ያለውን እንዲነግራቸው አዘዘው (2 ጴጥ 2፥5)።

በመጨረሻም ሕዝቡ አልሰሙም። የእግዚአብሔርን ምሕረት የተሞላ ማስጠንቀቂያ ቸል አሉ። ነጻነታቸውንም በመጠቀም፥ ልጆቹ በድጋሚ ከእግዚአብሔር ዘወር አሉ። ታዲያ የእግዚአብሔር ልብ ያን ያህል ቢሰበር ምን ይደንቃል? ነገር ግን ኖኅና ቤተ ሰቡ ነበሩ። ከጥፋት ውሃ በኋላ፥ እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን የሰጠውን የመጀመሪያ ትእዛዝ ድገመው (“ብዙ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት”፤ ዘፍ 9፥1)። እንደ ገና፥ እግዚአብሔር በኖኅ ቤተ ሰብ ጀመረ። የሰው ልጆችን ሁሉ የሚያጠቃልል ቃል ኪዳንን ከኖኅ ጋር ገባ (ዘፍ 9፥8–17)። ቃል ኪዳን ማለት ተስፋ እና መሐላ ነው። ይህ ቃል ኪዳን አንድዮሽ ነው፤ እግዚአብሔር

የሰውን ዘር ላለማጥፋት ተስፋን የሰጠበት ነው (ዘፍ 9፥11)። በሚያስደንቅ ሁኔታ፥ እግዚአብሔር አሁንም የሰው ቤተ ሰብን ፈለገ።

ባይገርምም፥ በማይተመን መልኩ፥ የእግዚአብሔርን መልካምነት መበደል የተለመደ ሆነ። ሦስተኛው ዐመፅ የጥፋት ውሃን ተከትሎ መጣ። ይህኛው፥ የቀሩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች እንደ ክፈፍ የሚይዝና፥ ሊያሸንፉት የማይችሉትን የእግዚአብሔር ትዕግስትና ፍቅር ማሳያ ነው።

*ዐመፅ# 3*

እንደ አዳምና ሔዋን እንዲሁም እንደ ኖኅ ታሪክ፥ ስለ ባቢሎን ግንብ ሰምታችሁ ይሆናል። ካልሰማችሁ፥ ምንም አይደል፥ ምክንያቱም ብዙ ቤተ ክርስቲያን ሂያጆች ታሪኩ ላይ *በእርግጥ* ምን እንደተፈጸመ አያውቁም።

የባቢሎን ግንብ ታሪክ በዘፍ 11፥9–11 ላይ ይገኛል። ከጥፋት ወሃ በኋላ፥ እግዚአብሔር የኖኅ ቤተ ሰብ እንዲባዙና ምድርን እንዲሞሉአት ፈለገ። ልክ እንደ አዳምና ሔዋን፥ ፍጥረትን ከእግዚአብሔር ጋር በመሆን እንዲንከባከቡ ትእዛዝ ተሰጣቸው። በዚህ ፈንታ ግን፥ ባቢሎን በሚባል ስፍራ ተከማችተው፥ ለራሳቸው ክብር ግንብን ገነቡ (ዘፍ 11፥1)።

ይህ ሰዎች የሚያውቁት ትረካ ነው፥ የዚህ ታሪክ ዋናው ቁም ነገር የሚገኘው በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ በሚገኙ ሁለት እንግዳ ቁጥሮች ውስጥ ነው።

> ልዑል ለአሕዛብ ርስታቸውን በሰጠ ጊዜ፥ የሰውንም ዘር በለያየ ጊዜ፥ በእስራኤል ልጆች [የእግዚአብሔር ልጆች][4] ቁጥር ልክ፥ የአሕዛብን ርስት ድንበር ለየ። የእግዚአብሔር (ያህዌ) ድርሻ የገዛ ሕዝቡ፥ ያዕቆብ የተለየ ርስቱ ነውና። (ዘዳ 32፥8–9 አ.መ.ት)

እነዚህ ሁለት ቁጥሮች፥ በባቢሎን ግንብ ከተፈጸሙት ፍርዶች አንዱ የሰው ዘር መለያየት እንደ ሆነ ይናገራሉ። እስከዚህ ታሪክ ድረስ፥ እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር የነበረው የግንኙነት ይዘት ጥቅላዊ ነበር። ያ በባቢሎን ተቀየረ። የሰው ልጆች በቋንቋና በመልክአ ምድር ተከፋፈሉ።

---

[4] በዘዳ 32፥8 ላይ አዲሱ መደበኛ ትርጉም “በእስራኤል ልጆች” ምትክ የማሶሬቱ ቅጅ፥ የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም እንዲሁም የሙት ባህር ጥቅል “የእግዚአብሔር ልጆች” ይላሉ ይላል። የዚህ መጽሐፍ ደራሲም፥ የ “እግዚአብሔር ልጆች” የሚለው የተመረጠ ቀደምት ጽሑፍ እንደሆነ ያምናል።

ይባስ ብሎ፥ እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ራሱን ለየ። ፍቃዱን በሚጥሱት የሰው ልጆች በማዘን፥ምድራዊ አገራትን እንደ ርስት ለሌሎች የልእለ ተፈጥሮአዊ ቤተ ሰብ አባላት፥ ማለትም ለእግዚአብሔር ልጆች አሳልፎ ሰጠ። እነዚህ፥ ከጥፋት ወሃ በፊት ከበደሉት የተለዩ ቡድን ናቸው። እግዚአብሔር ሰውን ከቤቱ ማባረር አልቻለም። ያንን፥ በዔድን አድርጓል። ከጥፋት ውሃ በኋላ ግን ሰውን ላለማጥፋት ተስፋን ስለሰጠ (ዘፍ 9፥11)፥ *ያ ዐይነት ጥፋት አይደገምም*። *ታዲያ ምን ማድረግ ይችላል*? ባጭሩ ይህንን ነው ያለው፥ “በቃ! አምላካችሁ እንድሆን ካልፈለጋችሁ፥ ሰማያዊ ረዳቶቼን በእናንተ ላይ እሾምላችኋለሁ።”

የዚህ ፍርድ ውጤት በተለያዩ መንገዶች ተገልጿል። ምን ያህል ጊዜ እንደወሰደባቸው ባይነገረንም፥ እግዚአብሔር በአሕዛብ ላይ የሾማቸው ልእለ ተፈሮአዊ ልጆቹ መጥፎ ሥራን እንደሰሩ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ከመበላሸታቸው የተነሣ (መዝ 82፥1–5)፥ እነርሱ ላይም እግዚአብሔር መፍረድ ነበረበት። አንድ ቀን፥ ዘላለማዊነታቸውን ገፎ፥ አገራትን ለራሱ ይወስዳል (መዝ 82፥6–8)። ለተነሣንለት ዓላማ ስንል ይህን እንረዳ፡-ምድራዊ ቤተ ሰብን በተመለከተ፥ እግዚአብሔር አሁን ልጅ አልባ ሆነ። ሁሉን አየ። ተስፋን ቆረጠ...በርግጥ... ገና አልቆረጠም!

*የእግዚአብሔር ጽኑ ፍቅር*

የባቢሎን ግንብ ከወደቀ በኋላ ምን እንደ ሆነ እስቲ ገመቱ? እግዚአብሔር፥ የመውለጃ ዕድሜዋ ያለፈባት ሣራ የምትባል ያረጀችን ሴት ላገባው፥ ለአብርሃም(የመጀመሪያ ስሙ አብራም ነበር) ተገለጠለት። እግዚአብሔርም ለአብርሃም ቃል ኪዳን ገባለት። እግዚአብሔር፥ ሽማግሌውና ሚስቱ ወንድ ልጅን እንደሚወልዱ፥ ተስፋ ሰጣቸው። እግዚአብሔርም ተዓምርን አደረገ፤ ልጁም ለእግዚአብሔር አዲስ ምድራዊ ቤተ ሰብ ጅማሬ ሆነ (ዘፍ 12፥1–9፤ 15፥1–6፤ 18፥1–15)።

እግዚአብሔር የሰውን ልጆች ርስት አድርጎ ለሰማያዊ ሠራዊቱ ከሰጠ በኋላ፥ የራሱ የሆነውን አዲስ ቤተ ሰብ በአብርሃም በኩል ጀመረ። አብርሃም የእግዚአብሔርን ተስፋዎች አመነ (ዘፍ 15፥6)። የእግዚአብሔርን ሞገስ ወይም ፍቅር ለማግኘት አብርሃም ያደረገው ምንም ነገር አልነበረም። አብርሃምን መርጦ እንደ አዲስ እንዲጀምር ያደረገው *እግዚአብሔር* ነው። በእግዚአብሔርና በአብርሃም መካከል የነበረው ግንኙነትም በእግዚአብሔር የተጀመረ ነው። አብርሃምም አመነ።

በኋላም፥ በእግዚአብሔር ጥሪና በአብርሃም እምነት የተጀመረው የቃል ኪዳን ግንኙነት አካላዊ በሆነ ግርዘት ተዘከረ (ዘፍ 17፥1–14፤ ሮሜ 4፥1–12)።

መላው የአብርሃም ቤተ ሰብም፥ ምሳሌውን ተከተሉ (ዘፍ 17፥23)። የግርዘትን ምልክት  መቀበል እግዚአብሔር የአብርሃም ዘርን ቤተ ሰቡ ማድረጉን ያመላክታል። በአብርሃም ዘር ላሉ ሴቶችም ግርዘት ምልክት ነበር። ጋብቻቸውን የሚፈጽሙት ከራሳቸው ዘር ጋር በመሆኑ፥ የራሳቸው ልጅ እንዲኖራቸው በወሰኑ ጊዜ፥ የዘራቸው ጅማሬ በተዓምራት ከአብርሃምና ከሣራ እንደሆነ ያመላክታቸዋል።

እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባው ቃል ኪዳን በእግዚአብሔር ተስፋ ላይ ባለ እምነት የተመሠረተ መሆኑን መረዳት አስፈላጊ ነገር ነው። እግዚአብሔር አብርሃምን የቀረበው አብርሃም ጥሩ ትእዛዝ ጠባቂ ስለሆነ አይደለም። ድነት በምግባር ላይ የተመሠረተ አይደለም፤ ድነታችንን መግዛት አንችልም። ያ ቢሆን ኖሮ፥ እግዚአብሔር ከሥራችን የተነሳ *ባለዕዳችን* ይሆን ነበር። ለሥራችንም ክፍያን መስጠት ግድ ይለው ነበር። ይህ ምን ያህል እንግዳ እንደሆነ ተመልከቱ። በዚህ ምትክ፥ አብርሃምና ዘሩ እምነታቸውን የቃል ኪዳኑን ምልክት በመጠበቅ አሳዩ። ግርዘትም፥ ለእግዚአብሔር ማደራቸውን ማሳያ ውጫዊ ምልክት ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ አብርሃምን በእምነት ስላለ ታማኝ አማኝነት ምሳሌ አድርጎታል (ሮሜ 4፥1–12)። የትኛውንም ትእዛዝ ከመፈጸሙ በፊት፥ ከእምነቱ የተነሣ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን አግኝቶ ነበር። ፍሬ ነገሩ እምነቱ ነበር። በእግዚአብሔር ስላለው እምነት–ታማኝነት–በኋላ እንመለስበታለን። ዛሬ ይህንን ደቀ መዝሙርነት እንለዋለን። እምነትና ታማኝነት ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው፤ ግንኙነት ቢኖራቸዋም ተለዋዋጭ ግን አይደሉም። ድነትና ደቀ መዝሙርነትም እንዲሁ ናቸው።

ለአብርሃም የተሰጠው የልጅ ተስፋ ( በልጁም፥ ታላቅ ሕዝብ የሚሆን አዲስ ቤተ ሰብ) እግዚአብሔር ከዔድን ጥፋት በኋላ የገባው ሁለተኛው ቃል ኪዳን ነው። የመጀመሪያው ከኖኅ ጋር ነበር። ሁለቱም የእግዚአብሔርን ምድራዊ ቤተ ሰብ የማግኘት ሕልም ለመጠበቅ የተገቡ ናቸው። እነዚህ ቃል ኪዳኖች፥ እግዚአብሔር ተስፋ እንዳልቆረጠ የሚያሳዩ ብቻ አይደሉም። ይልቁንም እግዚአብሔር የዘላለምን ሕይወት ለሕዝቡ ለመስጠት እጁን መዘርጋቱን ይናገራሉ። እግዚአብሔር ሰዎችን መውደዱን ማቆም አልቻለም። እግዚአብሔር አሁንም ምድራዊ ቤተ ሰብን ይሻል።

እግዚአብሔር ለአብርሃምም የገባውን ተስፋ ጠበቀ። አብርሃምና ሣራ ወንድ ልጅን (ይስሐቅን) ወለዱ (ዘፍ 17፥19–21፤ 21፥1–7)። የአብርሃምም ዘር እስራኤል በመባል ታወቁ፥ ይህ ስም በብሉይ ኪዳን ለእግዚአብሔር ምድራዊ ቤተ ሰብ በብዛት የዋለ ነው (ዘፍ 32፥28፤ ዘጸ 32፥9፤ ኢሳ 44፥1)። ከባቢሎን ግንብ ዐመፅ በኋላ ለልዕለ ተፈጥሮአዊ የእግዚአብሔር ልጆች ታልፈው የተሰጡት

ሀገሮችስ ዕጣቸው ምንድን ነው? በመጽሐፍ ቅዱስ፥ እነዚህ “አሕዛብ” ተባሉ፥ ይህም “ከእስራኤል ውጭ” ያሉትን ሁሉ የሚያመላክት ቃል ነው። ምንም የባቢሎን አምጽ ቢከስተም፥ እግዚአብሔር እነዚህን ህዝቦች አልረሳቸውም።

እግዚአብሔር አዲስን ሕዝብ (እስራኤልን) እንደ ገና መጀመር ብቻ ሳይሆን፥ የአብርሃም ዘር አንድ ቀን እርሱ ለተዋቸው የምድር ነገዶች በረከት እንደሚሆኑ ለአብርሃም ነገረው (ዘፍ 12፥3)! ከብዙ ዓመታትም በኋላ፥ የአብርሃም ዘር የሆነው ኢየሱስ፥ የምድር ነገዶች ወደ እግዚአብሔር ለመምጣታቸው ምክንያት ሆነ (ገላ 3፥16–18፡ 26–29)። ኢየሱስም ከመጣቱ በፊትም፥ አሕዛብ ሌሎች አማልክትን ከተዉና በእግዚብሔርም አምነው የቃል ኪዳኑን ምልክት ከተቀበሉ፥ የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ አባል መሆን ይችሉ ነበር።

በአብርሃምና በኢየሱስ መካከል ብዙ ዘመናት አለፉ። እስራኤል “እንደ እግዚአብሔር ርስት” (ዘዳ 32፥9) የነበራት ታሪክ ግን ማራኪ አልነበረም። የእግዚአብሔር ሕዝብ ነበሩ፤ በሚያሳዝን ግን በሚጠበቅ መልኩ ታማኝ አልነበሩም። የጨለማው ሰዓት ገና እየመጣ ነበር።

## ምዕራፍ ሦስት

## እግዚአብሔር በቤተ ሰቡ ተከዳ

የመጽሐፍ ቅዱሷ እስራኤል ውድቀትና ድል የተሞላ ረጅምና ጥምዘምዝ ታሪክ አላት። እግዚአብሔርም ከሰዎች የሚጠበቅውን ስለሚያውቅ ይህ አላስደነቀውም። ከመጀመሪያውም እግዚአብሔር ከማን ጋር እየተደራደረ እንደሆነ ያውቃል።

*ፊት የተነሣ እንግዳ*

የአብርሃም ዘር ወደፊት አስቸጋሪ ጊዜ እንደሚገጥማቸው፥ እግዚአብሔር ለአብርሃም አሳውቆታል። እንዲህ በማለት፥ “ዘርህ ለእርሱ ባልሆነች ምድር ስደተኞች እንዲሆኑ በእርግጥ እወቅ፤ ባሪያዎች አድርገውም አራት መቶ ዓመት ያስጨንቋቸዋል” (ዘፍ 15፥13)። ያ መጥፎ ዜና ነበር። እግዚአብሔር ግን ተጨማሪ ተስፋን ሰጠ፦ “ደግሞም በባርነት በሚገዙአቸው ሕዝብ ላይ እኔ እፈርዳለሁ፤ከዚያም በኋላ በብዙ ከብት ይወጣሉ” (ዘፍ 15፥14)።

እንደተባለውም፥የአብርሃም ዘሮች፥ እግዚአብሔር ስሙን “እስራኤል” ብሎ በለወጠው የአብርሃም የልጅ ልጅ ያዕቆብ ተመርተው፥ በግብፅ በፈርዖን ቁጥጥር ሥር ዋሉ (ዘፀ 1)። ወደ ግብፅ የሄዱት፥ በእግዚአብሔር ፍቃድ ረሃብን ያመልጡ ዘንድ ነው (ዘፍ 45፥5–11)። ችግሩ የተፈጠረው፥ የረሃቡ ዘመን ከተፈጸመ በኋላ እግዚአብሔር ወደ ሰጣቸው ምድር ባለመመለሳቸው ነው። በግብፅ መቆየት ካለባቸው ጊዜ የበለጠ ቆዩ።

በግብፅ የነበሩ እስራኤላውያን በበዙ ቁጥር፥ ፈርዖን በሀገሩ ላይ የነበረውን ሥልጣን እንዳያጣ ሠጋ (ዘፀ 1፥8–10)። በእስራኤላውያን ላይ አድካሚ ሥራን ጫነባቸው፤ አዲስ የሚወለዱ ወንዶች ልጆቻቸውንም ገደለ (ዘፀ 1፥14–16)። እግዚአብሔር ግን ጣልቃ በመግባት እስራኤላውያን እንዲያይሉ አደረገ (ዘፀ 1፥8–21)።

እስራኤላውያን ለአራት መቶ ዓመታት በአስቸጋሪ ሀኔታ በግብፅ ኖሩ። በመጨረሻም፥ እግዚብሔር ጣልቃ በመግባት፥ ሙሴ የተባለ ወንድ ልጅን ሕይወት አዳነ። ሙሴ በፈርዖን ቤት በአፍንጫው ሥር ያድግ ዘንድ እግዚአብሔር ሁኔታዎችን አመቻቸ (ዘፀ 2፥1–10)። ረዳት የለሹን እስራኤላዊውን ለመታደግ በተጀመረ ጥል ግብፃዊውን እስከገደለበት ቀን ድረስ፥ ሙሴ የተደላደለ ሕይወትን ይመራ ነበር። ፍትህንም ሽሽት ከግብፅ ተሰደደ።

ምድያም በሚባል ምድረ በዳም አዲስ ሕይወት ጀመረ። የዓለምንም ሆነ የእስራኤልን ሕዝብ ታሪክ በለወጠ ሁነት፥ እግዚአብሔር ሙሴን በሲና ተራራ በሚነድ ቁጥቋጦ ውስጥ ተገናኘው (ዘፀ 3፥1–15)። ፈርዖንንም ይገጥም ዘንድ እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ግብፅ ላከው። ፈርዖን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ይለቅ ዘንድ ሙሴ መናገር ነበረበት። በምትኩም እግዚአብሔር ሙሴን ሊጠብቅ ኀይልንም ሊሰጠው ተስፋ ገባ (ዘፀ 3፥16–22)።

የቀረው ታሪክ በዓለም ላይ በጣም ከሚታወቁት አንዱ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን አንብባችሁ ባትውቁ አንኳ ይህን ታሪክ ወይ ሰምታችሁታል ወይ በፊልም አይታችሁታል። ፈርዖን እስራኤላውያንን አልለቅም በማለቱ እግዚአብሔር በግብፅና በአማልክቶቿ ላይ መቅሰፍትን ላከ (ዘፀ 7–12)። ከግብፅ ባርነትም እስራኤልን በግድ ነጻ ያወጣ ዘንድ እግዚአብሔር ሙሴን ተጠቀመበት። ግብፃውያን እስራኤላውያንን ለመግደል ወስነው ወደ ምድረ በዳ ሲያሳድዱአቸው፥ እግዚአብሔር ሊያድናቸው ቀይ ባሕርን ከፈለ (ዘፀ 13፥17 እስከ ዘፀ 14)። የቀይ ባሕር መከፈል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጻፉት ተዓምራቶች እጅግ አስደናቂው ነው፤ መዝናኛ ግን አልነበረም። የርሱ የሆነውን ሕዝብ ለማዳን የተፈጸመ ነው። እግዚአብሔር ቤተ ሰቡን ፈለገ።

ሕግና ታማኝነት

ቀስ በቀስ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለሙሴ አስቀድሞ ወደ ተናገረው ሥፍራ አመጣቸው፤ በዚያም ሕጐቹን ማለትም አሥርቱን ትእዛዛት ለእስራኤላውያን ሰጣቸው። ከእነርሱም ጋር ቃል ኪዳን ገባ። አሥሩ ትእዛዛት ከመሰጣቸው በፊት፥ እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደነበሩ ማወቅ አስፈላጊ ነው። ፈርዖንን ለመግጠም ሙሴ በሄደበት ወቅት እግዚብሔር ሕዝቡን ቤተ ሰቡ እንደሆነ ተናግሯል (ዘፀ 3፥7፡10፤ 4፥23፤ 5፥1፤ 6፥7፤ 7፥4)። ሕጉ የእግዚአብሔር ቤተ ሰብነትን *እንዲያስገኝላቸው* የተሠጠ አይደለም። እስራኤላውያን *ቀድሞም* የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ ነበሩ።

ይህ ልዩነት አስፈላጊ በመሆኑ የበለጠ ማብራራት አለብን። እግዚአብሔር ሕጉን የሰጠው ህዝቡ በቤተ ሰቡ ውስጥ ሥፍራቸውን እንዲይዙበት ሳይሆን *በቤተ ሰቡ ውስጥ መሆን መፈለጋቸውን እንዲያሳዩበት ነው።* ሕጉ፥ ታማኝነታቸውን እንደማያጐድሉና ሌላ አምላክን እንደማይከተሉ ለእግዚአብሔር የሚያሳዩበት መንገድ ነው። ታማኝ አማኝ መሆናቸውም፥ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እንደ "ካህናት መንግስት" በመጠቀም ሌሎቹን ሀገራት እንዲያገለግሉ ይጠቀምባቸው ዘንድ ይረዳዋል (ዘፀ 19፥5–6)። ሰዎችን ቤተ ሰቡ እንዲሆኑ እግዚአብሔር ፈልጓል፤ ይህን በአንድ ቡድን ማለትም በእስራኤል እየጀመረ ነው። ታማኝ አማኞች ቢሆኑ፥ ለምድር ነገዶች ሁሉ በረከት ይሆናሉ (ዘፍ 12፥3)።

ይህንን ቃል ኪዳን ለመረዳት አንድ ተጨማሪ አቅጣጫ አለ። ሕጉ ብቁ ሆነው በመገኘት፥ የእግዚአብሔርን ፍቅር የሚገዙበት መንገድም አይደለም። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን አስቀድሞ ወዶአል (ዘዳ 7፥7–8)። እግዚአብሔር፥ ዕድሜያቸው ለገፋው ለአብርሃምና ሣራ መለኮታዊ ኀይልን ሰጥቶ ለእስራኤላውያን መገኘት ምክንያት የሚሆንን ልጅ እንዲወልዱ አድርጓል። ቁም ነገሩ ቤተ ሰብን ማግኘት ነበር። እግዚአብሔር የትእዛዛት ዝርዝር የሰጠው ለቤተ ሰብነት ብቁ እንዲሆኑበት አይደለም። ቤተ ሰቡ ናቸው። የእግዚአብሔር ሕጎች የተዘጋጁት እስራኤላውያን ሌሎቹን አማልክት እንዳይከተሉ፥ በደስታ እንዲኖሩ፥ እርስ በርሳቸውም በሰላም እንዲኖሩ እንጂ እግዚብሔር ለእነርሱ ያለውን ፍቅር መለኪያ እንዲሆኑ አይደለም።

እንደተባለው እግዚአብሔር ነጻ ፍቃዳቸውን መጣስ አልፈለገም። የጠየቃቸው በእርሱ እንዲያምኑ፥ማለትም ማን እንደሆነና በፍቅር እንደፈጠራቸው፥ እንዲሁም ሌሎቹን አማልክት እንዲተዉ ነው። ማንኛቸውም እስራኤላውያን ከፈለጉ የእግዚአብሔርን ፍቅር መተው ይችላሉ። አለማመንንም መምረጥ ይችላሉ። ሌላ አምላክንም መርጠው ማምለክ ይችላሉ። በኋላ እንደምንመለከተው፥ ብዙዎች ይህን መርጠው ነበር።

እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ሕግ የተቀበሉበትን የሲና ተራራ ከለቀቁ በኋላ እግዚአብሔር ወደ ተስፋይቱ ምድር በሰው መልክ (እንደ መልአክ) ተመስሎ መራቸው (ዘፀ 23፥20–23፤ መሳ 2፥1)። ሕዝቡ በመንገድም ሳሉ፥ በቂ ምግብና ውሃ የለንም በማለት አጉረመረሙ። እግዚብሔርም አዘጋጀላቸው (ዘፀ 15፥22–27፤ 16፥1–30)። በምድሪቱ ላይ ከነበሩ ገዳይ ጠላቶች ጋር መዋጋት ነበረባቸው። እግዚአብሔር ግን ከጥፋት አዳናቸው (ዘዳ 2–3፤ ኢያ 11–12፤ መዝ 136፥10–24፤ ሐዋ 13፥19)።

*ጠመዝማዛው ቁልቁለት*

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ወደ ምድሪቱ ካስገባቸው በኋላ ለርሱ ያላቸው ፍቅር ጥልቅ የሆነ እምነታቸውና ታማኝነታቸው ትልቅ የሆነ ይመስላችሁ ይሆናል። ያ አልሆነም። በምትኩም፥ ከክፋት ጋር አብሮ መኖርን መረጡ። የምድሪቱን ጣዖታሞች ማለትም ሌሎች አማልክት ተከታዮችን አላባረሩም። ዐመፅ ጥፋትን እንደሚያመጣ ካለፈው ታሪክ አልተማሩም። ክህደታቸውና እግዚአብሔርን አለመውደዳቸው ወደ ታላቅ የሞራል ስብራት ትዕይንት መራቸው።

> የእግዚአብሔርም መልአክ ከጌልጌላ ወደ ቦኪም ወጥቶ እንዲህ አለ፦ እኔ ከግብፅ አውጥቻችኋለሁ፥ ለአባቶቻችሁም ወደ ማልሁላቸው ምድር

አግብቻችኋለሁ፤ እኔም፡- ከእናንተ ጋር ያደረግሁትን ቃል ኪዳን ለዘላለም አላፈርስም፤ እናንተም መሠዊያቸውን አፍርሱ እንጂ በዚህች ምድር ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ቃል ኪዳን አታድርጉ አልሁ። እናንተ ግን ቃሌን አልሰማችሁም፤ ይህንስ ለምን አደረጋችሁ? ስለዚህም፡-ከፊታችሁ አላወጣቸውም፥ ነገር ግን ያስጨንቋችኋል፥ አማልክቶቻቸውም ወጥመድ ይሆኑባችኋል አልሁ (መሳ 2፥1—3)።

እግዚአብሔር በድጋሚ... በሕዝቡ ላይ መፍረድ ነበረበት። በመሠረቱ እያለ ያለው ይህንን ነው፡- "የለሁበትም፤ ስለማትፈልጉኝ፥ እስቲ በራሳችሁ ማድረግ የምትችሉትን አብረን እንይ።" ያንን ከዚህ በፊት አይተናል። አስቀድመንም እንዳየነው፥ እምላካቸው ከእነርሱ ጋር ባለመኖሩ የእስራኤል ልጆች መጥፎ ሆነባቸው። ታሪክን በድጋሚ እያወሳን በመሆኑ የእግዚአብሔርም ምላሽ የተለመደው ነበር፤ እግዚአብሔር ከችግራቸው ሊያወጣቸው ወደ እስራኤል ደጋግሞ ይመጣ ነበር። ሁላችንም እንደዚያ ዓይነት ሰዎችን እናውቃለን። ምናልባትም፥ እናንተ እንደዚያ ዓይነት ሰዎች ትሆኑ ይሆናል። አንዳንዴ ምክንያት በማታገኙለት መልኩ፥ ከፍቅር የተነሣ ርዳታን ለማድረግ ከሰዎች ጋር ትጣበቃላችሁ። እግዚብሔር እያደርገ የነበረውን ካሰባችሁት ዕብደት ይመስላል። ሰው ሳይፈልገው፥ ሰውን ቤተ ሰቡ እንዲሆን ፈለገ። ፍቅሩ አመክንዮን ይጥሳል።

ከላይ የጠቀስነውን ትዕይንት ያገኘንበት የመሳፍንት መጽሐፍ፥ የእስራኤልን የማያልቅ መንፈሳዊ የውድቀት አዙሪት ያስከተለውን መከራ፥ እርዳን የሚል ጩኸትንና የእግዚአብሔር በፍቅር መመለስን የሚገልጽ መጽሐፍ ነው። ይህ አዙሪት በመቶ ለሚቈጠሩ ዓመታት ዘልቋል። አዙሪቱ ጡዘት ላይ የሚደርሰው፥ የእስራኤል ልጆች፥ ነቢይና ካህን የነበረውን ሳሙኤልን የሚገዛቸው ንጉሥን እንዲቀባላቸው በጠየቁ ወቅት ነው።

የሕዝቡ ንጉሥ (የሳኦል) ምርጫ መታለፍ የማይቻል ጥፋትን ማምጣቱ አያስገርምም። መቼም የመረጥነው ንጉሥ፥ ሥራውን ሸሽቶ የሚደበቅ ከሆነ፥ ወደፊት ነገሮች ጥሩ እንደማይሆኑ ሊያሳየን ይገባል (1 ሳሙ 10፥22)። ውሎ አድሮ፥ እግዚአብሔር በሳኦል ምትክ ዳዊትን መረጠ። ዳዊት በሞራል ቀውስ የተዘፈቀ ቢሆንም ከሳኦል የተሻለ ነበር። ለእግዚአብሔር ፍቅርንም ሆነ ታማኝነትን አላጓደለም። ብዙዎቹን የእግዚአብሔር የምግባር ሕጎች ጥሷል ነገር ግን ንስሓ ይገባ ነበር፤ እንዲሁም ሌላን አምላክ አላመለከም። ከዚህም የተነሣ፥ ልጆቹ ብቻ በእስራኤል ላይ ህጋዊ ንጉሦች እንዲሆኑ እግዚአብሔር ለዳዊት የቃል ኪዳን ተስፋን ሰጠው።

ይህ ቃል ኪዳን ለዳዊት ሥረወ መንግስትን የሚመሠርት ነበር። እግዚአብሔር ሕጋዊ ንጉሥ እንዲሆን የመረጠው ከዳዊት ዘር የሆነውን ብቻ ነበር። በሚያሳዝን

መልኩ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኘው የእስራኤል ታሪክ፥ የንግሥና ዘር ያላቸው ነገር ግን ለንግሥና ብቁ ያልሆኑ ሰዎች ታሪክን የያዘ ነው። እግዚብሔር ሌሎቹን አማልክትን በመከተላቸውና ባለመታመናቸው ምክንያት ብዙ የዳዊት ዘሮችን ማስወገድ ነበረበት። ዙፋንን ወራሽ የሆነ የዳዊት ዘር ሁሉ እግዚአብሔርን መውደድና የትክክለኛው የቤተ ሰብ ታሪክ ተካፋይ መሆን ይጠበቅበት ነበር። ከዚህ የተነሣ፥ ንጉሥ የሆነ ሁሉ የእግዚአብሔርን የሕግ መጽሐፍ ቅጅ በግሉ ሊኖረው ይገባል (ዘዳ 17፥18፤ 2 ነገ 11፥12)። ታማኝ አማኝነት ምን ማለት እንደሆነ የሚያሳይ ላቅ ያለ ምሣሌ ሊሆን ይገባዋል።

ርስትና ሐብት የታላቅነት ማሳያዎች ከሆኑ፥ የዳዊት ልጅ ሰሎሞን በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ታላቁ ንጉሥ ነበር። አሳዛኝ በሆነ መልኩ፥ ለእውነተኛው አምላክ ያለው ታማኝነትና እምነት ጠወለገ። ለፖለቲካ ፋይዳ ይጠቅመኛል በማለት ለእስራኤል ጣዖትን ማምለክ ያስተማሩ ብዙ ጋብቻዎችን ፈጸመ፤ ለሌሎች አማልክትም ሠዋ (1 ነገ 11፥1–8)። በሌላ ቋንቋ፥ ሰለሞን ሐገራዊ ውድቀት ያስከተለ የዐመጽና የመንፈሳዊ ማመቻመች አዙሪት ጀማሪ ሆነ።

*የመጨረሻው ክህደት*

ከሰሎሞን ሞት በኋላ፥ ከአሥራ ሁለቱ ነገዶች አሥሩ በምትኩ በነገሠው ላይ ዐመጹ (1 ነገ 11፥41–12፥24)። የእስራኤል መንግስትም፥ በነገዶችና በመልክዓ ምድር ለሁለት ተከፈለ። ይህ፥ የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ እንደ ተበተነ ቤት ሆነ ማለት ነው። በተከታይ ዘመናት የነበሩት ንጉሦች የእግዚአብሔርን ሕግ ቅጂ እንኳ አይተው የማያውቁ መሆናቸው እጅግ የሚያሳዝን ጉዳይ ነበር (2 ነገ 22፥8–13)።

በተከፈለችው አገር በሰሜን የሚገኙት፥ በፖለቲካ ምክንያት ያመጹት አሥሩ ነገዶች፥ ወዲያውኑ ራሳቸውን በመንፈሳዊ ዐመፅ ውስጥ ዘፈቁት (1 ነገ 12፥25–33)። በመለኮታዊ ኃይል ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣቸውንና ምድሪቱን የሰጣቸውን እግዚአብሔርን ባለማመንና ታማኝነትን በማጉደል አብላጫው እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ከዱ። በየሀገሩ ይዞሩ የነበሩት ነቢያትም እስራኤል መንፈሳዊ ዝሙትን "ሴተኛ አዳሪ" በመሆን ፈጽማለች እያሉ ይሰብኩ የነበረው ለዚሁ ነው። ይህ ግልጽ ምሳሌ ነው። የደቡቡ ክፋይ ማለትም ሁለቱ ነገዶች ቀስ በቀስ ወደ መንፈሳዊ ዐመፅ አመሩ፤ ለነገሩ ቀስ በቀስ የሚደረግም ኀጢአት ያው ኀጢአት ነው።

እግዚአብሔርን መተው በመልካም አይጠናቀቅም። መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ ሥፍራ ይህንን ይላል፦ "ኀጢአታችሁም እንዲያገኛችሁ እወቁ" (ዘኁ 32፥23)። በሌላ ጊዜ እንዳደረገው፥ እግዚአብሔር ሰዎች ነጻነታቸውን እንዲጠቀሙ ቀጥሎም የሚመጣባቸውንም ጠንቅ እንዲቀበሉ ፈቀደ። በ722 ቅ.ዓ. ሰሜናዊው ክፍል፥

እኔ የብሉይ ኪዳን “ክሊንጐን”[5] በምላቸው በአሦራዊያን ተደመሰሰ። ከ “ስታር ትሬክ” ይልቅ “ሎርድ ኦፍ ዘሪንግስ” ፊልምን የምታውቁ ከሆነ፥ አሦራዊያን “ሆርድስ ኦፍ ሞርዶር”[6] ናቸው።

ምሳሌዎቹን የምወድበት መክንያት፥ አሦራዊያን በጭካኔያቸው እጅግ የታወቁ በመሆናቸው ነው። ቤተ ሰብን በመበተንና ያላቸውን ሁሉ በመዝረፍ፥ አሥሩ ነገዶችን በጥንታዊው ዓለም ሁሉ ላይ በታተኗቸው። በደቡብ የሚገኙትም ሁለቱ ነገዶች ከመቶ ዓመት ትንሽ በበለጠ ጊዜ (586 ቅ.ዓ.) በባቢሎናውያን ተገዙ። በሺዎች የሚቆጠሩ እስራኤላውያንም በግድ ወደ ባቢሎን ተጋዙ።

እስቲ እውነተኛ እንሁን። እግዚአብሔር አሁን ሕዝቡን ረስቶ ቢሆን እንረዳዋለን። ከአብርሃም ዘመን ጀምሮ በተደጋጋሚ ከሺህ ዓመታት ለሚበልጥ ጊዜ ዐምጸዋል። አሁን የእጃቸውን አገኙ  የሚለውን ማሰብ አስቸጋሪ አይደለም። እግዚአብሔር ግን የሚሠራው እንደዚያ አይደለም።

ከዚህ ወዲህ በቃ ማለት ሲገባው፥ እግዚአብሔር *አሁንም* ምድራዊ ቤተ ሰቡን ይሻል። ነገር ግን፥ ሕዝቡን እንዲሁም ቀሪውን የሰው ዘር ለማግኘት ሌላ ዘዴን መጠቀም ነበረበት። እግዚአብሔር ብዙ ቃል ኪዳኖችን ከሕዝቡ ጋር ገብቶ ነበር። ነገር ግን ሰዎች ሁል ጊዜ ሰው ብቻ ናቸው፤ እንደተለመደው ይወድቃሉ… ሁሌም። ለልዕለ ተፈጥሮዋዊው ፍጡሮች (የ “እግዚአብሔር ልጆች”፤ ዘዳ 32፥ 8) ተላልፈው የተሰጡትም ሀገራት የፈጣሪያቸው የእስራኤል አምላክ ጠላቶች ሆኑ። ነገሮች እጅግ ተወሳሰቡ።

እግዚአብሔር በሁለት የተከፈለ መፍትሔን አዘጋጀ። የመጨረሻዎቹ የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ አባላት ወደ ግዞት ከመሄዳቸው በፊት፥ እግዚአብሔር ሁለት ነቢያትን፥ ኤርምያስንና ሕዝቅኤልን፥ አስነሥቶ ሕዝቡ ፈጽሞ እንዳልተረሱ አስነገረ። ይልቁንም፥ እግዚአብሔር ከልጆቹ ጋር፥ በመንፈሱ መምጣት የሚጀመር “አዲስ ኪዳንን” እንደሚገባ ተናገረ (ኤር 31፥31–34፤ ሕዝ 36፥22–28)። አዲስ ቀን እየመጣ ነበር።

ነገር ግን “የሚመጣው አዲስ ቀን”፥ እግዚብሔር ቀድሞ የገባቸውን ቃል ኪዳኖች ሳይሽርና ሳይለውጥ ቃሉን እንዴት ይጠብቃል የሚለውን ጥያቄ አይመልስም። አብዛኞቹ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ንቀው ሌሎቹን አማልክት አምልከዋል።

---

[5] Klingons “ስታር ትሬክ” በተባለው ፊልም ላይ የሚገኙ እጅግ ጨካኝና ክፉ ገጽ ባሕርያቶች ናቸው

[6] እነዚህ፥ በ “ሎርድ ኦፍ ዘሪንግስ” ፊልም ላይ የሚገኙ ክፉዎች የሆኑ ገጸ ባሕርያት ናቸው።

ንቀታቸውንም ሕጉን በመጣስ አሳይተዋል። ይህ እግዚአብሔርን አሳዝኖታል። ተስፋዎቹንም ማክበር ይፈልጋል፣ ነገር ግን ብዙዎች ልጆቹ የአሕዛብን አማልክት በማምለክ ተታለዋል።

ያ የሞት መንገድ ነበር። ይህን አናስታውስ፤ በዔድን ከሆነው የተነሣ፥ እያንዳንዱ ሰው ወደ እውነተኛው አምላክ እስካልተመለሰ፥ በፍቅሩና በተስፋውም እስካላመነ ድረስ የዘላለም ሕይወት የለውም፤ ለሞትም የተወሰነ ነው። መላው እስራኤላውያን ይህንን ዘንግተውታል። ደስ ያላቸው ቀን ተነሥተው አማልክትን ከመንፈሳዊ "ብፌ" መርጠው ማምለክ አይችሉም። እውነተኛውን አምላክ ማመንና በእምነታቸውም መጽናት ነበረባቸው።

የእስራኤል ንጉሥችን ስናይ ችግሩ ይብሳል። የዳዊት ልጆች ዙፋኑን እንደሚወርሱ እግዚአብሔር ለዳዊት ቃል ኪዳንን ገብቶ ነበር፤ ነገር ግን ብዙዎቹ ከእግዚአብሔር ራቁ። እግዚአብሔር ይህንን አለማመንና አለመታመን ዝም ብሎ ማለፍ አይችልም። ተስፋውንም ፍቆ መጣል አይችልም። ያን ቢያደርግ፥ ከመጀመሪያው ሁሉም ነገር  የማይሆን ዕቅድ ነው ብሎ እንደማመን ነው። ሁሉን የሚያውቅ እግዚአብሔር ደግሞ የማይሆን ዕቅድ ሊኖረው አይችልም።

እግዚአብሔርን ለናቁና ከእርሱ ለተለዩ ሕዝቦች፥ እርሱ ተስፋውን እንዴት ሊጠብቅ ይችላል? አዲስ ልብ ያስፈልጋቸዋል። እንዲመራቸው ህልውናው ያስፈልጋቸዋል። የሚያስፈልገው፥ የአብርሃምና የዳዊት ዘር የሆነ የእግዚአብሔርንም መልክ በፍጽምና የሚያንጸባርቅ የመጨረሻው ንጉሥ ነው። ያም ዘር በሰው ዘር ላይ የመጣውን የሞት እርግማን መሻር አለበት። ግን ሰው ብቻ የሆነ

እንዴት ሞትን ማሸነፍ ይችላል? አምላክም መሆን አለበት። ያ ሁሉ እንዴት ይሆናል?

ችግር የለም... ኑ! እንይ።

## ምዕራፍ አራት

## እግዚአብሔር ሰብአዊ ቤተ ሰቡን ተቀላቀለ

ክርስቲያኖች ስለ ኢየሱስ መምጣት ያውቃሉ። ብላቴና ከሆነች ከድንግል ማርያም በተዓምር እንደ ተወለደ ያውቃሉ (ማቴ 1፥18–25)። በገና በዓል ከሚደረገው ግርግር የተነሣም፥ በግርግም የተኛውን የሕጻኑን ኢየሱስ ምስል አብላጫው ባሕል ያውቀዋል። ረጅም ዓመታትን ያስቆጠሩ፥ ነገር ግን አሁንም የሚዘመሩ የልደት በዓል መዝሙሮች፥ ስለመሲሁ በብሉይ የተነገሩትን ትንቢቶች ኢየሱስ እንደፈጸመ ያበስራሉ።

*ስለ ኢየሱስ ከመስቀሉ ያለፈ ብዙ ነገር አለ*

አብዛኛው አትኩሮት የሚያጠነጥነው፥ ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣው በመስቀል ሊሞት እንደሆነ ነው። እርሱ የኅጢአታችንን ሥርኤት በማስገኘት ወደ እግዚአብሔር ቤተ ሰብ የምንቀላቀልበትም መንገድም ነው (ዮሐ 3፥16)። በሌላ አባባል፥ ብዙ ክርስቲያኖች ስለ ኢየሱስ ሲያስቡ፥ መስቀሉ ላይ አትኩሮት ሰጥተው ነው። ያ የሚቀረው ነገር አለ።

አትኩሮታችን መስቀሉ ላይ ብቻ ካደረግን እግዚአብሔር በኢየሱስ ሰው የመሆኑን እውነት በተወሰነ መንገድ እናጣዋለን። ብዙ ክርስቲያኖች የአምላክ ሰው መሆንን ያስፈለገበትን ሌሎች ምክንያቶች አይረዱም። የብሉይ ኪዳን ቃል ኪዳኖችን ለመፈጸምና አስቀድመን የተነጋገርናቸውን የልዕለ ተፈጥሮአዊ ዐመፅ ጠንቆችን ለመቀልበስ አምላክ ሰው መሆን ነበረበት።

ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም ለመኖር የነበራቸው ተስፋ ሕያው ሆኖ የተጠበቀው፥ እግዚአብሔር ሰውን ለማጥፋትም ሆነ ዕቅዱን ለመተው ባለመፈለጉ ነው። እግዚአብሔር ለሰዎች ይቅርታን እያደረገ ከእርሱ ጋር ሕብረት እንዲያደርጉ እየጠራ በተደጋጋሚ ወደ እነርሱ ይመጣ ነበር። ሰዎች እርሱን እንዲያምኑ፥ እምነታቸውንም ከእርሱ ጋር በመስማማትና እርስ በርሳቸውም በሰላም በመኖር እንዲያሳዩ ይፈልግ ነበር። ልጆቹ ግን በየጊዜው ናቁት። እግዚአብሔር “ከእኔ ጋር አሁንም መሆን ትችላላችሁ—አምናችሁ ልባችሁ ምን ላይ እንዳለ አሳዩኝ” ባለ ቁጥር ችግሩ ይበልጥ አየባሰ ሄደ። የችግሩን ጥልቀት ለማሳየት፥ መጽሐፍ ቅዱስ እረኛ የሌላቸውን የተቅበዝባዥ በጎችን ምሳሌ ይጠቀማል (ኢሳ 53፥6፤ ማቴ 9፥36)። ያ ዓላማውን የመታ ምሳሌ ነው።

ባለፈው ምዕራፍ መጨረሻ ላይ እንዳሰፈርኩት፥ የእግዚአብሔር ልጆች ያምኑ ዘንድ የሚረዳቸው አዲስ ልብና የሚመራቸው የእግዚአብሔር ህልውና

ያስፈልጋቸው ነበር። ሰዎች በመጨረሻ ከሚወዳቸው እግዚአብሔር ጋር ለዘላለም እንዳይኖሩ ከሚያደርጋቸውና ከራሳቸው የሚያድናቸው መንገድ ያስፈልጋቸው ነበር። እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን እንዲያከብር፥ የሞትንም እርግማን እንዲሽርና ልጆቹንም በእምነታቸው እንዲጸኑ የሚያደርግ መንገድን እግዚብሔር ማግኘት ነበረበት።

እግዚአብሔር ለእነዚህ ችግሮች ያቀረበው መፍትሔ ሥር ነቀል ነበር። *ሰው መሆን* ነበረበት። የሰውን ዘር ተቀላቀለ። *ኢየሱስ በታሪክ ውስጥ የሚመጣው እዚህ ጋ ነው*። ኢየሱስ አምላክ ሰው ነው (ዮሐ 1፥1፡ 14–15፤ ቆላ 1፥15–20፡ 2፥6–9)። ኢየሱስ ለእነዚህ መሰናክሎች ሁሉ መልስ ነበር።

በሰዎች ላይ የነበረው የሞት እርግማን የሚቀለበሰው ለሰው ልጆች በምትካቸው የሚሞት ሲገኝ ነው። ከእንዲህ አይነትም ሞት ባኋላም፥ እግዚአብሔር ብቻ ሊያደርግ የሚችለው ትንሣኤ መከተል ነበረበት። *ኢየሱስ በዔድን ለሆነው ጉዳይ መፍትሔ ነበር።*

እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ታስታውሳላችሁ? እግዚአብሔር ለአብርሃምና ሣራ በተአምራት ወንድ ልጅ ሰጥቶአቸዋል። *ያ* የሀገረ እስራኤል ጅማሬ ነበር። እግዚአብሔር ለአብርሃም ከዘሮቹ አንዱ በባቢሎን ለተተዉት የምድር ነገዶች በረከት እንደሚሆን ነገሮታል። ሰው ብቻ የሆነ እንዴት ይህን ሊያደርግ ይችላል? ለአብርሃም የተገባውን ተስፋ በመፈጸም፥ ከእስራኤል ውጭ ያሉትን የምድር ነገዶች መባረክ የሚችለው ታማኙ የአብርሃምን ዘር እግዚአብሔር ራሱ መሆን አለበት። *ያ የአብርሃም ዘር ኢየሱስ ነበር (ማቴ* 1፥1፤ ሉቃ 3፥34)። እግዚአብሔር በተዋቸው ሀገሮች የሚኖሩትን አሕዛብ፥ ከሌሎች አማልክት ነጻ የሚያወጣውና ከእግዚአብሔር ቤተ ሰብም ጋር የሚቀላቅላቸው ተስፋ የተገባለት ዘር እርሱ ነበር (ገላ 3፥16–18፤ 26–29)። *ለአብርሃም የተገባው ቃል ኪዳን እንዲፈጸም መፍትሔው ኢየሱስ ነበር።*

ኢየሱስ የዳዊት ዘር ስለሆነ ንግሥና የተገባው ነበር (ማቴ 1፥1፤ ሉቃ 1፥32፤ ሮሜ 1፥3)። *ለዳዊት የተገባው ቃል ኪዳን እንዲፈጸም መፍትሔው ኢየሱስ ነበር።* ኢየሱስ ትክክለኛው ዘርና ለእግዚአብሔርም ፍጹም ታማኝነት ነበረው። በእግዚአብሔር ላይ ዐምጾ አያውቅም። ኀጢአትም አድርጎ አያውቅም (2 ቆሮ 5፥21፤ ዕብ 4፥15፤ 1 ጴጥ 2፥22)። ኢየሱስ ኀጢአት አድርጎ ስለማያውቅ፥ ለእግዚአብሔር ሕግ ዓላማና በሲና ለተገባው ቃል ኪዳን ፍጻሜ እንከን የለሽ ምሳሌ ነው። ኢየሱስ፥ የመጨረሻው የእግዚአብሔር መልክ ነጸብራቅ ነው (2 ቆሮ 4፥3፤ ቆላ 1፥15)። እርሱ የእግዚአብሔርን መልክ እንዴት ማሳየት እንዳለብን ማመላከቻ ነው፤ እግዚአብሔር የኢየሱስን ምሳሌ እንድንከተል ይፈልጋል (2 ቆሮ

3፥18፤ ቆላ 3፥10)። በኋላ እንደምንመለከተው፥ ደቀ መዝሙር የመሆን ትርጉሙም ይህ ነው (1 ጴጥ 2፥21)።

የእግዚአብሔር ሰው መሆንን መረዳት አስቸጋሪ ሐሳብ ነው። እግዚአብሔር ሰው መሆን የቻለው ከአንድ በላይ የሆነ አካል ስለሆነ ነው። እግዚአብሔር ሥሉስ ነገር ግን በመለኮት አንድ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ "አብ"፥ "ወልድ" እና "መንፈስ ቅዱስ" የሚሉትን ቃላት ሦስቱን አካላት ለመለየት ይጠቀማል። ይህንኑ ሐሳብ ክርስቲያኖች ሥላሴ ብለው ይጠሩታል። "እግዚአብሔር ወልድ" በኢየሱስ ሰው ሆነ (ዮሐ 1፥1፣14—15)። የእግዚአብሔርን "ሥጋ ሆኖ" መምጣት፥ የነገረ መለኮት አጥኚዎች ትሥጉት ይሉታል። ቃል ኪዳኖቹን ሁሉ ሊፈጽም የሚችል አብም ሊታመንበት የሚቻለው አምላክ—ሰው ኢየሱስ ብቻ ነው።

እግዚአብሔር "ዓለም ሳይፈጠር" ልጁን ኢየሱስን ልኮ ሕዝቡን ወደ እርሱ ቤተ ሰብ እንደሚያመጣ አስቀድሞ እንደሚያውቅ መግለጼን ታስታውሱ ይሆናል (ኤፌ1፥1—14፤ 1ጴጥ 1፥20)። እግዚብሔር ምድራዊ ቤተ ስብ ይኖረው ዘንድ ልጁ ሰው ለመሆን፥ ለመሰቃየት እንዲሁም ለመሞት መፍቀዱ ሌላው አስደናቂ ነገር ነው። ይህንን አንድ የአዲስ ኪዳን ክፍል እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፦

> ስለዚህ ወደ ዓለም ሲገባ [ክርስቶስ ለእግዚአብሔር]፦መሥዋዕትንና መባን አልወደድህም ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ...እነሆ፥ በመጽሐፍ ጥቅልል ስለ እኔ እንደ ተጻፈ አምላኬ ሆይ፥ ፈቃድህን ላደርግ መጥቼአለሁ አልሁ ይላል(ዕብ 10፥5፣7)።

እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ሆኖ መምጣቱ መልካም ነገር ነው። ቃል ኪዳኖቹ ብቻ ሳይሆን፥ በመለኮታዊ ዐመፆች የተፈጠሩትን መከራዎች ማሸነፍ በአደጋ ላይ ወድቆ ነበር። ዐመፆቹ የእግዚአብሔርን ሰው መሆን ግድ እንደሚሉ መረዳት ይገባናል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ቤተ ሰቡን መቀላቀሉ ለመንፈስ ቅዱስ መምጣት ወሳኝ ዝግጅት ነበር።

*ከውድቀት የላቀ መፍትሔ*

እግዚአብሔር በኢየሱስ ሰው በመሆኑ፥ ሊሞት ይችላል። ይህ አስፈላጊ ነው፥ ሞት ድል የሚነሣው በትንሣኤ ነውና። አስቀድሞ ሞት ከሌለ ትንሣኤን ማግኘት አይቻልም። ኢየሱስ አምላክም ስለሆነ ሕይወቱን መልሶ የማንሣት ኀይል ነበረው (ዮሐ 10፥17—18)። የኢየሱስ ሞት የእግዚአብሔር ዕቅድ ስለነበረ፥ እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሙታን መካከል እንደሚያስነሣው ዓለም ከመፈጠሩ በፊት አስቀድሞ ያውቅ ነበር (ሐዋ 2፥23—24፣ 32፤ 3፥25፤ 10፥40፤ ገላ 1፥1)።

በትንሣኤው ምክንያት፥ በእኛና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው ርቀት ተሰበረ። ሞት ድል ተነሣ። እነዚህ በዔድን የነበረው ዐመፅ ውጤቶች ነበሩ። በእባቡ (በሰይጣን) ፈተና ተከስተው የነበሩት የአዳምና የሔዋን ችግሮች መልስ አገኙ። በኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ የሚያምኑ ሁሉ፥ ይቅርታንና የዘላለምን ሕይወት በማግኘት በእግዚአብሔር ቤተ ሰብ ውስጥ ለዘላለም ይኖራሉ (ሮሜ 4፥16–25፤ 8፥10–11፤ 10፥9–10፤ 1 ቆሮ 6፥14)።

ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ወደ ሰማይ መመለስ ወይም ማረግ ነበረበት። ኢየሱስ ወደ ሰማይ ዐርጐ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ በዙፋኑ ተቀመጠ (ማር 16፥ 19፤ ዮሐ 20፥17፤ ቆላ 3፥1፤ ዕብ 12፥2)። ይህ በአማኞች ሁሉ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ከመላኩ በፊት ቀድሞ ሊሆን የተገባው ነበር (ሐዋ 2፥33፤ ሮሜ 8፥9–11)። መንፈስ ቅዱስ ይመጣ ዘንድ ኢየሱስ መሄድ ነበረበት (ዮሐ 14፥ 25–26፤15፥26፤ 16፥7፤ ሉቃ 24፥49)።

የመንፈስ ቅዱስ መምጣት በኤርምያስና በሕዝቅኤል የተነገረው የአዲስ ኪዳን ትንቢት ፍጻሜ ነበር (ኤር 31፥31–34፤ ሕዝ 36፥22–28)። በብልሹነት ላይ ድል ለመንሣት ኀይልን የሚሰጠውና (ገላ 5፥16–17) ኢየሱስ ከሠራቸው ሥራዎች “የሚበልጥ” የሚያደርገው መንፈስ ቅዱስ ነው (ዮሐ 14፥12)። ኢየሱስም ሞቱና ትንሣኤው ለአዲስ ኪዳን ፍጻሜ ቁልፍ እንደሆነ ያውቅ ነበር። በመጨረሻው እራት ላይ፥ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ደሙ ለእነርሱ የሚፈስ “የአዲስ ኪዳን ደም” እንደሆነ የተናገረበት ምክንያት ይህ ነው (ማቴ 26፥28፤ ማር 14፥14፤ ሉቃ 22፥20)። ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከሄደና መንፈስ ቅዱስም ወደ ምድር ከመጣ በኋላ የሰው ልጅ ብልሹነትን በተመለከተ ረዳት የለሽ አይደለም።

ዋናው ነጥብ፥ እግዚአብሔር ከምድራዊ ቤተ ሰቡ ጋር የመጣውን ችግር– የተለመደው ውድቀትና ዐመፅ– ለማስወገድ ራሱ ሰው ሆኖ ቃል ኪዳኑን መፈጸም ነበረበት።

በዚህ መጽሐፍ መጀመሪያ የጠየቅኩትን ጥያቄ አስቡ፦ እግዚአብሔር ምን ይሻል? *አንተን /አንቺን/ እናንተን ይሻል።* በቤቱ ለዘላለም ከእርሱ ጋር *እንድንኖር*፥ አንድያ ልጁን የሞትንና የኀጢአትን ችግር ይፈታና ከሰው ጋር ያለውን ቃል ኪዳን ይጠብቅ ዘንድ ወደ ምድር ላከው። እግዚአብሔር ምድራዊ ቤተ ሰቡን ተቀላቀለ። ሌላ መንገድ አልነበረም። ወንጌል ከእኛ ባሕርይ ማለትም ድነትንና የእግዚአብሔርን ፍቅር ለመግዛት ከምናደርገው ጥረት ጋር የተያያዘ እንዳልሆነ የሚያሳዩ ብዙ ምክንያቶች አሉ። ይህ ከሁሉ የሚበልጠው ነው። ፍጽምና የጐደለው ባሕርያችን በቂ ነው በሎ ማሰብ ዕብደት ነው። ድነታችን በጥረታችን ቢሆን ኖሮ የክርስቶስ መምጣት፥ መሞትና ትንሣኤው አስፈላጊ ባልሆነ ነበር።

*ሰይጣንና ጀሌዎቹ፡-ቂሎችና ጅላጅሎች?*

ታሪኩን በተመለከተ እንድትዘነጉት የማልፈልገው አንድ ጠምዛዛ ጉዳይ አለ። ይህንን ጠርጥራችሁ ይሆናል። እኔ ከአንድ ጊዜ በላይ እንደ ጠይቅኩ አውቃለሁ። የኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ እባቡ (ሰይጣን) ያመጣውን ከገለበጠ፥ ዓለምን ሁሉ የሞላውን ክፉት ካገደና የአማጽያኑን የአሕዛብ አማልክት ሥልጣን ከሻረ፥ *ሰይጣንና ክፉ መናፍስቱ ኢየሱስን ለመግደል ለምን ፈለጉ?* ይህ ግልፐ ድንቁርና ይመስላል።

እስቲ አስቡት። የኢየሱስ ሞት በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ለሁሉም ነገር ቁልፍ ነው፤ ምክንያቱም ሞትን የሚያሸንፍ ትንሣኤ እንዲኖር ሞት የግድ መኖር አለበት። ተልዕኮውም ካልተፈጸመ ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር አብ መሄድ አይችልም፤ ይህን ስንል ብክለትን የሚያሸንፈው መንፈስ ቅዱስ መምጣት አይችልም ማለታችን ነው። ሰይጣንና የጨለማው ኀይላት ኢየሱስን ትተውት ቢሆን ኖሮ፥ *የእግዚአብሔር ዕቅድ አይፈጸምም ነበር።* መለኮታዊ ቂሎች ናቸውን?

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ብዙ ጽፌያለሁ። እጅግ የሚማርክ ጉዳይ ነው። ይህን ጥያቄም አዲስ ኪዳን መልሶታል። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለሰበከው የኢየሱስ የምስራች "ወንጌል" ሲናገር፡-

> ነገር ግን እግዚአብሔር አስቀድሞ ከዘመናት በፊት ለክብራችን የወሰነውን፥ ተሰውሮም የነበረውን የእግዚአብሔርን ጥበብ በምሥጢር እንናገራለን። ከዚችም ዓለም ገዞች አንዱ እንኳ ይህን ጥበብ አላወቀም፤ አውቀውስ ቢሆኑ የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር (1ቆሮ 2፥7–8)፤

"ገዞች" የሚለውን ቃል ጳውሎስ በሌላ ሥፍራ ክፉዎች የሆኑትን የመንፈሳዊ ዓለም አባላትን ለመግለጽ ተጠቅሞበታል (ኤፌ 3፥10፤ 6፥12፤ ቆላ 1፥16)። ጉዳዩ ግልጽ ነው። ሰይጣን፥ *አጋንንትና ጠላት የሆኑት የእግዚአብሔር ልጆች የእግዚአብሔርን ዕቅድ አያውቁም ነበር።* ኢየሱስ አገልግሎቱን የጀመረ ጊዜ ማን እንደሆነ በእርግጥ ያውቁ ነበር። ኢየሱስን "የእግዚአብሔር ልጅ"ና "የእግዚአብሔር ቅዱሱ" በማለት ጠርተውታል (ማቴ 4፥1–11፤ 8፥29፤ ማር 1፥12–13፡ 21–24፤ 3፥11፤ ሉቃ 4፥1–13፡ 31–37፤ 8፥28)። እግዚአብሔር፥ ልክ በዔድን እንደነበረው የመጀመሪያ ዕቅዱ፥ ምድራዊ ቤተ ሰቡ ከእርሱ ጋር እንዲገዛ እንደሚፈልግ ብሉይ ኪዳን በግልጽ አስቀምጦልናል። ሰይጣንና ጀሌዎቹ ኢየሱስ ይህንን ለማድረግ እንደመጣ መገመት ይችላሉ። *እንዴት ለሚለው ግን መልስ አልነበራቸውም።* እንደ አስተሳሰባቸው፥ እሱን

መግደል ተገቢ ነው። ያ ግን ለሁሉም ነገር ቁልፉ ነበር። እግዚአብሔር አሞኛቸው።

እግዚአብሔር ከልእለ ተፈጥሮአዊ ጠላቶቹ መጠበቡ ፈገግ ማሰኘቱ አይቀሬ ነው። ግን፥ ዋናውን ጉዳይ አንሳት። እግዚብሔር ምድራዊ ቤተ ሰቡን የተቀላቀለው ሰይጣንንም ሆነ አጋንንትን ሞኝ ለማስመሰል አይደለም። ይህን ያደረገው፥ እኛ ቤተ ሰቡ ውስጥ እንድንገኝለት ነው። ሌላ መነሻ አሳብ አላስፈለገውም። እናንተ በቂ ምክንያቶች ናችሁ።

ታሪኩ ገና ብዙ የሚቀሩት ጉዳዮች አሉት። ኢየሱስ የራሱን ድርሻ ተውጥቷል። የመንፈስ ቅዱስን ሚና ግን ቀላል ግን ወሳኝ ለሆነ ምክንያት ቀረብ ብለን ማየት ግድ ይለናል፤ ይህ እግዚአብሔር የተቻለውን ያህል ብዙ ሰዎችን ወደ ቤተ ሰቡ በማምጣት ሂደት ውስጥ ካለን ኅላፊነት ጋር በቀጥታ የተያያዘ ጉዳይ ነው።

## ምዕራፍ 5

## እግዚአብሔር ቤተ ሰቡን ተከታተለ

ቀደም ብሎ ባለው ምዕራፍ እንደገለጽኩት፥ የመንፈስ ቅዱስ መምጣት በኤርሚያስና በሕዝቅኤል የተነገረው የአዲስ ኪዳን ትንቢት ፍጻሜ ነው (ኤር 31፥31–34፤ ሕዝ 36፥22–28)። በአማኙ ሕይወት ውስጥ ያለው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት በብክለት ላይ ድልን መስጠት ነው። ይህ የወደቁትን የእግዚአብሔር ልጆች በጥፊ የማለት ያህል ነው። በተጨማሪም፥ በሌሎች መለኮታዊ ጠላቶች ላይ ቀጥተኛ ጥቃትን እንደማሳረፍ ነው።

የመንፈስ ቅዱስ መምጣት በእግዚአብሔር የተፈቱትን ሐገራት በሚያስተዳድሩት በእግዚአብሔር ልጆች ላይ የሰርጎ ገብ ዘመቻን የማካሄድ ያህል ነው (ዘዳ 32፥8)፤ እነዚህ ልጆችም እግዚአብሔርን ከማገልገል ፈቀቅ ያሉ፥ በሥልጣናቸው ሥር የነበሩ ሕዝቦችን የበደሉ መለኮታዊ (ልዕለ ሰብ) ፍጡሮች ናቸው (መዝ 82)።

ያን ሁሉ ኢየሱስ ያውቃል። ከትንሣኤ በኋላ በተጻፉ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት (ለምሳሌ፡- በሐዋርያት ሥራና በራዕይ መጽሐፍ) ንባቦቻችን ላይ ብዙ ጊዜ የማናስተውለው ይህንኑ ጉዳይ ነው።

### *የመጨረሻው መጀመሪያ*

የኢየሱስ መሄድ የመንፈስ ቅዱስን መምጣት እውን አድርጎታል (ዮሐ 14፥26፤ 15፥26፤ 16፥7፤ ሉቃ 24፥49)። ኢየሱስ ከሞት ተነሥቶ በምድር በነበረ ወቅት ለተከታዮቹ በቅርብ ስለሚሆነው ጉዳይ እንዲህ ብሎ ነበር፡-

> ከእነርሱም ጋር አብሮ ሳለ ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ አዘዛቸው፥ ነገር ግን፡-ከእኔ የሰማችሁትን አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል ጠብቁ፤ ዮሐንስ በውኃ አጥምቆ ነበርና፥ እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ አለ... ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ (ሐዋ 1፥4–5፥8)።

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን ማንበበ ከቀጠላችሁ፥ ኢየሱስ ስለምን እየተናገረ እንደሆነ ለማወቅ ጊዜ አይፈጅባችሁም። ኢየሱስ ከሄደ በኋላ (ሐዋ 1፥9–11) መንፈስ ቅዱስ በሚቀጥለው ምዕራፍ በሸበረቀ ክብር ይመጣል።

> በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፥ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ፥ ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፥ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው። እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው፤ በያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው። በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር (ሐዋ 2፥1–4)።

መንፈስ ቅዱስም የኢየሱስን ተከታዮች በተለያዩ ቋንቋዎች መናገር እንዳስቻላቸው የቀረው ትረካ ይነግረናል። ከዓለም ሁሉ ለተሰበሰቡት አይሁድ፥ የኢየሱስን ታሪክ ማለትም ሞቱንና ትንሣኤውን ይናገሩ ነበር። "አይሁድ" በብሉይ ኪዳን ዘመን ከምርኮ የተነሣ በዓለም ላይ ለተበተኑትና በባዕድ ምድር ለሚኖሩት እስራኤላውያን የተሰጠ ስም ነው። የኢየሱስን ተከታዮች ስብከት በገዛ ቋንቋቸው ሲነገር የሰሙት አይሁድ የብሉይ ኪዳን እስራኤላውያን ዘር ነበሩ። በቀደመው የእስራኤል ሐይማኖታዊ የጊዜ ሰሌዳ የሚከበረውን ቅዱስ በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም የመጡ ነበሩ።

የኢየሱስ ተከታዮችን ያውቁ የነበሩ የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ግን ሕዝቡ ሁሉ በመጠጥ ብዛት የሰከሩ መሰላቸው። እነዚህ ሁሉ በድንገት በተለያየ ቋንቋ መናገራቸው የሚቻል ነገር አይደለም። ነገር ግን ሐዋርያው ጴጥሮስ ጉዳዩን በተመለከተ ማስረዳት ጀመረ። ለነገሩ፥ በፊታቸው ነገሩን አፍረጠረጠው ብንል ይቀላል፦

> "አይሁድ በኢየሩሳሌምም የምትኖሩ ሁላችሁ፥ ይህ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን፥ ቃሎቼንም አድምጡ። ለእናንተ እንደ መሰላችሁ እነዚህ የሰከሩ አይደሉም፥ ከቀኑ ሦስተኛ ሰዓት ነውና፤ ነገር ግን ይህ በነቢዩ በኢዩኤል የተባለው ነው። እግዚአብሔር ይላል። በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፤ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፥ ጎበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ፥ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልም ያልማሉ፤ ደግሞም በዚያች ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎቼ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ ትንቢትም ይናገራሉ። ድንቆችን በላይ በሰማይ፥ ምልክቶችንም በታች በምድር እሰጣለሁ... የጌታን ስም የሚጠራም ሁሉ ይድናል። የእስራኤል ሰዎች ሆይ፥ ይህን ቃል ስሙ፤ ራሳችሁ እንደምታውቁ፥ የናዝሬቱ ኢየሱስ እግዚአብሔር በመካከላችሁ በእርሱ በኩል ባደረገው ተአምራትና በድንቆች በምልክቶችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰው ነበረ፤ እርሱንም በእግዚአብሔር በተወሰነው አሳቡና በቀደመው እውቀቱ ተሰጥቶ በዓመፀኞች እጅ ሰቅላችሁ ገደላችሁት። እግዚአብሔር ግን

የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሣው፥ ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለምና... ስለዚህ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ብሎና የመንፈስ ቅዱስን የተስፋ ቃል ከአብ ተቀብሎ ይህን እናንተ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙትን አፈሰሰው” (ሐዋ 2፥14–19፣ 21–24፣ 33)።

ጴጥሮስ እየነገራቸው ያለው፥ በገዛ ዐይናቸው የሚያዩትና በጆሮአቸው የሚሰሙት ክስተት፥ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መምጣት የተከናወነ ተዓምር እንደሆነ ነው። የሆነውን ሁሉ እንዲነግራቸው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን እንደ ላከ ጴጥሮስ ይናገር ነበር። መሲሁ መጥቷል፥ ተገድሏል፥ ከሙታንም ተነስቷል– እነርሱም ይህንን ሊያምኑ ይገባል። የጴጥሮስም ስብከት ውጤት አስገራሚ ነበር። ሦስት ሺህ ሰዎችም ለኃጢአት ይቅርታ “የጌታን ስም በመጥራት” ዳኑ (ሐዋ 2፥ 41)።

ይኼ በዚህ ታሪክ ውስጥ ሰባኪ ደግሞ ደጋግሞ ስለመስቀል የሚያወሳበት ነጥብ ነው። መስቀሉና ትንሳኤው ወደዚህ ስፍራ ስለሚመሩን ይህን ማሰብ ጥሩና መልካም ይሆናል፤ነገር ግን፣ እጅግ አስፈላጊ የሆነውን የታሪኩን ክፍል እናጣዋለን።

*ልዕለ ተፍጥሯዊ ሰርጎ ገብነት*

ሐዋ 2 ላይ የተከናወነው የመንፈስ ቅዱስ መምጣት መሆኑን አስተውሉ። የመንፈስ መምጣት የአዲስ ኪዳን ማለትም ለሰው ልጆች ከእግዚአብሔር የተሰጠው ቁልፍ የአዲስ ተስፋ ሥርዓት አካል ነው። ብዙ ክርስቲያኖች ይኼ ማለት እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን ባልተቀበሉ አይሁዶች ላይ ብቻ ሳይሆን በባቢሎን ግንብ ዘመን እግዚአብሔርን የናቃቸው አሕዛብን  ጭምር ለመዋጀት መንፈሳዊ ጦርነትን ማወጅ እንደሆነ አያስተውሉም። *እግዚአብሔር ቤተሰቡን በመፈለግ ላይ ነው፤* ልጆቹ ያሉበት ስፍራ አያሳስበውም። ይፈልጋቸዋል፥ ያገኛቸውማል።

በሐዋ 2 ያየነው መንፈስ በነፋስና እሳት መልክ ስለመምጣቱ ነው (ሐዋ 2፥2-3)። በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕልውና በተገኘባቸው ራዕዮች ውስጥ እሳትና ጭስ የተለመዱ ነገሮች ናቸው (ዘፀ 13፥ 21- 22፤ ሕዝ 1፥4፣ 13፣ 27)። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር በአውሎ ነፋስም መልክ መጥቶ ያውቃል (ኢሳ 6፥ 4፣ 6፤ ሕዝ 1፥4፤ ኢዮብ 38፥1፤ 40፤6)። የመንፈስን መምጣት በገዛ ዓይኖቻቸው የተመለከቱና ጴጥሮስን ያደመጡ አይሁዶች የድነት ቀን ስለመምጣቱ ያውቃሉ።

በክስተቱ ምን እንደተከናወነ አስቡ፤ ዘሮቻቸው ተበታትነው በነበሩባቸው ሀገራት ይኖሩ የነበሩ ሶስት ሺህ አይሁዳውያን ሃይማታዊ በኣል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም

መጥተው ነበር። የመንፈስ መምጣት ምስክር ሆኑ፤ ስለ መሲሁ ኢየሱስና ስላደረገው ነገር ሰሙ። በክርስቶስ አመኑ፤ ተከታዮቹም ሆኑ። በቀጣይ ምን የሚያደርጉ ይመስላችኋል?

ወደ ቤቶቻቸው ተመለሱ።

ይኼ ምን ይፈይዳል? ፋይዳውማ ተፈትተውና ጠፍተው የነበሩ ሐገራት ሶስት ሺህ ወንጌላውያን ተተክሎባቸዋል። በሌሎች አማልክቶች ተገዝተው ወዳሉ አስቸጋሪ ሐገራት እንደ ምስጢር መልዕክተኞች ሰርገው ገቡ። እግዚአብሔር የራሱን ሰብዓዊ ቤተ ሰብ የሚያበዛበት ጅማሮ ቡቃያ ሆኑ። የመጀመሪያው ማዕበል ናቸው። ተልዕኳቸው ምን ነበር? ግልጽ ነው። ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የሰጠው ታላቁ ተልዕኮ ነበር። ክርስቲያኖች ምንባቡን በሚገባ ያውቁታል፡-

> እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋቹንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋው ደቀመዝሙርት አድርጓቸው። እነሆ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ (ማቴ 28፥19-20)።

ግን አሁንም ይህ ታላቁ ተልዕኮ ልክ ቢሆንም፤ የጎደለ ነገር አለው። ቁ. 18ን ዘልየዋለሁ። በርግጥ እኔ ብቻ ሳልሆን አብዛኞቹ ሰዎች ስለ ወንጌል ተልዕኮ ሲያወሩ ይዘሉታል። አጉልተን ማየት ያለብን በደማቅ የተጻፈውን ሙሉውን የኢየሱስ ንግግር ነው፡-

> ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናራቸው፡- **ስልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ።** እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋቹንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋው ደቀመዝሙርት አድርጓቸው። እነሆ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ (ማቴ 28፥18-20)።

አገኛችሁት? ኢየሱስ በሰማይም ሆነ *በምድር* ስልጣን ተሰጥቶታል። ከሰማይ አንፃር ያለው ስልጣን ለመረዳት እጅጉን ቀላል ነው። ኢየሱስ ወደላይ ካረገ በኋላ በአብ ቀኝ ተቀመጠ (ቆላ 3፥1፤ ዕብ 12፥2)። ከምድር አንጻር ያለው ስልጣንስ? ይኼ በቀላሉ የምንረሳው ነው። ከትንሳኤው በኋላ የተካናወነው ዕርገቱ እስከዛ ሰዓት ድረስ በምድር ላይ ስልጣን የነበራቸውን ኃይላት ስልጣናቸው ማብቃቱን አረጋግጧል። እነዛ እነማን ናቸው? እነዚህ እግዚአብሔር በፈታቸው ሐገራት ላይ የተሸሙት የወደቁ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው (ዘዳ 32፥8)።

*እዚህ ምንም ስራ የላችሁም!*

የክርስቶስ ትንሣኤና ወደ አብ ማረግ አመጸኞቹ የእግዚአብሔር ልጆች ስልጣን ባዶና ከንቱ መሆኑን ያመለክታል። ከዚህ በኋላ በገዟቸው ሰዎችና ሕዝቦች ላይ ሕጋዊ የሆነ የገዢነት ስልጣን የላቸውም። መሲሁ ከአብርሃምና ዳዊት ዘር ቢሆንም፤ ድነት ለአይሁድ ብቻ አይደለም። ኢየሱስ የሁሉም ሰው መሲህና የሕዝቦች ሁሉ ጌታ ነው። ትንሣኤው፣ ዕርገቱና የመንፈስ ቅዱስ መምጣት የወደቁ የእግዚአብሔር ልጆች ፍጻሜ ጅማሮ ነው። ሕጋዊነታቸውን አጥተዋል።

ለዚህ ነው አዲስ ኪዳን የክርስቶስን ትንሳኤና ዕርገቱን ከልዕለ ተፈጥሮአዊ የጨለማ ኃይላት ሽንፈት ጋር የሚያቆራኘው። እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሙታን ስያስነሳው (ቆላ 2፥12) ያገኘነው የኃጢአት ይቅርታ ብቻ ሳይሆን (ቆላ 2፥13-14) "ኃይላትና ስልጣናትነን ገፎ ድል በመንሳት በእርሱ እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው" (ቆላ 2፣15) እንጂ። ጳውሎስ "ኃይላትና ስልጣናት" የሚለውን ቃል በብሉይ ኪዳን የአሕዛብ ገዢ የሆኑ የወደቁ ልዕለ-ኃያል እግዚአብሔር ልጆችን ለመግለጥ መጠቀሙን አስተውሉ (ሮሜ 8፥38፤ 1ቆሮ 15፥24፤ ኤፌ1፥ 21፤ 2፥2፤ 3፥10፤ 6፥12፤ ቆላ 1፥13)።

"ኃይላትና ስልጣናት" የሚለውን ቃል ጳውሎስ የተሸነፉ የጨለማ ኃይላትን ለመግለጽ የሚጠቀምበት ተወዳጅ ቃል ነው። ኢየሱስ ከሙታን ከተነሳ በኋላ "ወደ ሰማይ ወጥቶ በእግዚአብሔር ቀኝ አለ፤መላእክትና ሥልጣናት፥ ኀይላት ተገዝተውለታል" (1ጴጥ 3፥22)። እግዚአብሔር ክርስቶስን ከሙታን ስያስነሳውና በቀኙ ስያስቀምጠው ኢየሱስ "በአሁኑ ዘመን ብቻ ሳይሆን በሚመጣው ዘመን" ጭምር ከአለቆች፣ ኃይላትና ስልጣናት "ሁሉ በላይ" ከፍ ብሎ ተቀምጧል (ኤፌ 1፥20-21)። ኢየሱስ ኃይላት፣ ገዢዎችንና ሥልጣናትን ከደመሰሰ በኋላ በሚመጣው ዘመን "መንግስቱን ለእግዚአብሔር አብ" ያስረክባል (1ቆሮ 15፥ 24)።

ሐዋሪያው ጳውሎስ የክርስቶስን ትንሣኤና ዕርገት አሕዛብ ላይ ገዢ የነበሩ የወደቁ የእግዚአብሔር ልጆች ፍጻሜ መጀመሪያ አድርጎ ያያል። በርግጥ ይኼ አያስገርምም። ደግሞም ይኼንን ሐሳብ ከተተዉት ሐገሮች ሕዝቦች ማለትም ከአሕዛብ ድነት ጋር ያስተሳስራል። ከሙታን የተነሣው ኢየሱስና መንፈስ ቅዱስ አሕዛብን ባሪያ አድርገው በጉልበት ከገዟቸው የጨለማ ኃይላት ነጻ ያወጣሉ (መዝ 82፥2-5)።

እግዚአብሔር ሕዝቦች በባቢሎን ከተበታተኑ በኋላ ለአብርሃም መገለጡን አስታውሱ።ለአብርሃም በእርሱና በዘሩ አማካኝነት እነዚያ ሕዝቦች አንድ ቀን

እንደሚባረኩ ተስፋ ሰጥቶ ነበር። የአሕዛብ ሐዋሪያ የሆነው ጳውሎስ ያንን ተስፋ በሚገባ ያውቅ ነበር። በመሆኑም ነበር "አሕዛብ እግዚአብሔርን ስለ ምሕረቱ ያመሰግኑት" ዘንድ ኢየሱስ ለአብርሃምና ለዘሩ "የተሰጠውን የተስፋ ቃል" አጽኚ መሆኑን የጻፈው (ሮሜ 15፥8-9)።

ጳውሎስ እዚያ ላይ አያበቃም። እግዚአብሔር በአሕዛብ ተስፋ ያለመቁረጡን ለማሳየት ብሉይ ኪዳንን መጥቀስ ይወድ ነበር። እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ ቤተሰቡ ይሆኑ ዘንድ ፍላጎት ነበረው። ጳውሎስ በብሉይ ኪዳን የ "እሴይ ሥር" የተባለው መሲሁ አሕዛብ ተስፋ እንደሚያደርጉበትና እንደሚገዛቸው ያውቅ ነበር (ኢሳ 11፥10)። ደግሞም እነዚህ የተረሱ ሕዝቦች አንድ ቀን እውነተኛውን አምላክ እንደሚያመልኩ ያውቅ ነበር (መዝ 117፥1)።

ይኼ ዕቅድ የመንፈሳዊ ውጊያ ዘመቻ በይፋ የተጀመረው መንፈስ ቅዱስ በወረደበትና ሶስት ሺህ ሰዎች በኢየሱስ ባመኑበት ጊዜ ነው (ሐዋ 2)። እነዚህ አዳዲስ አማኞች ወደየሀገራቸው ተመለሱ። የክርስቶስ ወንጌል በክፉ ልእለ ተፈጥሮአዊ ኀይላት ሥር ወደ ነበሩ ሀገሮች ሰርጎ ገባ። መጽሐፍ ቅዱስ ይኼንን ሂደት "የእግዚአብሔር መንግስት" መስፋፋት ይለዋል። ሰዎች የዘላለም ሕይወት ከማይሰጡት የወደቁና እኩይ አማልክት አገዛዝ ወጥተው የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት ሲሆኑ፣ የእግዚአብሔር መንግስት ያድጋል። አንዱ መንግስት እየጠፋ ሌላኛው ይስፋፋል።

እናም የእግዚአብሔር መንግስት በአንድ መልኩ አሁን እዚህ ያለ ሲሆን፣ … በሌላ መልኩ ደግሞ ሙሉ በሙሉ አሁን አልተገለጠም። እግዚአብሔር የሚወዳቸውን ልጆች ሳፈልግ ያለፈበት ቅንጣት ቅጽበት የለም። ስውር እጆቹ በየስፍራው እና በሁኔታዎች ሁሉ ውስጥ ናቸው። ልጆቹ ቤተሰቡን ያሳድጉ ዘንድ ተፅዕኖ እየፈጠረ በኃይል ያስታጥቃቸዋል። አንድ ቀን የዕቅዱ ፍጻሜ ከጫፍ ይድርሳል። ሁሉም ነገር ሙሉ ክብ ሆኖ ይገጥማል። ታሪኩ ደራሲው ከረጅም ዘመናት በፊት እንዳሰበው ሆኖ ይደመደማል።

## ምዕራፍ ስድስት

## እግዚአብሔር ለዘላለም ከቤተሰቡ ጋር ሆነ

ያለፈውን ምዕራፍ የጨረስኩት ግልጥ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ፍርጥም ያለ አቋም በማስጨበጥ ነበር። ክርስቶስ ተነስቷል። እርሱ በመስቀል ላይ እና በትንሣኤው የፈጸመው ድርጊት ብቸኛ የድነት መንገድ እንደሆነ የሚያምኑ ሁሉ የዘላላም ሕይወት አላቸው። ነገር ግን እኛ ደግሞ *አሁን* የክርስቶስ መንግስት አባላት ብንሆንም (ቆላ 1፡13)፤ መንግስቱ ገና በሙላት አልተገለጠም።

የሰይጣን እና የወደቁ የእግዚአብሔር ልጆች ሽንፈትም እንዲሁ ነው። ነገሩ ሂደት ላይ ነው፤ ግን ገና አልተጠናቀቀም። በእግዚአብሔር መንግስት አባላት ላይ ሰይጣን የባለቤትነት ጥያቄም ሆነ፣ የሞት ኃይል ስልጣን የላቸውም። በክርስቶስ የእግዚአብሔር ሆነናል። እኛ ከእሱና ከእግዚአብሔር ጋር የዘላላም ሕይወት እንዲኖረን ትንሳኤ እናገኝ ዘንድ ኢየሱስ ሞትን ድል ነስቷል (ሮሜ 6፥8-9፤ 8፥11፤ 1ቆሮ 6፥14፤ 15፥ 42-40)። ነገር ግን፥ "በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሰራው መንፈስ አለቃ እንደሆነው በአየር ላይ ሥልጣን" (ኤፌ 2፥2)። ያለው ኀይል አሁንም ይሰራል።

የጨለማ ኃይላት ከዙፋናቸው ወርደዋል፤ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ እጅ አልሰጡም። የተሸነፉትን ጦርነት በተቃውሞ እየተዋጉ ይገኛል። በክርስቶስ ከእግዚአብሔር ድነት የተቀበሉ በሙሉ "ከጨለማ ሥልጣን ... ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግስት ፈልሰዋል" (ቆላ 1፥13)። የእግዚአብሔር መንግስት ባደገ ቁጥር የጨለማው መንግስት እየጠፋ ይሄዳል።

ወደፊት አሻግሮ ከማየት ይልቅ አሁን ባለው እኩይና ስቃይ ውስጥ መስመጥ ቀላል ሊሆን ይችላል። አንዳንዴ ኢየሱስ "ክፉ ከሆነ ከአሁኑ ዓለም ያድነን ዘንድ እንደ አምላካችንና እንደ አባታችን ፈቃድ ራሱን ሰጠ" (ገላ 1፥4) የሚለውን ማስታወስ ከባድ ሊሆን ይችላል።

መጽሐፍ ቅዱስ ይኼንን ማመንታት አይኮንንም። ቃሉ ስለዚህ ጉዳይ በግልጽ "ፍጥረት ሁሉ እስከ አሁን ድረስ አብሮ በመቃተትና በምጥ" "የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃል...ተስፋውም ፍጥረት ራሱ ደግሞ ከጥፋት ባርነት ነፃነት ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር ነፃነት እንዲደርስ ነው" ይላል (ሮሜ 8፥18-21)።

*የታሪኩ ጡዘት*

የተቀረውን የታሪኩን ክፍል በግሩም አጨራረሱ ላይ ማተኮር እሻለሁ። እንደምታውቁት ሁሉም የታሪክ ንግርት የማይረሳ አጨራረስ አለው። የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክም እንዲሁ ነው (ደመናና በገና ከጠበቃችሁ ግን ለመቀየም ተዘጋጁ)። የመጽሐፍ ቅዱስን የመጨረሻ ታሪክ እኛ *አግኝተነዋል* በምንለው ነገር ማሰብ ይቀናናል። ለምሳሌ፡- ሁላችንም ሞት ሳይሆን የዘላለም ሕይወት ይኖረናል። ይኼ የሚያጓጓ ቢሆንም "የዘላለም ሕይወት" ብዙ የሚነገርን ነገር የለም። ጊዜን ከመግለጥ ውጭ ስለ ልቀቱ አይገልጥልንም።

የዘላላም ሕይወት ልቀቱ በአዕምሯችን የበለጠ ጎልቶ የሚከሰተው ሕይወትን በታሪኩ ፍጻሜ ከተገለጠችው ዓለም አቀፏ ዔድን አንጻር ስናስብ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻው መጽሐፍ የሆነው የራዕይ መጽሐፍ ታሪኩን በዔድንአንድምታ ይደመድመዋል (ራዕይ 21-22)። በዚያ እግዚአብሔር አለ። ሰማይ ወደ ምድር ተመልሶ መጥቷናል። በዚያ ኢየሱስ አለ። የሕይወት ዛፍ በዚያ አለ።ይኼኛው ዔድንከመጀመሪያው የተሻለ ነው። እኩይ ሩጫውን ጨርሷል። በዓለም ውስጥ ሊፈነዳ አድብቶ የተቀመጠ እኩይ የለም። ስለዚህ ፍጥረት ወደ ፍፁምነትን ከፍ ብሏል። በእጽዋት፣ በእንስሳት ወይንም በሰው የሕይወት ልምምድ በሽታም ሆነ ሞት የለም። ግድያም ሆነ ጥቃት በዚያ የለም። ተለማምደነው የማናውቀው ፍጹም ሕይወት ነው።

ይህ የ "ዔድን አስተሳሰብ" መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ትኩረት የሚሰጠውን የታሪኩን ጡዘት" ወደ መረዳት ያቀርበናል። ከሮሜ 8 የወጣው ከላይ ያካተትኩት ምንባብ አመለካከታችንን በእግዚአብሔርን ዕቅድ ውስጥ ቁንጮ የሆነውን "የእግዚአብሔር ልጆች መገለጥ ... የእግዚአብሔር ልጆች ክብር" እንዲስተካከል ያደርገዋል። አዎ! ፍጥረት አዲስ ለመሆን ይቃትታል፤ ይሁን እንጂ ይኼ ነፃነት ሰዎች ከሆኑ የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ መክበር ጋር የተሳሰረ ነው፡፡

በሌላ አነጋገር፣ እግዚአብሔር እየሰራ ለኖረው ስራ የመጨረሻው ግቦቹ እኛ ነን። በጎልውናው ውስጥ ለዘላለም ለመኖር መሰራታችንና ከእርሱ ጋር ለዘላለም የሚያኖረን የልጅነት መብታችን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ቀዳሚ እውነታ ነው። የምንኖርበት መኖሪያችን ምንም እንኳ አስደናቂ ቢሆንም ትዕይንቱ የሚካሄድበት ሥፍራ ነው። የራዕይ መጽሐፍ የመጨረሻ ራእይ አዲሲቷን ዔድን በሚከተለው መንገድ በመግለጥ ያሰፈርኩትን ነጥብ ያጐለብትልኛል፡-

> "አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርንም አየሁ፥ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛው ምድር አልፈዋልና፥ ባሕርም ወደፊት የለም። ቅድስቲቱም ከተማ

> አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፥ ለባልዋ እንደተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ፥ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ። ታላቅም ድምፅ ከሰማይ፡- **እነሆ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው፤ ከእነርሱም ጋር ያድራል፥ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ፤ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል"** *ራዕይ* 21፥1-3

*ዘላለማዊ ማንነት*

የ"እግዚአብሔር ልጆች መገለጥ...የእግዚአብሔር ልጆች ክብር" የሚለው እውነት አንድ ቀን ክርስቶስን ወደ መምሰል እንደምንለወጥ ያመለክታል። ሐዋርያው ዮሐንስ "ወዳጆች ሆይ፤ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፣ ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱንም እንድንመስል እናውቃለን" እንዳለው ነው (1 ዮሐ 3፥2)። ይኼው ሐሳብ በተለያየ መንገድ እንደሚከተለው ተገልጿል፡-

> "ልጁ በብዙ ወንድሞች መካካል በኩር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና" (ሮሜ 8፥29)
>
> "እኛ አገራችን በሰማይ ነውና፣ ከዚያ ደግሞ የሚመጣ መድኃኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን፤ እርሱም ሁሉን አንኳ ለራሱ ሊያስገዛ እንደሚችልበት አሰራር ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጠዋል" (ፊል 3፥20-21)

መጨረሻችን የላቀው የእግዚአብሔር አምሳል እንደሆነው ኢየሱስ እግዚአብሔርን ወደ መምሰል በሙላት መለወጥ ነው። አሁን ሂደት ላይ ነን፤ "እኛ ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደመስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን" (2ቆሮ 3፥18)። መጽሐፍ ቅዱስ ታሪካችንን በትንሣኤና በመለወጥ ይደመድመዋል። ኢየሱስ በትንሣኤው ያገኘውን የከበረ አካል ይዘን ለዘላለም ሕይወት እንነሳለን። ጳውሎስ ይኼንን አካል "ሰማያዊ አካል" ይለዋል (1ቆሮ 15፥35-58)።

ፍጻሜያችንና መክበራችንን በተመለከተ ተወዳጁ ጥቅሴ ትንሽ ግልጥ አይደለም። ኢየሱስ እኛን ለእግዚአብሔር፣ እግዚአብሔርን ደግሞ ለእኛ ባስተዋወቀበት የዕብራውያን መጽሐፍ ይገኛል። ኢየሱስ በሰማያዊ የእግዚአብሔር ልጆች "ማህበር"ፊት ቆሟል። በቤተሰቡም ውስጥ "ወንድሞቼ" ብሎ ሲጠራን ፈጽሞ እንደማያፍርብን በድፍረት ያውጃል (ዕብ 2፥ 11)፣ ለእግዚአብሔርና ለልዕለ ኃያላን የቤተሰቡ አባላት "ስምህን ለወንድሞቼ እነግራቸዋለሁ በማኅበርም መካከል

በዜማ አመሰግንሃለሁ...እነሆኝ እኔን እግዚአብሔር የሰጠኝንም ልጆች"(ዕብ 2፥12)ይላቸዋል።

ሕጋዊና ቋሚ የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ አባላት መሆን የመጨረሻው ግባችን ነው። በመጨረሻም የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ *እንሆናለን*። ይኼ እግዚአብሔር ከፍጥረቱ መጀመሪያ እንዲሆን የፈለገው ነው። ፍጥረት በሞላ በናፍቆት እየጠበቀ ያለው ያንኑ ነው።

*ዘላለማዊ አጋርነት*

ሕይወት በአዲሱ ፍጥረት (ሰማይ) ምን እንደሚመስል የሚገልጽ ውይይት አድርጋችሁ ታውቃላችሁ? ከብዙ ሰዎች፣ ፍጻሜ ዐልባ አምልኮ ወይም ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረግ መጨረሻ የሌለው ጥያቄና መልስ ወይም የከበረችው ቤተክርስቲያን ተገናኝታ ሰላምታ የምትለዋወጥበት አድርገው የሚፈገልጹ አያሌ ምሳሌዎችን ሰምቻለሁ። (የመጨረሻው እንደ እኔ ዓይነት ጭምት ለሆኑ ሰዎች አስፈሪ ነው።)

ሕይወት ፍፁም በሆነች ገነት ውስጥ ምን እንደምትመስል የየራሳችንን ምናባዊ ድምዳሜ ብንሰጥም መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚያኛው ዓለም ልምምድ ብዙ አይነግረንም። ቃሉ የሚነግረን እውነታ ከላይ የዘረዘርናቸውን ግምቶች የሚያፈርስ ነው። በኢየሱስ ላይ ባለ እምነታቸው ጸንተው "ድል የነሱ" "በአሕዛብ ላይ ስልጣንን" ያገኛሉ (ራዕይ 2፥26)። ኢየሱስም "ከእኔ ጋር በዙፋኔ " ተቀመጡ ይላቸዋል (ራዕ 3፥ 21)። አንድ ቀን በመላእክት ላይ እንፈርዳለን (1ቆሮ 6፥3)።

እነዚህ ሀረጎች ምን እያሉ ነው? *አሁን* አሕዛብን ማን እየገዛ እንዳለ በመጠየቅ መጀመር እንችላላን። መልሱ በባቢሎን ለተበተኑት አሕዛብ የተሰጡ የወደቁ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው የሚል ነው። በሌላ አነጋገር አሁን እግዚአብሔር አሕዛብን ሙሉ በሙሉ (በአብላጫም ቢሆን) አልገዛም ማለት ነው። ቀደም ብሎ እንዳየነው የእግዚአብሔር መንግስት መስፋፋት ሂደታዊ ነው—*የተጀመረ* ግን ገና ያላለቀ ሂደት። በመጨረሻው ቀናት ሂደቱ ሲጠናቀቅ አማኞች "በመላእክት ላይ ይፈርዳሉ"—የወደቁ የእግዚአብሔር ልጆችን በመተካት እንፈርድባቸዋለን። ከንጉሳችንና ከወንድማችን ከኢየሱስ ጋር በመሆን በአሕዛብ ላይ እንገዛለን።

ዘወትር ይኼንን ሐሳብ ሳወራ "የሥራ ድርሻችን ምንድን ነው?" የሚል አይቀሬ ጥያቄ ይከሰታል። አንዳንድ አማኞች ከሌሎች አማኞች የበለጠ ስልጣን ይኖራቸዋል? የሌላ አማኝ አለቃ እሆናለሁን? ሁላችንም እንዴት ገዢ እንሆናለን? ሥራችን "ማን ከማን በላይ ነው" የሚለውን ይወስናል?

እነዚህ ጥያቄዎች በሙሉ ፍፁም ባልሆነው የወደቀ ዓለም በሚኖሩ ሰዎች የሚጠየቁ ልንረዳቸው የሚገቡ ጥያቄዎች ናቸው። አመለካከታችን በተለማመድነው የወደቀና የተበላሸ ዓለም ተበክሏል። መጽሐፍ ቅዱሳችን ግን የፍፃሜያችንን እውነታ በአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት መልክ አይገልጸውም። የአባትና ልጅ ግንኙነት ነው። የእግዚአብሔር ልጆች የሆንን ከወንድሞቻችን ጋር—ሰዎችም ሆነ መለኮታዊ ከሆኑት— በመሆን ከእርሱ ጋር አብረን እንሰራለን። እንደታቀደልን አብረን የእግዚአብሔርን መልክ እናንጸባርቃለን። እጅጉን የምንናፍቀው ወንድማችን ኢየሱስ ነው። የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑት ሁሉ የመጨረሻው የአብ መልክ አንጸባራቂ በሆነው በኢየሱስ መልክ ተሰርተዋል።

ዋናው ነጥባችን፣ በአዲሱ ገነት አገዛዛችን ቤተ ሰባዊ አጋርነት እንጂ እርከናዊ ያለመሆኑ ነው። ሁሉም የቤተ ሰብ አባል ከከበረ፥ በሌላው ላይ የመሰልጠን እርከናዊ ፍላጎት ይጠፋል።

እንደ እውነቱ ከሆነ እንደዚህ አይነት ነገር ማሰብ አንችልም። የምንኖረው በተበላሸ ዓለም ነው። ከእርሱ ጋር ባቀድው መልኩ ሕይወትን እንድንኖርለት፥ እግዚአብሔር እኛን —አንተን— ፈለገ። አንድ ቀን ይህ ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ እንደሚል፡-

> “ዐይን ያላየውን፣ ጆሮም ያልሰማውን፣ የሰውም ልብ ያላሰበውን፣ እግዚአብሔር ለሚወዱት አዘጋጅቶአል።” (1 ቆሮ 2፥9 አ.መ.ት)

## ማጠቃለያና ቅድመ እይታ

አሁን መጽሐፍ ቅዱስ ስለምን እንደሚያወራ የተረዳችሁ ይመስለኛል። አስገራሚ ታሪክ ነው።

ከዚህ ቀጥሎ ወዴት እንሄዳለን? ብላችሁ እየባተላችሁ ይሆናል። በታሪኩ ብርሃንም መሰረት ማጤን ያለብን አስለፈላጊ አንኳር ጉዳዮች አሉ።

በታሪኩ ጅማሮ ስለ አብርሃም የሚከተለውን ብዬ ነበር፡-

> *ሐዋርያው ጳውሎስ አብርሃምን በእምነት ስላለ ታማኝ አማኝነት ምሳሌ አድርጎታል (ሮሜ 4፥1–12)። የትኛውንም ትእዛዝ ከመፈጸሙ በፊት፥ ከእምነቱ የተነሣ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን አግኝቶ ነበር። ፍሬ ነገሩ እምነቱ ነበር። በእግዚአብሔር ስላለው እምነት–ታማኝነት–በኋላ እንመለስበታለን። ዛሬ ይህንን ደቀ መዝሙርነት እንለዋለን። እምነትና ታማኝነት ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው፤ ግንኙነት ቢኖራቸዋም ተለዋዋጭ ግን አይደሉም። ድነትና ደቀ መዝሙርነትም እንዲሁ ናቸው።*

ይኼ አንቀጽ ለቀረው ጉዟችን ካርታ ይሆናል። *"ታማኝ-አማኝነት"* የሚል ሐረግ ደግሞ የጉዟችን መመሪያ ስለሚሆን እስቲ እናብራራው፡-

***"ማመን"***

በቀጣይ ክፍል ስለወንጌል እናወራለን። ወንጌል ምን እንደሆነና ምን እንዳልሆነ እንመለከታለን። ወንጌል ምን ማለት እንደሆነና ከመጽሐፍ ቅዱስ አንፃር ይዘቱ ምን እንደሆነ እናወራለን። ይህም አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት በወንጌል *ማመን* የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ መሆኛ ዓይነተኛ መንገድ በመሆኑ ነው። የዳንነው በዚህ መልኩ ነው። ድነት የሚገኘው በእምነት ነው። ይኼ እግዚአብሔር ድነትን በመስጠት ወደ ቤተ ሰቡ ለመጨመር የዘረጋው መንገድ ነው። ያ ሁሉ ኢየሱስ በሰራው *ሥራ* ላይ የተመሠረተ ነው።

***"ታማኝነት–ሎሌነት"***

በዚህ መጽሐፍ የመጨረሻ ክፍል ስለ ደቀመዝሙርነት እናወራለን። የደቀመዝሙር ቃል ትርጉም "ተከታይ" ማለት ነው። የኢየሱስ ደቀመዝሙር ማለት ኢየሱስን መከተልና እሱን መምሰል ማለት ነው። ኢየሱስ "እኔን ያየ አብን አይቷል" (ዮሐ 14፥7፣ 9) ብሏል። ኢየሱስ እግዚአብሔርን መውደዱን የሚያሳይ ሕይወት

ኖሯል። በዚያም ለአባቱና ለዕቅዱ ያለውን ታማኝነት አሳየ። ደቀመዝሙርነት ለኢየሱስና ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር ማሳያ ነው። የእግዚአብሔርን ፍቅር መግዣ መንገድ አይደለም። እግዚአብሔር ያቀደውን የድነት ስራ ስለፈጸመልን ኢየሱስን ማመስገኛ መንገድ ነው። ደቀመዝሙርነት ኢየሱስ የፈጸመልን ድነት መተኪያ ወይም በድነቱ የጎደለውን ማሟያ መንገድ አይደለም። ኢየሱስ የፈጸመልንን ድነት ማመናችንን ማሳያ መንገድ እንጂ (ያዕ 2፥14-26)።

ከላይ እንዳልኩት፣ ማመንና ታማኝነት ሁለት ተዛማጅ ግን የተለያዩ ነገሮች ናቸው። አንዱ ሌላውን አይተካም። ድነትና ደቀመዝሙርነትም እንዲሁ ናቸው። ወንጌልን ለድነታችን እናምናለን። ለአዳኛችን ያለንን ታማኝነት ደግሞ የእርሱ ደቀመዝሙር በመሆን እናሳያለን።

# ክፍል ሁለት፡- ወንጌሉ

## ምዕራፍ ሰባት

## ወንጌል ምንድነው?

ይኼንን ጥያቄ በዚህ ስፍራ መጠየቅ ተገቢ አይመስልም። የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ ማለትም እግዚአብሔር የቤተ ሰቡ አባል እንሆን ዘንድ የፈለገበትን ታሪክ በመዳሰስ በዛ ያለ ጊዜ አሳልፈናል። ያንን ቤተ ሰብ በወንጌል በማመን ተቀላቅለናል።

አብዛኞቹ ቤተ ክርስቲያን የሚሄዱ ሰዎች ወንጌሉን በትክክል እንደማይረዱት ለማወቅ ችያለሁ። አንዳንዶች ወንጌል ምን ማለት እንደሆነ በግልጽ ማስረዳት አይችሉም። ሌሎች በተቀናጀ መልኩ ለመግለጽ የሚችሉት ደግሞ ለቀላልነቱ እጅ ላለመስጠት ይታገላሉ። የዘላለም ሕይወት ማግኛ ብቸኛው መስፈርት በወንጌል ማመን እንደሆነ የሚገልጸውን እውነት ለመቀበል በውስጣቸው ይሰቃያሉ፡፡

አንዳንዶቻችሁ ስለምን እያወራሁ እንደሆነ ለማወቅ ጓግታችሁ ይሆናል። ማለት የምፈልገውን ሳብራራው፥ ራሳችሁን ወይም ሌላ የምታውቁትን ሰው በምለው ነገር ውስጥ እንደምታዩት ለመወራረድ ፍቃደኛ ነኝ።

“ወንጌል” የሚለውን ቃል በመተርጎም እንጀምራለን። በየመሃሉም መብራራት እንዳለባቸው የማስባቸውን አንዳንድ ጥያቄዎች እጠይቃለሁ። ወንጌል ምን *እንዳልሆነም* መናገር ተገቢ ነው። ወደዚያ ክፍል ስንደርስ ከላይ ስለገለጽኩት ትግል ምንነት ትረዳላችሁ።

*ወንጌል ምንድነው?*

“ወንጌል” የሚለውን ቃል መተርጎም ቀላል ነው። “ወንጌል” የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የድነት መልዕክትን ያመለክታል። በአማርኛው “ወንጌል” ተብሎ የተተረጎመው ቃል አዲስ ኪዳን በተጻፈበት በግሪክ—መልካም የምስራች ይዞ ለመጣ ሰው የሚሰጥን ሽልማት የሚያመለክት ነው። ከዚህም የተነሣ ወንጌል የሚለው ቃል ስለመዳን ከሚናገር መልካም ዜና ጋር—ከየምስራች— ተያይዞ ትሰሙታላችሁ።

ከላይ ስላነሳነው ጉዳይ እናስብ። አንድ ነገር እንደተማርን ይሰማን ይሆናል። እንደተማርን እገምታለሁ፤ ነገር ግን ማወቅ የሚያስፈልገንን ነገር ያወቅን አይመስለኝም። ቃሉን *መተርጎም* መቻላችን መልካም ነው። ነገር ግን፥ የድነት

መልእክት ይዘቱ ምን እንደሆነ አልተናገርንም። “ወንጌል” የሚለውን ቃል ተረጎምን እንጂ ወንጌል ምን እንደሆነ አልተናገርንም።

ወንጌል ምን እንደሆነ እስቲ እንይ፤ እግዚአብሔር ያቀረበው ድነት ይዘት ምንድን ነው? የመልካም ዜናው ዝርዝር ጉዳዮች ምንድን ናቸው? ለምንስ መልካም ዜና ሊሆን ቻለ? ቃሉ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለ100 ጊዜ የተጠቀሰ በመሆኑ፥ ይህንን ማወቅ አያዳግትም።

ሐዋሪያው ጳውሎስ ከየትኛውም የአዲስ ኪዳን ፀሐፊ በበለጠ ሁኔታ ስለ ወንጌል አውስቷል። ወንጌል የሚለውን ቃል ስለ ኢየሱስ የሚሰብከውን ወንጌል ለማመልከት ይጠቀማል፡-

> ወንድሞቼ ሆይ፡- የሰበክሁላችሁን ደግሞም የተቀበላችሁትን በእርሱም ደግሞ የቆማችሁበትን በእርሱም ደግሞ የምትድኑበትን ወንጌል አሳስባችኋለሁ፤ በከንቱ ካለመናችሁ በቀር ብታስቡት በምን ቃል እንደሰበክሁላችሁ አሳስባችኋለሁ ... መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለኃጢአታችን ሞተ፣ ተቀበረም፤ መጽሐፍ እንደሚል በሦስተኛ ቀን ተነሣ። (1ቆሮ 15፥1-4)

ጳውሎስ በሌላ ስፍራ ደግሞ የሚሰብከውን መልዕክት ማለትም ወንጌልን እንደሚከተለው ይተረጉመዋል፡-

> ሐዋሪያ ሊሆን የተጠራ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ጳውሎስ... ለእግዚአብሔር ወንጌል ተለየ። ይህም ወንጌል በስጋ ከዳዊት ዘር ስለተወለደ፣ እንደ ቅድስና መንፈስ ግን ከሙታን መነሳት የተነሳ በኃይል የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ስለ ተገለጠ ስለ ልጁ ነው። እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በእርሱም ከእምነት የሚነሳ መታዘዝ እንዲገኝ ጸጋንና ሐዋሪያነትን ተቀበልን ...(ሮሜ 1፤ 1-5)

የምስራች የሆነው ወንጌል ይዘቱ በእነዚህ ምንባባት ውስጥ በግልጥ ጎልቶ ይታያል። ዝርዝሮቹንም እነሆ፡-

- እግዚአብሔር ልጁን ላከ ....
- ከዳዊት ዘር የተወለደውን ....
- ሰው የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስ ...
- ስለኅጢአታችን የሞተውን ...

- የተቀበረውን ...
- ከሙታን የተነሳውን ...

እነዚህ ነገሮች የመልካም የምስራች *ይዘት* ናቸው። እስቲ ከላይ የዘረዘርናቸውን ከዚህ በፊት በተነጋገርነው የታሪኩ ትልቅ ምስል ብርሃን አንፃር እንመልከት፡-

> የእግዚአብሔር ልጅ ሰው ሆነ። ኃጢአታችን ከእግዚአብሔር ቤተ ሰብ ውጪ እንዳያደርገን ተሰቃይቶ በመስቀል ሞተ። እኛ ሞትን ድል ነስተን ብቸኛ እውነተኛ አምላክ ከሆነው ከአባቱና ከአባታችን ጋር ለዘላለም እንኖር ዘንድ እሱ ከሙታን ተነሣ።

እስቲ ትንሽ እናብራራው። መልካሙ ዜና ይህ ከሆነ *ለምን* መልካም ተባለ? ብዙ ምክንያት ማቅረብ እንችላለን። መልካምነቱ፣ ድነታችን በእኛ ብቃት አለመመሠረቱ ነው። በሕይወት መንገድ ላይ የሩጫችንን ብቃት እንዲሁም ንጽህናችንን ማሳየት አይጠበቅብንም። የወንጌል መልዕክት ይዘቱ እኛ በብቃታችን የሰራነው ወይም ልንሰራ ያለው ወይም መስራት ያለብን ስራ አይደለም። በሌላ ሰው የተደረገልን ነገር ነው። ፍጹም ስላልሆነን ያ ለእኛ መልካም ዜና ነው። ማንኛችንም እግዚአብሔርን ሁልጊዜ አናስደስተውም። ማንኛችንም በራሳችን ቤተ ሰቡ ውስጥ ልንከትትና በስሙ ልንጠራ ብቁ አይደለንም። *በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረን መደረግ አለብን።* የወንጌል ይዘቱ የሚነግረን ያ እንዴት እንደሚፈጽም ነው።

ጳውሎስ ለሰዎች መልካም የምስራች የመስበክ አገልግሎቱን *"ከእምነት የሚነሣ መታዘዝ እንዲገኝ"* በማለት ይገልጠዋል። የሰሙት ሰዎች መልዕክቱን *"አጥብቀው እንዲይዙ"* ያፈልጋል። ወንጌልን እንዴት "ልንታዘዝ" እንችላለን? በመጠመቅ? ገንዘብ በመስጠት? በጎ ምግባር በማሳየት? ጨዋ በመሆን? ለደሃ በመመጽወት? እነዚህ ሁሉ ጠቃሚ ቢሆኑም፣ መታዘዣ መንገዶች አይደሉም። እግዚአብሔር የሚፈልገው *"ከእምነት የሚነሣ መታዘዝ"* ነው። ወንጌልን የምንታዘዘው ወንጌልን *በማመን* ነው።

ጳውሎስ "ከመረዳት የመጣ መታዝዝ" እንዳላለ አስተውላችኋል? እግዚአብሔር በክርስቶስ ሰው የመሆኑን እውነት ሙሉ በሙሉ ላንረዳ እንችላለን፤ ወይም ትንሳኤ እንዴት ሊከናወን እንደሚችል ላይገባን ይችላል። ይኼ ምንም አይደለም። እግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ አውቃችሁ ለመጨረሻ ፈተና እንድንቀርብ አላዘዘንም። እሱ የሚፈልገው *እምነት* ነው፤ እነዚህ ነገሮች አምክኖአዊ መሆናቸውን መረዳት ሊቆይ ይችላል።

የወንጌል ይዘት ከእግዚአብሔር የተቸረን ምህረትና በቤተ ሰቡ ውስጥ የተሰጠን ቋሚ ስፍራ ነው። ስጦታው ፍቅሩንና ርኅራሄውን ያሳያል። በእነዚህ ቃላቶች ምትክ፥ መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንዴ “ፀጋ” የሚለውን ቃል ይጠቀማል። ከእርሱ የሚበልጥ ኀይል ስለሌለ፥ እግዚብሔር እንዲሰጠን አልተገደደም። እጁን የጠመዘዘው የለም። ስለወደደን ድነትን ሰጠን። ከእኛ የሚጠይቀው ማመን ብቻ ነው።

ያ የወንጌል መልካም የምስራች ነው።

*ወንጌል ለምን አስፈለገን?*

ይኼን ጥያቄ ቀድሞውኑ እንደመለስኩት ታስቡ ይሆናል። ዙሪያ ጥምጥም በሆነ መንገድ መልሼዋለሁ። በዙሪያዬ ባሉ አማኞች እንዳየሁት ከሆነ ነገሩን አፍረጥርጬ መናገር ያስፈልገኛል።

ወንጌል ለምን ያስፈልገናል? ምክያቱም በወንጌል ካልሆነ በቀር ከእግዚአብሔር ጋር የዘላለም ሕይወት ለማግኘት ተስፋ የለንም። ዜሮ ተስፋ። በኃጢአታችን ምክንያት ከእግዚአብሔር ተለይተናል። መፍትሔው ወንጌልን ማመን ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ያለንበትን የጥፋት ሁኔታ በብዙ መንገድ ይገልጣል። ኢየሱስ “የጠፉትን ፈልጎ ለማዳን እንደመጣ” ተናሯል (ሉቃ 19፥10)። ከተፈጥሯችን “በመተላለፋችንና በኃጢአታችን ሙታን”(ኤፌ 2፥1፣5) እንዲሁም “ኀጢአተኞች” ነበርን (ሮሜ5፥6)። የእርሱ “ጠላቶች” በመሆናችን (ሮሜ 5፥10)፣ ከእግዚአብሔር “ተለይተን” (ኤፌ 4፥18) እርሱንም “የምንጠላ” ነበርን (ቆላ 1፥21)። ይኼ አስደሳች ገጽታ አይደለም።

ከላይ የዳሰስነው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስረዳን የሆንነውን ማንነት ለምን እንደሆንን ነው። በእግዚአብሔር ቤተ ሰብ ውስጥ አልተወለድንም። በውጭ ያለን ነን። ቢሆንም እግዚአብሔር ቤተ ሰቡ ውስጥ እንድንሆን ፈለገን። ከባሕሪው በመጉደላችን፥ ዕውቀታችንና ነፃነታችንን የምንፈልገውን ሁሉ ለማግኘት ያላግባብ ተጠቀምን፤ በሂደቱም ሌሎችን ብዙ ጊዜ እንጎዳለን። ራሳችንን በሚያጠፋ መንገድ እንኖራለን። እግዚአብሔርን ማንጸባርቅ ሳንችል፥ ሕጉን እንጥሳለን። በሌሎች ላይ ወንጀል ስንሰራ፥ ስንጠቀምባቸው፥ ስንጎዳቸው፥ ኀጢአትን እናደርጋለን። ራስ ወዳድና አመጸኛ ኃጢአተኞች ነን። “ሁሉ ኃጢአትን ሰርተዋልና፣ የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል” (ሮሜ 3፥23)።

ይኼንን አንብበን መቆዘምም ሆነ መናደድ ቀላል ነው። የወንጌሉ ታሪክ መልካም ዜና ግን እግዚአብሔር ያን ሁሉ እንደሚያውቅና እንዲሁ እንደሚወደን ነው። ይህ ይሆናል ብለን አለማሰባችን ምክንያት ያለው፥ እንዲሁም ጠቃሚ ነው። ወንጌልን በሌላው ሐይማኖት ከሚገኘው የድነት ትምህርት ፈጽሞ የሚለየው ይህ ነው። ሌሎች ሐይማኖቶች ወይ ሐጢአትን ይክዳሉ፣ አሊያም ሃይማኖታዊ ተመስጦን፣ ጸሎት መደጋገምን፣ በዓላት ማክበርን፣ ካልሆነም መልካም መሆንን እንደ መፍትሔ ያቀርባሉ።

ግልጽ ለማድረግ ያህል፥ ሰው ያለበትን ሁኔታና ከዚያ ለመውጣት ያለመቻል ዐቅመ-ዉስንነቱን እውነት በግልጽ የሚነግረን ወንጌል ብቻ ነው። ሌሎች ሐይማኖቶች ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን የርቀት ክፍተት ራሳችን ማጥበብ እንደምንችል ወይም ምንም ክፍተት እንደሌለብን በመንገር ይዋሹናል። እግዚአብሔር መፍትሔ ማምጣት እንዳለበት እንዲሁም እንዳመጣ የሚነግረን የወንጌል እውነት ብቻ ነው። ወንጌል ግልጽና ሽንገላ-ዐልባ ነው። ብንጐዳበትም እውነቱን ይነግረናል። ያ ፍቅርን ያሳያል። ከተዋሸን ፍቅር አይደለም።

*ሌላ መዳኛ መንገዶች አሉን?*

ይብዛም ይነስም ይህንን ጥያቄ መልሻለሁ፥ ቢሆንም ጥያቄውን በሌላ አቅጣጫ ለማየት እፈልጋለሁ።

እግዚአብሔር የኃጢአትን ይቅርታ፣ ድነትና የዘላላም ሕይወትን *በነፃ* ሰጥቶናል። ይኼ የለፋንበትም ወይም የተገባን ሆኖ አይደለም። ደግሞም፥ በልፋታችንም ሆነ በሥራችን የኛ ማድረግ የምንችለው ነገር አይደለም። የተጠየቀው እምነት ብቻ ነው፡- በክርስቶስ ተሰርቶ ባለቀ ስራና በእግዚአብሔር ተስፋ ሙሉ በሙሉ መተማመን።

ነገር ግን ወንጌልን ማመን ማለት ስለ ድነት የሚነገሩ ሌሎች ሐሳቦችን ወይም ትምህርቶችን *አለማመን* ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሌላ መዳኛ መንገድ እንደሌለ ይነግረናል። እስቲ እናስበው። ወደ ሰማይ መግቢያ ሌላ መንገድ ካለ፤ እግዚአብሔር ልጁ ያንን የመሰለ ሰቅጣጭ ሞት በመስቀል ላይ ይሞት ዘንድ እንዴት ይልካል? ልጁ ሰው ሆኖ መምጣት፥ ሞትም ድል መነሳት ነበረበት። ይኼ ብቸኛ መንገድ ሲሆን፤ በዚህ የእግዚአብሔር ዕቅድ ማመን ደግሞ ብቸኛው የድነት መንገድ ነው። ከኢየሱስ ውጪ ማዳን የሚችል ሌላ የለም (ሐዋ 4፥12)። ይኼንን እውነት ኢየሱስ በግልጽ "እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፣ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም" (ዮሐ 14፥6) በማለት አስረግጧል።

ምንም ግራ የሚያጋባ ነገር የለም። ኢየሱስ በፈጸመው የድነት ስራ ካልሆነ በቀር ማንም የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ቤተ ሰብ አባል መሆን አይችልም። ወንጌል ብቸኛ ነው፤ በሌሎች ላይ ደርበን አናምነውም። በወንጌል ማመን ማለት ለሎሎች እምነቶች *ጀርባ መስጠት* ማለት ነው። ይኼንን "መመለስ" መጽሐፍ ቅዱስ ንስሃ ብሎ የሚጠራው ሌላው ገጽታ ነው። በሚቀጥሉት ክፍሎች ቢብራሩ የተሻሉ የሚሆኑ ሌሎችም ገጽታዎችም አሉ።

*ወንጌል ምን አይደለም?*

የወንጌልን *ይዘት* በተነተንንበት ክፍል ወንጌል ኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ምትክ የፈጸመው ተግባር መሆኑን በግልጽ አስቀምጠናል። የዘላለም ሕይወት ማለትም ድነት ኢየሱስ ክርስቶስ እነርሱን ወክሎ የፈጸመላቸው ስራ መሆኑን ለሚያምኑ የተሰጠ ስጦታ ነው።

ባህላችን ይኼንን ግልጽ እውነት ሊበክለው ይሞክራል። ራስን ማሻሻል ወይንም የደበዘዘ "መንፈሳዊነትን" በምትክነት ያቀርባል። የመጽሐፍ ቅዱስ የወንጌል ገለጻ ግን እነዚህን ያዋርዳቸዋል። ወንጌል ወይም ድነት አንድ ግለሰብ ራሱን ለማወቅ "ወደ ውስጡ የሚመለከትበት" ጉዞ እንዲሁም ከግለሰባዊ አብርሆት ጋር ፈጽሞ አይያያዝም። ወንጌል *"መንፈሳዊ መረዳቶች"* የተባሉ እንቶ ፈንቶ ሐሳብ ጥርቅምቅም አይደለም። እነዚህ ምሁራዊ ወይም ስነ ልቦናዊ ብቃትና ድርጊቶች ናቸው፤ ወንጌል ግን አይደሉም።

እነዚህን የመሳሰሉ *"አማራጭ ወንጌሎች"* በቀላሉ ለይተን ማስወገድ የምንችላቸው ናቸው። ነገር ግን ሌሎች በቀላሉ ለመለየት አስቸጋሪ የሆኑ፣ ሰዎች እግዚአብሔር በሰጣቸው ቀላል የድነት መንገድ "እፎይ" ብለው እንዳያርፉ የሚያደናቅፉ እንቅፋቶች አሉ።

ከላይ እንደገለጽኩላችሁ፣ በቤተ ክርስቲያን የምናገኛቸው አያሌ ሰዎች ከወንጌል እውነት ምንነት ጋር ትግል ላይ ናቸው። ምክንያቱ ደግሞ በተለያዩ የ *"ሰርተህ ጽደቅ"* ወጥመዶች ስለተያዙ ነው። እናንተም ሆናችሁ ሌሎች ሰዎች ወንጌል የሚለውን *ቃል* ለመተርጎምም ሆነ ይዘቱን ለመተንተን ትችሉ ይሆናል። ይሁን እንጂ የዘላለም ሕይወት ለማግኘት የሚያስፈልገው ብቸኛው ነገር ኢየሱስ እኛን ወክሎ በሰራው ስራ ማመን ነው የሚለው ሐሳብ ብቻውን ልክ አይመስልም። የሆነ ነገር *ማድረግ* አለብን። አለበለዚያ ይኼ እንዴት ሊገባን ይችላል?

የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ እና የወንጌልን ይዘት ሙሉ በሙሉ ከተረዳን እግዚአብሔር በነፃ ለሚሰጠን ነገር ሁሉ *የተገባን እንዳልሆነ* ወዲያው

እናስተውላለን። ይኼ የብዙ ሰዎች ትግል ነው። ያሉንን በጎ ነገሮች ሁሉ ደክመን እንዳገኘናቸው እንዲሰማን እንፈልጋለን። የደግነት መገለጫ መሆን አንፈልግም። መልካም ነገር ትንሽም ቢሆን ሳንለፋበት መቀበል ስህተት ይመስለናል።

ኩነኔ (የበደለኝነት ስሜት) አስተሳሰብን ከዚህ በላይ አታላይ በሆኑ መንገዶች አዛብቷል። *ወንጌል ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የተሰጠ የእግዚአብሔር ስጦታ እንደሆነ እንዳናይ* ችሎታችንን ሽባ ሊያድረግ ይችላል። አንዳንድ ሰዎች ስጦታን ሲቀበሉ እነርሱ በሆነ መንገድ ለሰጪው ላደረጉት ነገር የተገባቸው ምላሽ እንደሆነ እንዲያስቡ የሚያደርጋቸው ይኸው የበደለኝነት ስሜት ነው። ለራሳቸው ይኼንን ማሳመን ባቃታቸውም ጊዜ (ስጦታን ከተቀበሉ በኋላ እንኳ) እንደተገባቸው እንዲሰማቸው የሆነ ነገር ማድረግ እንዳለባቸው ይወስናሉ።

ኩነኔ በወንጌል የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ፍቅር እንዳናይ አሳውሮናል። በመጨረሻም ይኼ ምን ያህል ራስ ተኮር አስተሳሰብ እንደሆነ ልንረዳ ይገባል።

ይኼ ትንሽ ጠንከር ያለ ነገር ቢመስልም ስሙኝ። ሰዎች ዋጋ እንዳለን እንዲያስቡ መትጋት እንዳለብን ስናስብ ራሳችንን የትኩረት ሁሉ ማዕከል እያደረግን ነው። ዓላማችን ሌላ ሰው ትኩረት ወይም ፍቅር የተገባን እንደሆነ አድርጎ እንዲያስብ ከሆነ፥ ትኩረታችንን በሌላ ሰው ላይ ማድረግ አንችልም። ስለራሳችን በጎ እንዲሰማን እንሻለን (በመሆኑም፣ የማይገባንን እንደማንቀበልና የተቀበልነውን የማግኘት መብት ያለን አድርገን እናስባለን)። በተጨማሪም ሌሎች በተመሳሳይ መንገድ እንዲያስቡን እንፈልጋለን (በመሆኑም፣ አንድን ነገር ከሌሎች ስንቀበል ነገሩ የተሰጠን የተገባን ስለሆነ አድርገው *እንዲያስቡ ማድረግ* እንሻለን)።

ወንጌል እነዚህን ነገሮች በማራቆት ወደ ጎን ይጥላቸዋል። ያጋልጠናል፥ ከእኛም ራቁትን የቀረ ትህትና ይጠብቃል። መላው ትኩረታችን በእግዚአብሔርና በክርስቶስ ላይ ብቻ እንዲሆን ያደርጋል። ለብዙዎች የማይውጡት መራራ ክኒን የሆነባቸው በዚህ ምክንያት ነው። ምንም ዓይነት ምስጋና ለራሳችን እንድንቀበል አይፈቅድም።

ነገሩን ስንጠቀልለው፤ ወንጌል እናንተ ስለ ምታድርጉት ነገር *ግድ አይለውም፣* ግን ስለሆናችሁት *ሁሉ* ግድ ይለዋል። እናንተ ሰዎች ናችሁ። ከመጀመሪያውም የእግዚአብሔር ፍቅርና ዕቅድ መገለጫዎች ናችሁ። ይኼ ምንም ብቃት አይጠይቅም። እንዲሁ *የሆነ* ነው።

በዚህ የወደቀ ዓለም የምንኖር ኃጢአተኞች ስለሆንን፥ ውስጥና ውጫችንን አብጠርጥሮ ቢያውቅ ኖሮ ማንም ሊወደን አይገባም በሚል የሐሳብ ሳጥን ውስጥ

ተቆልፈን ያለን ሰዎች ነን። ከእግዚአብሔር ትኩረት የሚያመልጥ ምንም ነገር የሌለን በመሆኑም እግዚአብሔር ራሱ እንደሚወደን ማሰብ አንችልም። እሱ ሀሳባችንን፣ ንግግራችንን፣ ስሜታችንን፣ እና ድርጊታችንን ያውቃል። ያ በውስጣችን የሚፈጥረው የበደለኝነት ስሜት እንዲሁም የእኛ የተለመደው የእንካ በእንካ ግንኙነት፥ በወንጌል የተገለጠውን ቅድመ-ሁኔታ የለሽ ፍቅር ለመቀበል አዳጋች ያደርገዋል። እንደ አመለካከታችን ከሆነ፣ የማይገባ ጉዳይ ነው።

እዚህ ላይ ማንሳት የሚገባኝ አንድ ነጥብ ቢኖር፥ ወንጌልን ሰምተው በቅንነት የተቀበሉ ሰዎች አልዳኑም እያልኩ አለመሆኑን ነው። እንዳመኑና የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ አባላት እንደሆኑ የእውነት አምናለሁ።

የገለጽኩት፥ እነዚህ አማኞች እየኖሩ ሳለሉት ነፍስ አድቃቂ ውስጣዊ ሕይወት ነው።  የበደለኝነት ስሜታቸው የወንጌሉን ፀጋና ፍቅር ወደ ግል ብቃት ተኮር፤ ክፍያን መሰረት ወዳደረገ ልምምድ ቀይሮባቸዋል። ወንጌሉን ተረድተው በእምነት በተቀበሉበት ቅጽበት እግዚአብሔር ይወዳቸው እንደ ነበረ አሁን ይወደኝ ይሆን ብለው ያመነታሉ። አማኝ ሳሉ ያደረጉትን ኃጢአት እንደ ምክንያት በማቅረብ እግዚአብሔር እንደማይራራላቸውና ሊጨቅንባቸው እንደሚገባ ያስባሉ። እግዚአብሔር ከእነርሱ የሚጠብቅባቸውን መስፈርት እንዳላሟሉ አድርገው ራሳቸውን አሳምነዋል። በበቂ ሁኔታ ማመን ያለመቻላቸውን ወይም ያመኑ ሲመስላቸው ከነጭራሹ አለማመናቸውን እያሰቡ በጥርጣሬ ይባክናሉ።

በርካታ  እውነተኛ አማኞች የሰቆቃና ሽንፈት ሕይወት የሚኖሩበት አሳዛኝ እውነት በወንጌል ምክንያት ሳይሆን የበደለኝነት ስሜት ግልጽ የሆነውን የወንጌል እውነት ስላጣመመባቸው ነው። ቃሉን ሲያነቡ የሚያዩት ኃጢአታቸውና ውድቀታቸውን ብቻ ነው። ስብከቱ ሁሉ ክስ ነው (ክስን ዓላማ አድርገው ሁል ጊዜ የሚሰብኩ ሰባኪዮች ሊያፍሩ ይገባል)። በዚህ መልክ አስገራሚው ታሪክ ይጠፋል ወይም ይረሳል።

ድነት የብቃት ጉዳይ *አይደለም*፣ ሆኖም አያውቅም፥ ወደፊትም አይሆንም፤ *መሆንም አይችልም*። እግዚአብሔር በሚገኝበት ደረጃ ላይ ራሳችንን ለማስቀመጥ ማለትም ለህልውናው ብቁ ሆነን ለመገኘት የምናደርገው ምንም ነገር የለም። *የእግዚአብሔር ፍጹም ባሕሪው የለንም*። በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠርን አምሳያዎቹ ነን፥ ይህም ማለት ከእርሱ *እናንሳለን*፥ እግዚአብሔርም ይህንን ያውቃል። ኢየሱስ እንጂ *እኛ* ከእግዚአብሔር የተሰጠ መፍትሔ ያልሆንበትም ምክንያት ይኸው ነው።

ይህንን ወይም ያንንም በማድረግ ድልድይ ሰርተን ርቀቱን እናጠባለን ወይም ክፍተቱን እንሞላለን ብሎ ማሰብ ዕብደት ነው። እግዚአብሔር ከውድቀታችን ስለእኛ አንዳች አዲስ ነገር አልተማረም። ሁሉን ነገራችንን ያውቃል። በነበርንበት፣ባለንበት ይወደናል። ሮሜ 5፥8 ነገሩን በሚገባ ይገልጻል፡- “ ነገር ግን ገና *ኃጢአተኞች ሳለን* ክርስቶስ ስለእኛ ሞቷልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል” ይላል። ተረዳችሁ? ይኸው ነው፣ *ኃጢአተኞች ሳለን*። እግዚአብሔርን እንዲወዳችሁ ለማነሳሳት ማድረግ ያለባችሁ ስራ የለም። ካሰባችሁት ይኼ *በእውነት* መልካም የምስራች ነው። እግዚአብሔር ስለ ባህሪያችሁ የተሳሳተ ግንዛቤ ስለሌለው *ፈጽሞ* ተስፋ አልቆረጠባችሁም። እግዚአብሔር በነበራችሁበት ይወዳችኋል። “በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንዲያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና” (ዮሐ 3፥16)።

ይኼን እውነት ወደ ሁለት ልንሰነጥቀው እንችላለን። ድነት ማለትም የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ አባል መሆን፣ በስራ አይገኝም፤ በእምነት ብቻ የምንቀበለው ነው። እግዚአብሔር ባለ ፀጋ እና አፍቃሪ ስለሆነ በነጻ ሰጥቶናል። ሌላ ምክንያት የለም፤ ሊኖርም አይችልም።

# ክፍል ሦስት፡-ኢየሱስን መከተል

## ምዕራፍ ስምንት

## ደቀ መዝሙርነት ምንድነው?

የወንጌል ዓላማ ፈጽሞ መለወጥ ነው። ወንጌልን የተቀበለ ሁሉ "አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፣ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል" (2ቆሮ 5፥17) ይኼ በተግባር ምን መስሳል?

የዚህን ጥያቄ መልስ ታስታውሱ ይሆናል። እስቀድሜ፥ ደቀ መዝሙር ተከታይ ማለት እንደሆነ በተለይም የኢየሱስ ተከታይ እንደሆነ ተናግሬያለሁ። መከተል የሚለውን ቃል ኢየሱስን መምሰል ወይም እርሱን ማንጸባረቅ ብዬ ተርጉሜዋለሁ። "የልጁን መልክ መመሰል" የመጨረሻው ግባችን ነው(ሮሜ 8፥29፤ 2ቆሮ 3፥18፤ ቆላ 3፥10)።

ክርስቶስን የመምሰላችን መነሻ ሰበብ እግዚአብሔር እንዲወደንና ወደ መንግስቱ እንዲያስገባን *ለመደለል* አይደለም። እግዚአብሔር "ኃጢአተኞች ሳለን" (ሮሜ 5፥8)፤ እና የእርሱ "ጠላቶች" (ሮሜ 5፥10) ሆነን አስቀድሞ ወዶናል። በወንጌሉ *ባመንንበት* ጊዜ የቤተ ሰቡ አባላት በመሆን ወደ መንግስቱ ገብተናል። በራሳችን "ከእግዚአብሔር ተለይተን" (ኤፌ 4፥18)፥ አዳኝ የሚያስፈልገን የጠፉን ነን (ሉቃ 19፥10)። *እንደዚያ* ሳለን እግዚአብሔር ወደደን። እኛን ከቆሻሻው ድርጊታችንን እስክናነጻ አልጠበቀም።

ክርስቶስን የመምሰላችን መነሻ ሰበብ እግዚአብሔር እኛን በማፍቀር *ቀጥሎ* በመጨረሻም እንዲያድነነ ለማድረግ አይደለም። ይኼ በእኛ ብቃት የሚገኝም ሆነ የሚጠፋ አይደለም። ድነት ከመልካም ስራችን ወይም ከማንነታችን ጋር ፈጽሞ አይገናኝም። ድነት ኢየሱስ ለእኛ በሰራው ስራ ላይ የተመሰረተ ነው። "እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለእኛ ኃጢአት አደረገው" (2ቆሮ 5፥21)። እኛ ስለድነታችን ምንም ምስጋና መውሰድ አንችልም፤ጠቅላላ ዋጋው የኢየሱስ ነው።

### *ስለ ደቀ መዝሙርነት በግልጽ ማሰብ*

ከላይ የገለጽናቸው ነገሮች ሁሉ በደቀ መዛሙርነት ሕይወት ውስጥ እንዴት እንደሚተገበሩ በጥንቃቄ ማሰብ አለብን።

ከላይ ከገለጽኩላችሁ ከብቃት ወጥመድ የተነሣ፥ ድነትና ደቀ መዘሙርነት አንድ ያለመሆናቸውን እውነት በግልጽ መጨበጥ አለብን። ብዙ አማኞች ከበደለኝነት

ስሜት የተነሣ ሳያገናዝቡ የገዛ ሥራቸውን ወይም ብቃታቸውን ወንጌል ላይ ተጨማሪ ያደርጋሉ ። ውጤቱም ክርስቶስ እንዲኖረን የሚፈልገው የተትረፈረፈ ሕይወት ሳይሆን መንፈሳዊ እስራት ይሆናል (ዮሐ 10፥10፤ 2ቆሮ 1፥5፤ ኤፌ 3፥20)።

ድነት በወንጌል *በማመናችን* የተገኘ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። የማይገባን ነገር ነው። ለእርሱ ካለን ጠላትነትና ኃጢአት በተቃራኒ እግዚአብሔር ድነትን ሰጠን። ደቀ መዝሙርነት ወንጌልን በማመናችን እኛ የምንሠራው *ውጤት* ነው። ኢየሱስን መምሰል ያለብን ለእርሱና ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር ለመግለጽ ነው። ኢየሱስ የመጨረሻው የእግዚአብሔር ነጸብራቅ ነው። እኛም በተመሳሳይ መልኩ መኖር አለብን።

እንደ ኢየሱስ የተቀደሰ ሕይወት ለመኖር አያሌ ምክንያቶች አሉን። የእግዚአብሔርን ፍቅር ማግኘት ግን ከእነርሱ አንዱ አይደለም። ድነት ምንም ነገር አያስከፍለንም። በወንጌል ላመኑ ሁሉ ነፃ ስጦታ ነው። ደቀመዝሙርነት ግን የሚያስከፍለን ነገር አለው። ኢየሱስን መከተል ብዙ ጊዜ ቀላል አይደለም። ደቀ መዝሙርነት እግዚአብሔርን ለመውደድና ለማክበር፥ እንዲሁም እግዚአብሔር መልኩን እንዲያጸባርቁ ወንጌልንም አምነው ቤተ ሰቡ እንዲሆኑ የፈጠራቸውን ሰዎች የማክበር ምርጫ ማድረግን ይጠይቃል።

የክርስቶስን ሕይወት አስቡ፤ ቀላል አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው "የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፤ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና" (1ጴጥ 2፡ 21)። ኢየሱስ የመስዋዕትነት ሕይወት ኖሯል። እሱ እግዚአብሔርን አስቀድሞ ባልንጀሮችን (ሁሉን) በሙሉ ያስከተለ ሕይወት ኖረ።

> ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ። ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትዕዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛቱም ይህችን ትመስላለች፣ እርሷም ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት። በእነዚህ በሁለቱ ትዕዛዛት፣ ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ተሰቅለዋል (ማቴ 22፥36-40)።

ኢየሱስ ሕይወቱን እንዲህ የኖረው እግዚአብሔር እንዲወደው ወይም እንዲደሰትበት አይደለም። ኢየሱስ ወደ ምድር መጥቶ ኪዳኑን የመፈጸም ሥራ ከመስራቱ (ከብቃቱ) በፊት አስቀድሞ ይወደዋል። ኢየሱስን "ዓለማት ሳይፈጠሩ" ወዶታል (ዮሐ 17፥24)።

ኢየሱስን መከተል አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። የትኛውም አማኝ መጀመሪያ ሲያምን እንደ ኢየሱስ ባለመሆኑና ወጥነት ባለው መልኩ እንደ ኢየሱስ መኖር ከባድ በመሆኑ፤ እያንዳንዱ አማኝ ለባህሪው መለወጥ ወሳኝ የሚሆነውን የልብ ለውጥ (መጽሐፍ ቅዱስ "ንሰሃ" የሚለውን) ማድረግ አለበት። እኔም አድርጌ አውቃለሁ። ማቆም የነበሩብኝ ነገሮች፥ እንዲሁም ማድረግ መጀመር የነበሩብኝ ነገሮች ነበሩ። ግን የትኞቹም እግዚአብሔር እንዲወደኝ ለማድረግ አልነበረም፤ ቀድሞውኑ ወዶኛልና።

ኢየሱስ ያደረገውን ሁሉ ያደረገው እግዚአብሔርን ስለሚወድ ነው። እኛም እንዲሁ ማድረግ አለብን። ሰዎች በእግዚአብሔር ዕቅድና በእርሱ እንዲያምኑ ለመርዳት ኢየሱስ ይኖር ነበር። እኛም እንዲሁ ማድረግ አለብን። ኢየሱስ ወደ ምድር ለምን እንደመጣ ያውቃል–በምታካችን አስቀያሚውን ሞት ለመሞት። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፍቅርና ኃይል ተማምኖ ነበር። ከሙታን ተነስቶ እንደገና ከአባቱ ጋር እንደሚሆን ያውቃል።

እንዲሁ እኛ ዘላለማዊ ምልከታ ሊኖረን ይገባል። ይኼ ዓለም እውነተኛው ቤታችን አይደለም፤ ወቅታዊ ነው። የሚመጣው ዓለም ቋሚ ነው። ኢየሱስ ከሠራልን ሥራ የተነሣ ይኼንን ዓለም ወደ ኋላ ጥለን የሚመጣውን ዓለም ዘላለማዊ ሕይወት እንወርሳለን። የሕይወታችን ግብ መሆን ያለበት ላዳነን አምላክ ታማኝነት ማሳየት፣ በምስጋና መኖር፣ እንዲሁም ሌሎች ወደዚህ ወደ እግዚአብሔር ቤተ ሰብ እንዲመጡ መርዳት ነው።

ብንወድቅስ? ኃጥአት ብናደርግስ? ሁለቱንም እናደርጋለን።እግዚአብሔር ያንን ያውቃል።እሱ ሰውን አብጠርጥሮ ያውቃል።ነገር ግን እሱን በአጸፋ መልሰን ልንወደው የሚያስችል ምንም ነገር የመስራት ቅንጥብጣቢ ፍላጎት ሳይኖረን በፊት አስቀድሞ ወዶናል።አስቀድሞ " ኃጢአተኞች" (ሮሜ 5፡ 8) እና ጠላቶች ሳለን ወደደን።ቤተ ሰቡ ውስጥ ሳንሆን በፊት ወደደን።ይኼ ከሆነ ታዲያ ቤተ ሰቡ ከሆንን በኋላ ቀድሞ ከወደደን ባነሰ መጠን እንዴት ሊወደን ይችላል? መውደድን ማቆምስ እንዴት ይቻለዋል? ብንወድቅ ወይም ኃጥአት ብናደርግ ይቅር ይለናል። እንድናምነው፤ ኢየሱስን ወደመምሰል መልክ እንድንመለስ ይፈልጋል።

*እንደ ኢየሱሰ መኖር ለምን አስፈለገ?*

ከላይ ኢየሱስን ለመምሰል አያሌ ምክንያቶች መኖራቸውን ተናግሬያለሁ ነገር ግን *አንዳቸውም የእግዚአብሔርን ፍቅር ለመሸመት* እንዳማይፈይዱ አንስቻለሁ። እነዚህ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

በመጀመሪያ፥ ኃጢአት ለእኛ ብቻ ሳይሆን በዙሪያችን ላሉትም ጭምር ጎጂና አጥፊ ነው። በቤተ ሰቤ ውስጥ የመጠጥ፣ የሱስና የዝሙት ቅሌት ውጤቶችን አይቻለሁ።እነዚህ ነገሮች ሕይወትን እንደሚያጠፉ ግልጽ ነው። በተመሳሳይ መልኩ፣ የማያምኑት ባህል፥ ደስታ ለማግኘትና ራሳቸውን ለማርካት የሚያቀርቧቸው የዚህ ዓለም ነገሮች፥ ዘላቂ ዋጋ የሌላቸው መሆኑ ግልጽ ነው። ባህሉ ውሳኔያችን የሚያስከትለው ምስቅልቅል ሳያሳስበን “ደስታችንን” እንድናጣጥምና “ሕይወትን” እንድንኖራት ይነግረናል። ሕይወትን ዛሬና አሁኑኑ እንድንኖራት ይጠራናል። ከዚህ የላቀ ጥሪ የለም። መጽሐፍ ቅዱስ የዚህን ፍልስፍና ምንጭ ነግረናል፡-

> ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የስጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም። ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያድርግ ግን ለዘላለም ይኖራል (1ዮሐ 2፥15-17)።

ሁለተኛ፥ በብዙ መልኩ ከመጀመሪያው ተቃራኒ በሆነው ምክንያት፤ እግዚአብሔርን የመምሰል ሕይወት መኖር ለሌሎች በረከት የመሆኑ እውነት ነው። እውነቱ፥ አስተሳሰባችንና አኗኗራችን ለሌሎች በረከት፥ አሊያም መርገም ሊሆን መቻሉ ነው። ኢየሱስ ሰዎችን ያገለግል ነበር፥ ባርኮታቸውም ነበር። በራስ-ወዳድነትና በሁሉን አግበስባሽነት ስሌት የሚመራ ሕይወትን መኖር አርኪ አይደለም። በየገበያ ቦታው የሚሸጡ የሐሜት መጽሔቶች ይህን እውነት ያሳብቃሉ። ለሌሎች ባርኮት መሆን የኢየሱስን ሕይወት ማንፀባረቅ ብቻ ሳይሆን ግላዊ የሕይወት እርካታ አለው። ሕይወት ዋጋ የሚኖራት ሌሎችን በማገልገል ስንኖራት ብቻ ነው።

ሦስተኛ፥ እግዚአብሔርን የመምሰል ሕይወት ቋሚ የወንጌል ምስክር እንድንሆን ያስችላል። ሰዎች አኗኗራችንን ሲያዩ ከማያምነው ዓለም ልዩነት ከሌለው፥ ለሌሎች የሚኖር የአገልጋይ ሕይወትን ካላዩ፥ ወንጌል ሊታመን የሚገባ እንደሆነ አያስቡም (ወይም ቢያንስ ይምታታባቸዋል)። ሕይወታችን ከኢየሱስ መልእክት ጋር ተጣርሶ ያዩታል። በሌላ ቋንቋ ሰዎች ይወዳችኋል ብለን የምንነግራቸውን የኢየሱስ ሕይወት እንድንኖር ይጠብቃሉ። ያለምክንያት ይኼን ከእኛ አልጠበቁም። በተቃራኒው ከተኖረ ግብዝነት ነው፥ ይህንንም ማንም አያወድስም።

እግዚአብሔርን የመምሰል ሕይወት መኖር በሰማይ ስፍራን ለማግኘት አይደለም። በምናስመዘግበው “መንፈሳዊ ነጥብም” እግዚአብሔርን ባለዕዳ ልናደርገው

አንችልም። በዚህ ጉዳይ ላይ የሚያወሱን ምንባባት ሙሉ በሙሉ የተለየ ትኩረት አላቸው፡-

> እንግዲህ ወንድሞቼ ሆይ፤ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መስዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፣ እርሱም ለአዕምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህ ዓለም አትምሰሉ (ሮሜ 12፥1-2)።
>
> ሆኖም፡- ጌታ ለእርሱ የሆኑትን ያውቃል፣ ደግሞም፡- የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ከዓመፅ ይራቅ የሚለው ማኅተም ያለበት የተደላደለ የእግዚአብሔር መሰረት ቆሞአል (2ጢሞ 2፥19-21)።
>
> በክርስቶስ አንዳች ምክር ቢሆን፤ የፍቅር መጽናናት ቢሆን፣ የመንፈስ ኅብረት ቢሆን፣ ምህረትና ርኅራኄ ቢሆኑ፣ ደስታዬን ፈጽሙልኝ፤ በአንድ ሐሳብ ተስማሙ፤ አንድ ፍቅር አንድ ልብ አንድ አሳብም ይሁንላችሁ፤ ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ወዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ፤ ነገር ግን እያዳንዱ ባልጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትህትና ይቁጠር፤ እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት ባልንጀራውን ደግሞ እንጂ። በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን። እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም፤ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ በምስሉም እንደሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፤ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ (ፊል 2፥1-8)።

እነዚህ ምንባባት እንዴት መኖር እንዳለብን የተወሰኑ ሀሳቦችን የሚሰጡን ቢሆንም፤ የደቀ መዝሙርነትን ውስን መመሪያዎች እስካሁን አላገኘንም። ደቀ መዝሙር እንዴት መኖር አለበት? ደቀመዝሙር ሥራው ምንድን ነው? እንደ ዕድል ሆኖ፥ ኢየሱስና ክርስቲያን የተባሉት የመጀመሪያዎቹ ደቀመዛሙርት ይኼንን ግልጽ አድርገዋል። ኢየሱስ ራሱ ያላደረገውንና እንዴት መደረግ እንዳለበት በተግባር ያላሳየውን አንዳች ነገር ያደርጉ ዘንድ ተከታዮቹን አላዘዘም። እነርሱም በተራቸው ፈለጉን በመከተል  በመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን የነበሩትን ፈለጋቸውን እንዲከተሉ አስተምረዋል።

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## ደቀመዝሙር ምን ይሰራል?

ነገሩ ሊያስገርማችሁ ይችላል፤ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ በርካታ ነገሮችን ያደርጉ ዘንድ አላዘዛቸውም። እግዚአብሔርንና ሌሎችን ለመውደድ ያለው ራእዩ ውስብስብ አልነበረም። ነገር ግን ደቀመዛሙርቱ እንዲተገብሯቸው ያዘዛቸው ነገሮች የተተገበሩ እንደሆን የላቁና ሕይወትን ከመሰረቱ ለዋጭ ናቸው። ደቀመዝሙር የመሆን እጅግ የለቃውን ነጥብ በማንሣት

*ደቀመዛሙርት እግዚአብሔርንና ባልጀራቸውን ይወዳሉ፤ እርስ በርሳቸውም ይዋደዳሉ*

ኢየሱስ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ሕይወትን እንዴት እንዳደራጀው ተመልከቱ። ከሁሉ የሚበልጠው ትዕዛዝ ይህ ነበር፡-

> ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ። ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትዕዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛቱም ይህችን ትመስላለች፣ እርስዋም ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት። በእነዚህ በሁለቱ ትዕዛዛት፣ ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ተሰቅለዋል (ማቴ 22፥36-40)።

ኢየሱስ እነዚህ ነገሮች ተግብሯቸዋል። ደቀመዛሙርቱንም፡- “ ነገር ግን አብን እንድወድ ዓለም ሊያውቅ አብ እንዳዘዘኝ እንዲሁ አደርጋለሁ” (ዮሐ 14፡ 31) ብሏቸዋል። ኢየሱስ እግዚአብሔርን ማለትም አባቱን መውደዱን እንዴት ነበር የገለጠው? እግዚአብሔርን ታዘዘ። እግዚአብሔር ለርሱ ያለውን ዕቅድ ፈጸመ። ደግሞም ደቀመዛሙርቱን፡- “አብ እንደወደደኝ እኔ ደግሞ ወደድኋችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ” (ዮሐ 15፥9) ብሏቸዋል። ሁለቱ ታላላቅ ትዕዛዛት ግልጽ እንደሚያደርጉት፥ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ ተመሳሳይ ነገር ያደርጉ ዘንድ ጠየቀ።

ኢየሱስ ራሱን እንደ ምሣሌ በማቅርብ ተጨማሪ ነግሮችን ተናገረ። እርሱ ደቀ መዛሙርትን በወደደበት ፍቅር እርስ በእርስ እንዲዋደዱ ነገራቸው። ይህንን ቢያደርጉ፥ እርሱን ይታዘዛሉ እግዚአብሔርንም ያስደስቱታል። እንዲህ አላቸው፡-

> ነፍሱን ስለወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም። እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ። ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም፤ ባሪያ ጌታው የሚያድርገውን

> አያውቅምና፤ ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ፤ ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ለእናንተ አስታውቄአችኋለሁና። እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም፤ አብም በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ እንዲሰጣችሁ ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬአችሁም ሊኖር ሾምኋችሁ። እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ ይህን አዛችኋለሁ (ዮሐ 15፥13-17)።

> እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ እንደወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትዕዛዝ እሰጣችኋለሁ። እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፤ ደቀመዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ (ዮሐ 13፥34-35)።

እንደ ኢየሱስ (ገለፃ) ከሆነ እግዚአብሔርን መውደድና እርስ በእርስ መዋደድ የማይተኩ መሰረታዊ የደቀመዛሙርት ምልክቶች ናቸው። ኢየሱስ እነዚህን ትዕዛዛት በየትኛውም መንገድ ተቃራኒ ሆነው አያያቸውም። ውጥረት ውስጥም አይደሉም። የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው። አይነጣጠሉም።

ነገር ግን ሰዎችን እንዴት እንወዳቸዋለን? ታለቁ መገለጫ ሕይወትን ለሌላው መስጠት ነው፡- “ነፍሱን ስለወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም” (ዮሐ 15፥13)። ይኼ ኢየሱስ ለእኛ ያደረገው ነው፡-

> ስለ ጻድቅ የሚሞት በጭንቅ ይገኛልና፤ ስለ ቸር ሰው ግን ሊሞት እንኳ የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል። ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያሳያል። (ሮሜ 5፥ 7-8)

የዚህ እውነት የላቀው ድርጊት አጠር ያለ ዝርዝር ከ1ቆሮ 13፥4-7 ከተጻፈው የተሻለ ማሰብ አልችልም። ሊባል የሚገባውን ሁሉ ጥሩ አድርጎ ብሎታል። ክፍሉ የፍቅርን ባሕርያት እንዲህ በማለት ይገልጻል፡-

- ፍቅር ይታገሳል
- ፍቅር ቸርነትን ያደርጋል
- ፍቅር አይቀናም
- ፍቅር አይመካም
- ፍቅር አይታበይም
- ፍቅር የማይገባውን አያደርግም
- ፍቅር የራሱንም አይፈልግም
- ፍቅር አይበሳጭም

- ፍቅር በደልን አይቆጥርም
- ፍቅር ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል
- ፍቅር ስለ ዓመጻ ደስ አይለውም
- ፍቅር ሁሉን ይታገሳል
- ፍቅር ሁሉን ያምናል
- ፍቅር ሁሉን ተስፋ ያደርጋል
- ፍቅር በሁሉ ይጸናል

አብዛኛውን ጊዜ እዚህ ዝርዝር ውስጥ ያሉ ነጥቦችን በቫላንታይን (በፍቅር) ቀን ወይም በፍቅር ስጦታ ወረቀቶች ላይ ታዩአችዋላችሁ። ይኼ ጥሩ ነው። የትዳር አጋራችንን ወይም የትዳር አጋራችን ሊሆን ያለውን ሰው ማፍቀር ግድ ነው። ነገር ግን 1ቆሮ 13፥4–7 ከእንደዚህ ዓይነት ፍቅር ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ባጠቃላይ ሰዎችን ሁሉ በዚህ መልኩ ልንመለከት ይገባል። ሰዎች ይህንን እንደ ፍቅር አዩት አላዩት ጉዳያችን አይደለም። እግዚአብሔር ያየዋል ያውቀማል።

ከእነዚህ ውስጥ አንዳንድ ነጥቦች በዝርዝሩ ውስጥ ካሉ ከሌሎች ጋር ተሳስረው ሊነበቡ ይገባል። ለምሳሌ፦ “ፍቅር ሁሉን ያምናል” የሚለው፣ “ፍቅር ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል” ከሚለው ጋር ሚዛናዊ ተደርጎ መነበብ አለበት። “ፍቅር ሁሉን ያምናል” የሚለውን ነጥለን በማውጣት ፍቅር ሐሰተኛውን ወይም እኩይ አስተምህሮ ይወዳል ወደሚለው ድምዳሜ መምጣት የለብንም። በተመሳሳይ መልኩም “ፍቅር ሁሉን ተስፋ ያደርጋል” የሚለው ሌላውን ሰው ክፉ እንዲያገኘው ተስፋ ማድረግ የሚለውን አያመለክትም። በአጠቃላይ ዝርዝሩ ለመራዳት ቀላል የሆነ ነገር ግን የየዕለቱን ተግባራዊ ኑሯችንን የሚፈትን ነው።

ወደ ሌላ ጉዳይ ከማለፋችን በፊት አንድ ተጨማሪ ነጥብ መጨመር እፈልጋለሁ። የደቀመዝሙርነትን ምንነት የሚያመለክቱ እውነቶች በሙሉ “እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ እንደወደድኋችሁ እናንተ ደግም እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትዕዛዝ እሰጣችኋለሁ። እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ ደቀመዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ” (ዮሐ 13፥34-35) ከሚለው የኢየሱስ የመጀመሪያ ትዕዛዝ የሚመነጭ መሆኑን ማስተዋል ወሳኝ ነው። እርስ በርስ መዋደድ እና ሌሎችን መውደድ ደቀመዛሙርት ለሚያደርጓቸው እንደ ጸሎት፣ ፆም፣ አምልኮና ወዘተርፈ ድርጊቶች በሙሉ መነሻ ማዕከል ነው። እነዚህ ነገሮች በሙሉ የመሰረታዊው ትዕዛዝ  መገለጫዎች ናቸው፡፡

*ደቀመዛሙርት አንዳቸው ሌላኛውን ይንከባከባሉ*

አንዱ ሌላውን የመንከባከብ ሕይወት እርስ በእርስ ከመዋደድ የሚመነጭ ነው። አንዱ ሌላውን መንከባከብ፥ በማሕበር ውስጥ መሆንና ማሕበሩን መገንባት ማለት ነው።

ከባዓለ ኀምሳ ቀን በኋላ በወንጌል የሚያምኑ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ (ሐዋ 2፡ 1-4)፥ አማኞች በጊዜው በኢየሩሳሌም በነበረ በኋላ "ቤተክርስቲያን" ተብሎ በተጠራ፥ በፍጥነት እያደገ ባለ ማህበር አባላት ሆኑ። በአዲስ ኪዳን "ቤተክርስቲያን" የሚለው ቃል ሕንጻ ወይንም ህጋዊ ድርጅትን አያመለክትም። አዲስ ኪዳን እንደሚነግረን ከሆነ በኢየሩሳሌም የነበረችው ቤተክርስቲያን የምትታወቀው በድህነቷ ነበር። በሺዎች የሚቆጠሩ አዳዲስ አማኞች ቢኖሯቸውም፤ ለአምልኮ የሚሰበሰቡበት ሕንጻ አልነበራቸውም (ሐዋ 2፥41፤ 47፤ 5፥14)። ከመንግስት የተሰጠ ሕጋዊ እውቅና ስለሌላቸው፥ ከፍተኛ መከራ ይደርስባቸው ነበር (ሐዋ 3፥11-4፥31፤ 5፥17-42)።

"ቤተክርስቲያን" ሕጋዊ ዕውቅና ያላት ድርጅት ወይንም ሕንጻ ካልሆነች ታዲያ ምንድን ናት? የኢየሱስ ተከታዮች እንዴት ሊቆዩ ቻሉ? እርስ በእርስ የተጣበቀ፣ አንዱ ለሌላው መስዋዕት መሆን የሚችል ማሕበር ገንብተው ነበር። ዘምናይቱ ቤተ ክርስቲያን፥ ማህበር የሚለውን ቃል የምትጠቀመው ተመሳሳይ ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች (ልክ የስፖርት ደጋፊዎችን ወይም ከአንድ በጎ ድርጊት በኋላ የሚቆሙትን) ለመግለጽ ነው። ይህ አዲስ ኪዳን ማህበር ከሚለው ኀሳብ እጅግ ያነሰ ነው። የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ቤተ ሰብ ነበረች።

የጋራ ፍላጎት ባስተሳሰራቸው ሰዎች ቡድንና በቤተ ሰብ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ልዩነቱ ብዙ ነገር ነው። የአንድ እግር ኳስ ቡድን ደጋፊ ስለሆናችሁ ብቻ አንድ ሰው የቤት ኪራያችሁን ወይም አስቤዛችሁን እንዲከፍልላችሁ ትጠብቃላችሁ? ተመሳሳይ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካይ ስለመረጣችሁ ወይም ገንዘብ ለመሰብሰብ ተብሎ በተዘጋጀ የአምስት ኪሎ ሜትር ሩጫ ስለተሳተፋችሁ ብቻ አንድ ሰው ስራ እንዲቀጥራችሁ ወይም መኪናችሁን እንዲጠግንላችሁ ትፈልጋላችሁ? በርግጥ አይደለም። ከቤተ ሰብ ግን ድጋፍ *ትጠብቃላችሁ*፤ ወይም ቢያንስ የደም ትስስር ያለው ቤተ ሰብ በዚህ መልኩ እንዲሰራ ይጠበቃል።

የመጀመሪያዉ የሐዋሪያት ቤተክርስቲያን ያንን ነበር የምትመስለው። እነሆ ተመልከቷት፡-

> ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ፣ በዚያም ቀን ሶስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ፤ በሐዋሪያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራንም በመቁረስ በጸሎትም ይተጉ ነበር። ነገር ግን በሰው ሁሉ ፍርሃት ሆነ፤ በሐዋሪያትም እጅ ብዙ ድንቅና ምልክት ተደረገ። ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ፤ ያለቸውንም ሁሉ አንድነት አደረጉ። መሬታቸውንና ጥሪታቸውን እየሸጡ ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉት ነበር። በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቆረሱ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር። እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር (ሐዋ 2፥41-47)።

ይኼ ምንባብ የሚገልጠው ኮሚዩኒዝም ወይም ሶሻሊዝም አይደለም። የሆነ አንዳች ፖለቲካዊ ሥርዓትን እያብራራም። በምንባቡ ውስጥ ስለመንግስት ወይም በዚያ መልኩ እንድትንቀሳቀስ ያየነውን ባሕርይ ለማምጣት ከሀገር የተሰጠ መመሪያ የለም። ሙሉ በሙሉ በፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ነው። ምንባቡ የሚገልጸው የጤናማና የትክክለኛ ቤተ ሰብ ባሕርይን ነው። ቤተ ሰቦች የአባላቶቻቸውን ፍላጎት ያሟላሉ። ልዩነቱ ይኼኛው ቤተ ሰብ በሺዎች የሚቆጠሩ አባላትን የያዘ ነበር።

ይኼ ደቀመዝሙርት ምን እንደሚሰሩ ገላጭ ምስል ነው። ደቀመዝሙርት ማኅበራቸውን ይንከባከባሉ። ቤተ ሰብ ለአባላቱ እንደሚያደርግ እርስ በርሳቸው ይዋደዳሉ፤ ይደጋገፋሉ። ይኼ ማለት ያላቸውን ሀብት መካፈል ማለት ነው። ለአንዳንድ አማኞች ያ ሀብት ገንዘብ ሲሆን፤ ለሌሎች ምናልባትም ጊዜ ወይም አገልግሎት ወይም ሙያ ማካፈል ሊሆን ይችላል። በመሰረታዊነት፥ ማህበሩ ለማህበሩ አባላት መደረግ ያለበትን ነገር ያደርጋል።

ምናልባትም ብዙ ሰዎች ያሉበት በመሆኑ ይህ ማኅበር እርስ በርሱ እንዴት እንደሚተዋወቅ እያሰባችሁ ይሆን ይሆናል። አማኞች በመቅደስ ይሰበሰቡ ነበር (ነገሩ በተደጋጋሚ ከአይሁድ መሪዎች ጋር ቢያጋጭም ለወንጌል መስፋፋት ጠቃሚ ነበር)። እንዲሁም “ቤት ለቤት” ይገናኛሉ (ሐዋ 2፥46፤ 5፥42)። ይኼ ማለት በኢየሩሳሌም ያለችው የመጀመሪያይቱ “ቤተክርስቲያን” የትናንሽ ማኅበራት ትስስር ነበርች ማለት ነው። የማህበሩ ትንንሽ ቡድኖች ውስጥ ያሉ ሰዎች እርስ በርሳቸው ለመደጋገፍና አዳዲስ አማኞችን እውቅና ለመስጠት ቀዳሚዎች ነበሩ።

እነዚህ ትንንሽ ማህበሮች ለአዳዲስ አማኞች እንደ መግቢያ በር ናቸው። የክርስቲያን ማኅበር ወንጌልን ለተቀበሉ የተፈጠሩ ናቸው። እያንዳንዱ ማህበር፥

አባላታቸውንና በተወሰነ መልኩ ጠቅላላውን የአማኞች ማኅበር ደቀመዝሙር በማድረግ ሂደት ይሳተፋሉ። ይኼ ምን ይመስል ነበር?

መጀመሪያ የሚያደርጉት አዳዲስ አማኞችን የማጥመቅ ሥራ ነው (ሐዋ 2፥41፤ 8፥12-13፤ 10፥ 47-48፤ 16፥15)። ጥምቀት ከክርስቶስ ጋር አንድ እንደ ሆኑና ተካታዮቹ እንደሆኑ ለመመስከር በማህበሩ ፊት የሚፈጸም ተግባር ነው (ለምስክር ይሆኑ ዘንድ ሌሎች የማህበሩ አባላት ይታደማሉ)። ጥምቀት ብዙ ነገሮችን ያመለክታል። ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል በፈጸመው ሥራ ኃጢአትህ ይቅር ተብሎልሃል የሚል እና አሁን አዲስ ሕይወት አግኝተሃል የሚለው ከእነዚህ መካከል ናቸው (ሮሜ 6፥1-4፤ 2ቆሮ 5፥17)። ወደ ማኅበሩ ሕይወት ለመግባት ጥምቀት የመጀመሪያው እርምጃ ነው። ተጠማቂዎቹ በጥምቀታቸው በክርስቶስ ማመናቸውን ሲያረግጡ፤ ምስክሮቹ ደግሞ የመሰጠታቸውን እውነት ያስረግጣሉ።

የአማኝ ማህበሮች በሚገናኙበት ጊዜ ማን ምን እንደሚያስፈልገው ይለያሉ። በትንሽ ማኅበራቸው ውስጥ ያሉትን አስፈልጎቶች ማሟላት ከቻሉ ያደርጉታል። ይኼ የሌሎችን ፍላጎት ማሟላት ኢየሱስን እንዲመስሉ ያደርጋቸዋል። እርዳታ ያገኙት ደግሞ “በህይወት እያሉ አሁኑኑ” እንደ ኢየሱስ መኖር ምን ማለት መሆኑን ተማሩ ማለት ነው። በትንንሽ ማህበራት ውስጥ ያለው አስፈልጎት ከማህበሩ አቅም በላይ ሲሆን ሰፊው የአማኙ ቤተ ሰብ ለድጋፍ ዝግጁ ነው። ስለዚህ በኢየሩሳሌም የተጀመረችውን እያደገች ያለች ቤተክርስቲያን መሪዎች የነበሩት ሐዋርያት ማለትም የኢየሱስ የመጀመሪያ ደቀ መዛሙርት “በየዕለቱ በሚከናወነው ምግብ የማደል አሠራር ላይ” ረዳቶችን (ዲያቆናትን) በማኅበሩ ላይ ይሾሙ ነበር (ሐዋ 6፥1-7 አ.መ.ት)።

ይህን በተመለከቱ አንዱ የጥንቷ ቤተክርስቲያን ልማድ የጌታን ሞትና ትንሣኤ ለማስታወስ “የጌታ እራት” ድግስ ማሰናዳት ነበር (1ቆሮ 11፥17-34)። “የጌታ እራት” ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ሥጋውንና ደሙን በቅርቡ እንደሚሰጣቸው የተናገረበትን የመጨረሻ እራት የሚያስታውሱበት ሥርዐት ነው። ኢየሱስ ህይወቱን አሳልፎ መስጠቱ የአዲስ ኪዳን ተስፋ ፍጻሜ እንደሆነ ነግሯቸው ነበር (ሉቃ 22፥30)። በጌታ እራት ድግስ ላይ የተሰጠው ማብራሪያ ይህንኑ ይገልጻል (1ቆሮ 11፥25)። የጌታ እራት ኢየሱስ ያደረገውን ሥራ ማሰቢያ መንገድ ነው። ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ “ለመታሰቢያዬ አድርጉት” ብሎ ነበር (1ቆሮ 11፥24-25)። በተጨማሪም በአማኙ ማኅበር ውስጥ ያለው ደሃ ትክክለኛ እንክብካቤ እያገኘ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ሌላ መንገድም ነበር፡፡

*ደቀመዝሙረት ኅብረት ያደርጋሉ*

"ኅብረት" የአማኙን ማኅበረሰብ ድርጊት ለመግለጽ የዋለ የአዲስ ኪዳን ቃል ነው። አንዱ አንዱን መንከባከብ የመጽሐፍ ቅዱሳዊው ኅብረት አካል ነው፤ ምክንያቱም አማኞች ሲሰበሰቡ  አስፈልጎቶችን ያያሉ፥ ያሟላሉም። ይኼን ካልን፤ ደቀመዛሙርት የሚያድረጓቸው ሌሎች ነገሮችን ከማየታችን በፊት ስለ ኅብረት አጭር ውይይት ማድረግ ግድ ይለናል።

ዛሬ ዛሬ ብዙ አማኞች "ኅብረት"ን የጋራ ደስታ ጊዜ ከማሳለፍ ጋር ያስተሳስሩታል። በርግጥ በጋራ መደሰት ግንኙነትን ያጠናክራል። ከሰው ጋር አብሮ መሆን የጋራ ትስስር ይገነባል። ነገር ግን ደቀመዝሙር መሆንን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱሳዊው ኅብረት ያ አይደለም።

በጋራ ተሰባስቦ የደስታ ጊዜ በማሳለፍና በመጽሐፍ ቅዱሳዊው ኅብረት መካከል ያለው መሠረታዊ ልዩነት ኅብረት አብሮ ጊዜ ማሳለፍ ብቻ አለመሆኑ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊው ኅብረት ዓላማ ተኮር ነው።

የኅብረት የላቀ ግቡ "የክርስቶስ ልብ ይኖረን" ዘንድ በኢየሱስ ዙሪያ "አንድ ሀሳብ" እንዲኖረን ነው። በሌላ ቋንቋ የኅብረት ግቡ ደቀ መዝሙርነት ነው። እነዚህ ከፊልጵስዩስ መጽሐፍ የተወሰዱ ጥቅሶች ይህንን ይገልጹልናል፡-

> ይሁን እንጂ መጥቼ ባያችሁ ወይም ብርቅ በአንድ ልብ ስለ ወንጌል ሃይማኖት አብራችሁ እየተጋደላችሁ በአንድ መንፈስ እንድትቆሙ ስለ ኑሮአችሁ እሰማ ዘንድ ለክርስቶስ ወንጌል እንደሚገባ ኑሩ (ፊል 1፥ 27)።
>
> በክርስቶስ አንዳች ምክር ቢሆን የፍቅር መጽናናት ቢሆን የመንፈስ ኅብረት ቢሆን ምህረትና ርኅራኄ ቢሆኑ በአንድ አሳብ ተስማሙ በአንድ ፍቅር አንድም ልብ አንድም አሳብ ይሁንላችሁ...በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን (ፊል 2፥1-2፤ 5)።

የኢየሱስ ልብ አለን ማለት እና እንደ አማኝ ማህበረሰብ በአንድ ልብ መሆን ማለት ምን ማለት ነው? እስከ መጨረሻው ዝርዝር ጉዳይ ድረስ እያንዳንዱ አማኝ ተመሳሳይ ነገር ማመን አለበት ማለት ነው? ፈጽሞ። መጽሐፍ ቅዱስ አንድነትን እንጂ አንድ አይነትነትን አያወራም። "በአንድ አሳብ" መሆን የሚለውን የምንረዳበት የተሻለ መንገድ እያንዳንዱ የማኅበር አባል ወደ አንድ ግብ ለመድረስ ይጥራል ማለት ነው፤ ይህም ኢየሱስን ለመምሰል። ክርስቶስን ለመምስል ባለው

ሩጫና እንደ አማኝ አብሮ በማህበር የመኖር ግቡ ህብራዊ መሆን እንጂ አንድ አይነት መሆን ማለት አይደለም።

የጥንቷ ቤተክርስቲያን አማኞች ወደዚያ ግብ ለመድረስ አያሌ ነገሮችን ይከውኑ ነበር። ይጸልያሉ፣ ይፆማሉ፣ ያመልካሉ ደግሞም ቅዱስ ቃሉን ያጠናሉ። እነዚህን ተግባራት ደቀመዛሙርት በግልም ሆነ በማህበር የሚያከናውኗቸው በመሆናቸው፥ ከዚህ በመቀጠል እያንዳንዳቸውን በተናጠል እናያቸዋለን።

*ደቀ መዛሙርት ይጸልያሉ*

በአጭር ቃል ጸሎት ማለት *ለእግዚአብሔር መናገር* ማለት ነው። ያ ደግሞ ማሰብን ይጠይቃል። የምናስብውን ሁሉ እግዚአብሔር አስቀድሞ አያውቅም? ያውቃል። ታዲያ ለምን እንጸልያን? ጸሎት የሚደረገው ለእግዚአብሔር መረጃ ለማቅረብ አይደለም። ጸሎት የእግዚአብሔር ጥገኞች መሆናችንን ለእግዚአብሔርም ሆነ ለሌሎች ማሳያ መንገድ ነው። ጸሎት በራሳችን እንደማንደገፍ፣ ወይም ራሳችን ለራሳችን መፍትሄ ሰጪዎች መሆን ያለመቻላችንን ማሳያና እግዚአብሔር እንዲሰራ እየጠየቅን መሆኑን መግለጫ መንገድ ነው። ጸሎት በእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ መደገፋችንንና ደህንነታችንም በእሱ ብቻ መሆኑን ያሳያል። በዛ መልኩ ጸሎት አምልኮ ነው። በቡድን የሚደርግ ጸሎትም እንዲሁ ነው።

በሉቃስ 11፥1 ላይ ደቀመዛሙርቱ የዮሐንስንና ደቀ መዛሙርቱን ዋቢ በመጥራት ኢየሱስን "ጌታ ሆይ ዮሐንስ ደቀመዛሙርቱን እንዳስተማረ እንጸልይ ዘንድ አስተምረን" አሉት። የኢየሱስ ምላሽ የዛሬውን "የጌታ ጸሎት" የተሰኘው ታዋቂ ጸሎት ነበር (ሉቃ 11፥2-4፤ ማቴ 6፥9-15)። ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ምን አይነት ቃላት እየደጋገሙ መጸለይ እንዳለባቸው አለማስተማሩን ማስተዋል ጠቃሚ ነው። ይልቁንም ስትጸልዩ "እንዲህ ጸልዩ" (ማቴ 9፥9) ነበር ያላቸው። የጸሎት ሞዴል እየሰጣቸው ነበር። ለእግዚአብሔር ለመናገር ቀመር ወይም ልዩ ቃላትን መጠቀም አያስፈልግም። *ብቻ* ለእግዚአብሔር እንናገር። በተጨማሪም ጸሎት ለታይታም የሚደረግ አይደለም (ሉቃ 18፥9-14)።

በጌታችን ጸሎት ውስጥ እግዚአብሔር ቀድሞውኑ የማያውቀው አንዳች ነገር የለም። ደግሞም ጸሎት በእግዚአብሔር እውቀት ላይ የጎደለውን ክፍተት መሙያ መንገድ አይደለም። ይልቁን የጌታ ጸሎት ከአምልኮና እግዚአብሔርን ከማክብር ጋር ("ስምህ ይቀደስ")፥ ፈቃዱን ከመታዘዝ ጋር ("ፈቃድህ... ይሁን)፥ ከይቅርታ ጋር ("እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን")፥ እና ከፈተናና ከክፉ ሁሉ ከመዳን ጋር ("ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን") የተሳሰረ ነው። ጸሎት ልባችንን የሕይወታችን ጌታ ከሆነው

ከእግዚአብሔር ጋር ለማቀናጀትና በእርሱ ላይ ጥገኛ የሆነ አመለካከት ለመገንባት የተቀረጸ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የግልም ሆነ የጉባኤ ጸሎቶች የያዘ ነው። እነዚህን ጸሎቶች ስናነበ፥ ጸሎት እንደ ቁጣ፣ ሀዘን፣ ፍቅር የመሳሰሉ ስሜቶቻችንን በእግዚአብሔር ፊት የምናፈስበት መንገድ ነው። ያንን ስናደርግ እግዚአብሔር (ስለ እኛ የማያውቀውን) አዲስ ነገር እየተማረ አይደለም። እኛ ግን ለእርሱ መገዛትን፣ እርሱ የተሻለውን የሚያውቅልንና መልካም መሆኑን፣ ለእርዳታ ወደ እርሱ የመጣራትን አስፈላጊነት እንማራን። ኢየሱስም እንዳለው እግዚአብሔር ሰፊ እንደሆነው እንደ ፍቃዱ ጥበብ ጸሎትን ይመልሳል። በሌላ ቋንቋ የእግዚአብሔር ምላሽ ሁል ጊዜም የፈለግነውን ላይሆን ይችላል ግን እግዚአብሔር ከሁሉ የሚበልጠውን ታላቁን እቅዱን ለመፈጸም በሰዎች ልምምድና ባሕርይ ውስጥ የሚከናወኑ ነገሮችን ሁሉ ያውቃል። እግዚአብሔር ባልተጠበቀ መንገድም ይመልሳል።

በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኙት ጸሎቶች ራስን ማዕከል ያደረጉም አይደሉም። ይዘታቸው ሌሎችን መባረክ ወይም ለሌሎች ምህረት መጠየቅን ማዕከል ያደረጉ ናቸው። በተለምዶ የጳውሎስ ደብዳቤዎች ለተጻፈላቸው ሰዎች የተጸለዩ ጸሎቶችን ያካተቱ ናቸው። ጸሎት ሁልጊዜ ወይም በአብዛኛው የራሳችንን ፍላጎትና ጉድለታችንን ስለመግለጽ አይደለም።

ኢየሱስ በተደጋጋሚ ይጸልይ ነበር። እርሱ ጸሎት ያለማቋረጥ መደረግ እንዳለበት ያስተማረውን ትምህርቱን ይተገብር ነበር (ቆላ 4፥26፤ ሉቃ 18፥1-8)። ኢየሱስ ለሁሉም ጸሎቶቹ መልስ አላገኘም፤ የዘወትር ትኩረቱ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲፈጸም በመሆኑ (ማቴ 26፥36-46) ያንን ተቀብሎት ነበር። ይኼ ስለጸሎት እጅግ አስፈላጊ ማንቂያ ነው። ኢየሱስ ስንጸልይ እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንደሚመልስ አስተምሯል (ሉቃ 11፥9-13) ነገር ግን እርሱን ሳንታዘዝ ወይም ከገዛ ፍቃዱ ጋር ሳንስማማ፥ እግዚአብሔር መሻታችንን ሁሉ በፈለግንበት መንገድ ያደርጋል ብለን ማስብ የለብንም(ያዕ 4፥3፤ 1ዮሐ 3፥22፤ 5፥14)።

*ደቀመዛሙርት ይፆማሉ*

ምናልባትም *"ፆም"* ለብዙ አንባቢዎች እንግዳ ሊሆን ይችላል። በአጠቃላይ አንድን ነገር *መፆም* ማለት፤ ከዚያ ነገር *መራቅ* ማለት ነው። ከምግብ *"መፆም"* ማለት አለመብላት ማለት ነው። ሁል ጊዜ ባይሆንም፥ በአብዛኛው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናየው ይኼን ዓየነት ፆም ነው። ኢየሱስ ፆሚል (ማቴ 4፥2)። ደቀመዛሙርት ምሳሌውን ተከትለው እንደሚፆሙ ጠብቋል፤ እንዲሁም ሲፆሙ

እንደ ግብዞች እንዳይሆኑ አስጠንቅቋቸዋል (ማቴ 6፥16-18)። ፆም በእናንተና እግዚአብሔር መካከል የሚደረግ እንጂ የሌሎችን ትኩረት ወደ እኛ መሳቢያ አይደለም።

ፆም እንዲሁ ከምግብ ራስን ማቀብ ብቻ አይደለም። በየትኛውም በፈለጋችሁት መልኩ፥ ከየትኛውም ነገር መፆም ትችላላችሁ። ኢየሱስ የነገረን ክብደት የመቀነስ ዘዴ አይደለም። እርሱ ሲፆምና ስለ ፆም ሲያወራ ከዚህ የተለየ ነገር እያሰበ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ፆሞችን የዘገበ ቢሆንም ልዩ የሆነ የፆም መመሪያ ግን አልሰጠም። ሐዋሪያው ጳውሎስ የትዳር አጋሮች ራሳቸውን ለተለየ ጸሎት በመስጠት ከወሲብ ሊፆሙ እንደሚችሉ አውስቶ ነበር (1ቆሮ 7፥1-5)።

ግን ለምን እንደዚያ ይደረግ? ባለ ትዳሮች ተስማምተው ለተወሰነ ጊዜ ከወሲብ መታቀባቸውን የሚያወሳው በ1ቆሮ 7፥5 የተጻፉት የጳውሎስ ቃላት ፍንጭ ይሰጡናል፡-“ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ።” ፆም በጸሎት ላይ ትኩረት እንድናደርግ የተቀረጸ መንፈሳዊ ልምምድ ነው። ይኼንን እንዴት ያደርጋል? ምናልባት ይህ ምሳሌ ሳያግዘን አይቀርም። ለአንድ ቀን ምግብ ለመፆም ብትወስኑ፣ ረሀብ ሲሞረሞራችሁ መጸለይ እንዳለባችሁ ትዝ ይላችኋል። ፆም ለመፆም ወደ ወሰነችሁበት ጉዳይ እየጎተጎተ የሚመራችሁ አስታዋሽ መሳሪያ ነው።

ስለ ፆም ማሰቢያው ሌላ መንገድ ከጸሎት ወይም በአጠቃላይ ከእግዚአብሔር ጋር ካለን አካሄድ የሚያደናቅፉን ነገሮች ምንድን ናቸው ብሎ መጠየቅ ነው። መልሱ ስልካችን፣ ቴሌቪዥናችን ወይም ለመዝናናት የምናደርገው የትርፍ ጊዜ ልማድ ሊሆን ይችላል። ትኩረታችንን ወደ ጸሎትና ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ፥ እነዚህን ሁሉ ለጊዜው መተው (መፆም) እንችላለን።

የመጀመሪያቱ ቤተክርስቲያን ማህበር በጋራ ጸሎት ላይ ትኩረት ለማድረግ ይፆሙ ነበር (ሐዋ 13፥1-3፤ 14፥23)። በብሉይ ኪዳን፥ የማህበረሰብ የጋራ ፆም እንደ ሕዝብ ስለ ኃጢአት በጋራ የመጸጸትና የንስሃ ማሳያ ነበር (ኤር 36፥6፤ ኢዩ 2፥12)።

*ደቀመዛሙርት ያመልካሉ*

አምልኮ፤ ለመተርጎም ወይም ለመረዳት ቀላል እንደሆነ ታስቡ ይሆናል። መልካም፤ ግን ነውም አይደለምም። አብዛኛውን ጊዜ አምልኮን በቤተክርስቲያን ከሚደረጉ አገልግሎቶች በተለይም ከሙዚቃ ጋር እናያይዛለን። ያ አምልኮ አይደለም፥ ምንም እንኳ ዝማሬ እና ሙዚቃ በአማኞች ስብሰባ ውስጥ ቦታ

ቢኖራቸውም፥ መጽሐፍ ቅዱስ ቢያንስ አምልኮን በዚያ መልክ አይተረጉመውም (ኤፌ 5፥19፤ ቆላ 3፥16)። ሌላው በባህላችን ያለ ዝንባሌ፥ አምልኮን ውስጠታዊ ተጨባጭ ያልሆነ ስሜትና ልምምድ አድርጎ መውሰድ ነው። ይኼም አምልኮ አይደለም። ስለጉዳዩ የሚያወሱን አያሌ ምንባባት ቢኖሩም ሁለቱን እንያቸው፡-

> እንግዲህ ወንድሞቼ ሆይ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መስዋዕት አድርጋሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፤ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ እሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍፁምም የሆነውን ነገር ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ (ሮሜ 12፥1-2)።

> ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኖአል፤ አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ይሻልና (ዮሐ 4፥23)

የመጀመርያውን ምንባብ፥ የተቀደሰ ሕይወት ስለመኖር በተወያየንበት ክፍል አንስተነዋል። እግዚአብሔርን እንዴት እናመልካለን? እንደ ኢየሱስ በመኖር። አለምን አትምሰሉ፥ ማለትም ምኞቱንና የራስ ማርካት ሩጫውን። ያ አምልኮ ነው። ስለዚህ እውነተኛ አምልኮ የልብ ጉዳይ ነው።

ከሚከተለው ምክንያት የተነሣ ሁለተኛው ምንባብ አስደናቂ ነው። ኢየሱስ ለሴቲቱ የነገራት እግዚአብሔር ሰዎች እንዲያመልኩት መፈለጉን ነው። ስለዚህ አምልኮ ከእኛ የመነጨ ነገር አይደለም። እኛ ለእግዚአብሔር መልካምነትና ፍቅር ምላሽ እንድንሰጥ የተጋበዝን ነን። *እንዴት* እና *የት* የሚለው ሊለያይ ይችላል። ይህንን ለብቻችን በሙዚቃ ወይ ያለ ሙዚቃ፥ በቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ወይ ከዚያ ውጭ ልናደርግ እችላለን። ከሌሎች አማኞች ጋር በኅብረትም ልናደርገው እንችላለን።

አማኞች ለህብረት በሚሰበሰቡበት ጊዜ፥ እርስ በእርሳቸው “ ለፍቅርና ለመልካም ሥራ” ይነቃቃሉ (ዕብ 1፥24-25)። በሌላ ቋንቋ፥ ኢየሱስን ለመምሰል ማለትም ለመንፈሳዊ አምልኮ አንዱ ሌላውን ያበረታታል። እግዚአብሔርን ስለ መልካምነቱ፣ ፍቅሩ፣ በሕይወታቸው ላሳየው መግቦታዊ መገኘቱ ያመልኩታል (ሐዋ 2፥46-47፤ ያዕ 5፥13)። ምስጋና ዝማሬንና ሙዚቃን ሊያካትት ይችላል (ማቴ 26፥30፤ ኤፌ 5፥19፤ ቆላ 3፥16) ግን ያለጥርጥር ከተቀደሰ ሕይወት ጋር የተያያዘ ነው “ ...ለክርስቶስ ቀን ተዘጋጅታችሁ ቅኖችና አለ ነውር እንድትሆኑ የሚሻለውን ነገር ፈትናችሁ ትወዱ ዘንድ ፍቅራችሁ በእውቀትና በማስተዋል ሁሉ ከፊት ይልቅ እያደገ እንዲበዛ ይህን እጸልያለሁ” (ፊል 1፥10-11)።

“የመንፈሳዊ አምልኳችን እውነታ” በመሠረታዊነት ከኑሯችን ጋር የተሳሰረ የመሆኑን ዕይታ ማጣት የለብንም (ሮሜ 1፥1-2)። አምልኮ በቤታችን ወይም በቤተክርስቲያን ለሰላሳ ደቂቃ የምናድረርገው ልምምድ አይደለም። አምልኮ በእግዚአብሔር የተቃኘ እና ወደ እግዚአብሔር ያቀና ሕይወት መኖር ነው።

*ደቀ መዛሙርት ኃጢአትን ይናዘዛሉ፤ ይቅርታንም ከእግዚአብሔር ይቀበላሉ*

ከክርስቶስ ጋር ጉዞ እንደ ጀመሩ ደቀመዛሙርት ወዲያውኑ አጥብቀው ሊያውቁት የሚገባ ጉዳይ ቢኖር እንደሚወድቁ ነው። ማናችንም እንደ ኢየሱስ ኃጢአት አልባ አይደለንም፤ ለመሆንም ተስፋ አናደርግም (2ቆሮ 5፥21፤ 1ጴጥ 2፥21-22፤ 1ዮሐ 3፥5)። በዚህ ነጥብ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ ነው። ደቀ መዛሙርት ኃጢአት አድርገዋል (ማር 14፥30፣ 68፣ 72)። ከደቀመዛሙርቱ አንዱ የሆነው ዮሐንስ በኋለኛው ሕይወቱ እንደሚከተለው ጽፎ ነበር፡-

> ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን፤ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል። ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን እውነትም በእኛ ውስጥ የለም።በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው። ኃጢአትን አላደረግንም ብንል ሐሰተኛ እናደርገዋለን ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም (1ዮሐ 1፥7-10)።

በእግዚአብሔር ቤተ ሰብ ውስጥ የመሆናችን ምክንያቱ የእኛ ብቃት ያለመሆኑን ማወቅ በርግጥ አስደናቂ ነው። መልካሙ ስራችን እግዚአብሔርን የእኛ ባለዕዳ አያደርገውም። እግዚአብሔር የዘላለምን ሕይወት የሰጠን እኛ አለን ብለን በምናስበው መልካም ነገር ባለ እዳ አድርገነው አይደለም። የብቃታችን መኖር ሆነ ማነስ ከእኛ እንዲርቅ አላደረገውም። እግዚአብሔር “ገና ኀጢአተኞች ሳለን ወዶናል”(ሮሜ 5፥8)። በመሆኑም ድነትን በምግባራዊ ፍፁምነት ባለማግኘታችን እንዲሁ በምግባራዊ ዕድፈት አናጣውም።

ፍጹም ያለመሆናችንን በመገንዘብ፥ እውነተኛ የኢየሱስ ደቀመዝሙር በእግዚአብሔር መልካምነትና ፍቅር ላይ አትኩሮ መኖር አለበት። ከዮሐንስ መልዕክት የጠቀስነውን ምንባብ እንደገና ተመልከቱ። ይኼ ምንባብ እግዚአብሔርን ከማክበር በምንጎድልበት ጊዜ፣ ክርስቶስን ለመምሰል *የማይጠቅም* ነገር በምንሰራበት ጊዜ ወይም ክርስቶስን ለመምሰል *የሚጠቅም* ነገር በማንሰራበት ጊዜ፥ ማድረግ ስላለብን ነገር በትክክል ይነግረናል፡- “ኃጢአታችንን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።”

ኃጢአት ስናደርግና ስንወድቅ እውነቱን ማመን አለብን። ኑዛዜ ማለት ያ ነው። ኃጢአታችንን መደበቅ፣ ሰበብ መስጠት ወይም በአመክንዩ ማለፍ የለብንም። እግዚአብሔር ኅጢአታችንን እንድናምን ይፈልጋል። ለምን? መዋረድ (ትሁት መሆን) አለብን። ድነት በስራችን የተገባን ሳይሆን ኢየሱስ የፈጸመው እንደሆነ ማስታወስ ይኖርብናል። ኑዛዜ ከኢየሱስ የተነሣ የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆንን እውቅና ይሰጣል። ኅጢአታችን ከእግዚአብሔር ሊለየን አይችልም፤ ከእግዚአብሔር ቤተ ሰብም አንባረርም (ሮሜ 8፥31-19)። እግዚአብሔር በወንጌል ከማመናችን በፊት በደለኞች መሆናችንን ያውቃል። ድካማችን አያስገርመውም። ኃጢአታችንንም ስለ እኛ ያለውን ስሜት አይለውጠውም።

ታዲያ ስለ ኅጢአት ለምን ግድ የለናል የሚል ጥያቄ መነሳት አለበት። የአዲስ ኪዳን ደቀመዛሙርት ያ ዝንባሌ ያላቸው ሰዎች ገጥመዋቸዋል። ይህንኑ ጉዳይ ሐዋሪያው ጳውሎስ ለሮሜ አማኞች በጻፈው ደብዳቤ እንደሚከተለው አስፍሯል፡-

> እንግዲህ ም እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? አይደለም። ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደፊት እንዴት አድርገን በእርሱ አንኖራለን? ... እንግዲህ ለምኞቱ እንድትታዘዙ በሚሞት ስጋችሁ ኃጢአት አይንገስ፣ ብልቶቻችሁንም የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ፤ ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ፤ ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ። ኃጢአት አይገዛችሁምና ፤ ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁምና። እንግዲህ ምን ይሁን? ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች ስላይደለን ኃጢአትን እንስራን? አይደለም። ለመታዘዝ ባሪያዎች እንድትሆኑ ራሳችሁን ለሚታቀርቡለት ለእርሱ ለምትታዘዙለት ባሪያዎች እንደሆናችሁ ለጽድቅ የመታዘዝ ባሪያዎች ናችሁ (ሮሜ 6፥1-2፤ 12-16)።

መጽሐፍ ቅዱስ “በፍጹም! ኅጢአት እንዳታደርጉ አሊያ እግዚአብሔር ከዚህ በኋላ አይወዳችሁም” እንደማይል አስተውሉ። ይልቁን ትኩረቱ ራስን ወደሚያውደም እስራት ያለመመለስ ላይ ነው። በመሆኑም በአንድ መልኩ ኃጢአት እናደርጋለን፤ በሌላ መልኩ ደግሞ ኃጢአት ማድርግ የለብንም። ይህን ትግል፥ሐዋርያው ጳውሎስ በሚገባ ያውቀዋል(ሮሜ 7፥7-15)፤ ነገር ግን ስመ ጥር የኢየሱስ ተከታይ ነበር። አዲስ ኪዳን በተደጋጋሚ በውስጣችን ስላለው ጦርነት ያነቃናል። ልባችን ኢየሱስን መከተል ይፈልጋል፤ ፍጹም ያልሆነው ማንነታችን ግን በኑሯችን ግላዊ-እርካታና እንደኝነትን ይፈልጋል(1ጴጥ 2፥11፤ ያዕ 4፥1)።

ኢየሱስን በመከተል ስንኖር፥ "ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ሂሳብ አውራርድ" የሚለውን አባባል ማስተዋል ጥሩ ነው። ሀሳቡ ስንወድቅ፥ኀጢአታችንን ቶሎ መናዘዝና ስለ ይቅርታው እግዚአብሔርን ማመስገን እንዳለብን የሚያሳይ ነው። ኃጢአታችን ኢየሱስን ያስከፈለውን ዋጋ ማሰብ ይገባናል። "ገና ኀጢአተኞች ሳለን" (ሮሜ 5፥8)፥ ወንድሞቹና እህቶቹ እንድንሆን ወደ መስቀል ስለመሄዱ በማመስገን፥ ታማኝ በሆነ ፍቅር በመፅናት ልንከተለው ይገባል።

*ደቀመዛሙርት መጽሐፍ ቅዱሰ ያጠናሉ*

በቀድሞዋ ቤተክርስቲያን አማኞች የሐዋሪያትን ትምህርት ይሰማሉ፣ ደግሞም ቃሉን ያጠናሉ። ጳውሎስና ሌሎች የተላኩ ሐዋሪያት ቤተክርስያንን በጀመሩባቸው ቦታዎች ሁሉ ይህንኑ አድርገዋል (ሐዋ 2፥42፤ 4፥2፤ 5፥ 42፤ 17፥10-11፤ 18፥11፤ 20፥20)። በአዲስ ኪዳን ዘመን ብዙ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂ ስለሌላቸው፥ መጽሐፍ ቅዱስን የሚማሩበት የተለመደው ዘዴ ይህ ነው። በተጨማሪም አብዛኞቹ አማኞች ማንበብ አይችሉም ነበር። ምንም እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ በእጃችን ቢኖር፥ በተማረም ባህል ውስጥ እየኖርን ቢሆንም፥ ቃሉን በጋራ ከመማር ብዙ ነገር እንጠቀማለን።

ኢየሱስን ለመከተል ቃሉን መማር አስፈላጊ ነው። ካለሆነ ስለ ኃጢአት (ማለትም መወገድ ስላለባቸው ዝንባሌዎችና ባህሪያት) እና በመንፈስ ስለተሞላ ሕይወት (ማለትም መኖር ስለሚጠበቅብን ሕይወት) እንዴት ማወቅ እንችላለን? ቃሉ "ፊተኛ ኑሮአችሁን እያሰባችሁ እንደሚያታልል ምኞት የሚጣፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ፥ በአእምሮአችሁም መንፈስ ታደሱ፥ ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ" (ኤፌ 4፡ 22-24) በማለት ያስተምረናል። ወንጌልን በማመን የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ አባላት ስንሆን፣ ፍሬያማ ሕይወት እንድንኖር ሊያግዘን መንፈስ ቅዱስ አድሮብናል (1 ቆሮ 3፥16-17፤ 6፥19-20፤ 2ቆሮ 6፥16፤ ኤፌ 2፥22)።

> በመንፈስ ብትመሩ ግን ከሕግ በታች አይደላችሁም። የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣዖትን ማምለክ፣ ምዋርት፣ ክርክር፣ ቅንዓት፣ ቁጣ፣ አድመኝነት፣ መለያየት፣ መናፍቅነት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ ዘፋኝነት፣ ይህንንም የሚመስል ነው። አስቀድሜ እንዳልሁ እንደነዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግስት አይወርሱም። የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት ነው።እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም። የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱ ጋር ሰቀሉ (ገላ 5፡ 18-24)።

ደቀመዛሙርት ቃሉን ይማራሉ የተማሩትን በኑሮአቸው ይተገብራሉ። ይኼ ኢየሱስ እግዚአብሔርን መውደዱን ያሳየበት መንገድ ነው—የእግዚአብሔርን ፍቃድ ታዘዘ። ኅብረት ያንን በማድረግ ሂደት ውስጥ ትርጉም ያለው ድጋፍ ይሰጣል። ኅብረት ውስጥ ኢየሱስን ለአመታት ከተከተሉ የበሰሉ አማኞች ጋር እንገናኛለን። “አሮጌውን ሰው ማስወገድና አዲሱን ሰው መልበስን” ሲማሩ ሕይወታቸው እንዴት እንደተለወጠ ከእነርሱ መማር እንችላለን። ኢየሱስን በመምሰል ፍለጋችን ውስጥ በሚገጥመን ትግል ማበረታቻ ለማግኘት ወደ እነርሱ መሄድ እንችላለን። የእግዚአብሔርን ፍቅርና ይቅርታ ያስታውሱናል። እያንዳንዱ ክርስቲያን ከኀጢአት ለመራቅና መልካሙን ለማድረግ ትግል እንዳለበት ያውቃሉ(1ዮሐ 1፥ 5-10)። ሐዋሪያቶች እንኳ መልካም የሆነውን ለማድረግ ከኀጢአት ጋር ታግለዋል (ሮሜ 7፥7-25፤ ገላ 2፥11-14)። የክርስቶስን ምሳሌ በመከተል ፍለጋችን ውስጥ ኅብረት ማለት ተጨማሪ ተጠያቂነት፣ አብሮነት እና መበረታታት ነው፡፡

*ደቀመዛሙርት መከራ ይቀበላሉ*

ይኼ ግርምትን የሚፈጥርባችሁ ነጥብ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ይህ በአዲስ ኪዳን በግልጽ ተቀምጧል። ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ የሚከተለውን ብሏቸው ነበር፡-

> ዓለም ቢጠላችሁ ከእናንተ በፊት እኔን እንደጠላኝ እውቁ። ከዓለምስ ብትሆኑ ዓለም የራሱ የሆነውን ይወድ ነበር። ነገር ግን እኔ ከዓለም መረጥኋችሁ እንጂ ከዓለም ስለ አይደላችሁ ስለዚህ ዓለም ይጠላችኋል። ባሪያ ከጌታው አይበልጥም ብዬ የነገርኋችሁን ቃል አስቡ። እኔን አሳደውኝ እንደሆኑ እናንተንም ደግሞ ያሳድዱአችኋል፤ ቃሌን ጠብቀው እንደሆኑ ደግሞ ቃላችሁን ይጠብቃሉ (ዮሐ 15፥18-20)።

የእምነት ታማኝነት የሚፈተነው እዚህ ጋ ነው። በአኗኗራችን የተለወጠ ልብ ይኖረን ዘንድ መማር አንድ ነገር ነው፤ ነገር ግን ኢየሱስን መከተልና ስለዚያም መከራን መቀበል ፈጽሞ ሌላ ነገር ነው። ሐዋሪያት ኢየሱስን ስለ መከተላቸው ተሰቃይተዋል (ሐዋ 5፥42፤ 9፥16፤ 21፥13፤ 2ቆሮ 11፥22-29)። በእምነት መጽናት የአዲስ ኪዳን አንዱ ገጽታ ነው (ሮሜ 8፥17-18፤ 2ቆሮ 1፥ 3-7፤ ፊል 1፥27- 30፤ 1ጴጥ 3፥13-17)። ኢየሱስን መከራ ሲቀበል ያየው፥ ከዋናዎቹ አስራ ሁለት ሐዋሪያት አንዱ የሆነው ጴጥሮስ ስለ እምነቱም ታስሮ ነበር (ሐዋ 12፥1-19። ከመከራ የተነሳ ለተፈናቀሉና ለተበተኑ አማኞች የሚከተለውን ጽፎ ነበር፡-

> ኃጢአት አድርጋችሁ ብትጎሰሙ ብትታገሱ ምን ክብር አለበት? ነገር ግን መልካም አድርጋችሁ መከራን ስትቀበሉ ብትታገሱ ይህ ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ምስጋና ይባዋል። የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፤ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለእናንተ መከራን ተቀብሎአልና። እርሱም ኃጢአት አላደረገም ተንኰልም በአፉ አልተገኘበትም፤ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም መከራን ሲቀበል አልዛተም ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ (1ጴጥ 2፡ 20-23)።

በመከራ ለመጽናት ይህንን ማሰብ አለብን —ወንጌል በሚመጣው ሕይወት በእግዚአብሔር ቤተ ሰብ ውስጥ ዘላለማዊ ሥፍራን እንጂ በዚህ ሕይወት ድሎትን ተስፋ አልገባልንም። ይህ ዓለም እውነተኛው ቤታችን አይደለም።

*ደቀማዛሙርት ሌሎች ደቀመዛሙርትን ያፈራሉ*

እግዚአብሔርንና ባልንጀራን መውደድ፥ እርስ በእርስም መዋደድ ደቀመዝሙር የመሆን እጅግ አስፈላጊው ገጽታ ቢሆንም፥ ደቀመዛሙርት የሚያደርጉት እጅግ አስፈላጊ ተግባር ሌሎችን ደቀመዝሙር ማድረግ ነው። ይኼ ኢየሱስ ወደ አብ ከማረጉ በፊት ለተከታዩቹ የሰጠው ሥራ ነው። "ታላቁ ተልዕኮ" ተብሎ የተጠራውም ከዚያ የተነሣ ነው።

> ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናራቸው፡- **ስልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ።** እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋቹንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው። እነሆ እኔ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ (ማቴ 28፥18-20)።

"አሕዛብን ሁሉ... ደቀመዝሙርት አድርጓቸው።" ያ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ትልቁ ክፍል ነው። አሕዛብን በባርነት የገዙት የልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይላት ስልጣን ከእጃቸው ተወስዷል። እግዚአብሔር ልጆቹና አጋሮቹ የሆኑት የልጁ ደቀመዛሙርት በሁሉም ስፍራ የወንጌልን መልካም ምስራች እንዲያካፍሉ ይፈልጋል። እግዚአብሔር በተቻለ መጠን በርካታ ሰዎች ወደ ቤተ ሰቡ እንዲመጡ ይፈልጋል። ሥራችን መልካሙን የምስራች መናገር፤ የተናገርነውን ቃል በተናገርናቸው ሰዎች መካከል በተግባር መኖር፤ ወንጌል የተቀበሉትን ወደ እግዚአብሔር ቤተ ሰብ ማምጣት እና ይህንኑ ስራ እንዲሰሩ ማስተማር ነው፡፡

ይኼን እንዴት እናደርጋለን? እኛ ወንጌልን ወደ ማመን እንዴት እንደመጣን እናጋራለን። አስገራሚ በሆነ መንገድ ቀላል ነው።

በመጀመሪያ፥ ወንጌልን ከማመናችንና በኢየሱስ የመጣውን የእግዚአብሔር ምህረት ከመቀበላችን በፊት የነበረንን ሕይወት ለሰዎች እናወራለን። ሰዎች ታሪክን በተለይ የሌሎች ሰዎችን ታሪክ መስማት ይወዳሉ። ለምን? ምክንያቱም ሁል ጊዜ ከራሳችን ታሪክ ጋር የሚያያዝ ነገር በሌላው ታሪክ ውስጥ እናገኛለን። ወንጌልን ከመረዳታችሁ በፊት የነበራችሁን ሕይወት ለሌላ ሰው ስታወሩ፥ የሕይወታችሁ አንዳንድ ወይም ብዙው ጉዳዮች ከሚሰማችሁ ሰው ሕይወት ጋር ይመሳሰላል እንዲሁም ይያያዛል።

ሁለተኛ፥ ወንጌልን መስማትና ወንጌልን ማመን ለእናንተ የለውጥ ምክንያት እንደሆነ ንገሯቸው። ብዙውን ጊዜ ይኼ ከኃጢአታችን ይቅርታ ጋር የተገናኘ ነው። እኛ በራሳችንና በሌሎች ካደረግነው በተቃራኒ እግዚአብሔር እንደሚወደንና እንደሚፈልገን፥ ድነትን እንደሰጠን ማወቅ እጅግ አስደናቂ ነው። በመቀጠልም እግዚአብሔር የኃጢአት ይቅርታ በማግኘት ከእርሱ ጋር በዘላለም ሕይወት እንኖር ዘንድ ልጁን እንደላከ –ይኼንንም ከመጀመሪያ ማድረግ እንደፈለገ ተናገሩ።

ሦስተኛ፥ በወንጌል ማመንና የኃጢአትን ይቅርታ ማግኘት፥ በሕይወታችሁ ያሳደረውን መልካም ተጽዕኖ ለሰዎች ተናገሩ። የእግዚአብሔርን ይቅርታ፣ ፍቅርና የዘላለም ሕይወት ተስፋ ማወቅ ምን እንደሚመስል ንገሯቸው። በማንነታችሁና፥ የመኖራችሁን ምክንያት በተመለከተ አመለካከታችሁን እንዴት እንደለወጠው ንገሯቸው። በወንጌል ማመናችሁ ማንነታችሁን እንዴት እንደለወጠው ንገሯቸው።

አንዳንድ ሰዎች ስለ ተለወጠ ልብ ማረጋገጫ ይፈልጋሉ። ይኼ የተለመደ ነው፤ ደግሞም ኢየሱስን እንድንመስል ተጨማሪ ዕድል ነው። ይኼ የተቀደሰ ሕይወት እንድንኖር ከሚያደርጉን ምክንቶች አንዱ ነው። ኢየሱስ ሰዎችን ይወድና ያገለግላቸው ነበር። ሰዎች መወደድ ይፈልጋሉ፥ እውነተኝነትንም በሌሎች ውስጥ ይፈልጋሉ። ለሰዎች ኢየሱስ ቢሆን የሚያደርግላቸውን ነገር ማድረግ ወጤታማ ነገር ነው። ሰዎች ይህንን ያስተውላሉ። ሰው ሲወዳቸውና ሳይወዳቸው ያውቃሉ። ለወንጌል መልእክት ሲባል ከራሳችን ፊት ስናስቀድማቸው ያውቃሉ። ኢየሱስን ሁሉም አላመነውም። ወንጌልንም ለሰዎች ስናካፍል፥ ኢየሱስ እንደተቀበላቸው ብንቀበላቸው፥ ሁሉም ያምናሉ ማለት አይደለም። ነገር ግን፥ ብዙዎች ያምናሉ።

ጸሎት

እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ የእርሱ ቤተ ሰብ እንድንሆን ይጠራናል። ይህንን ካመንን የሚከተለውን ጸሎት አብረን እንጸልይ፡-

> እግዚአብሔር አባታችን ሆይ፥ ስለፍቅርህና ስለምህረትህ እናመሰግንሀለን። ለእኛ ካለህ ጥልቅ ፍቅር የተነሣ፥ ልጅህን በመስቀል ላይ ለእኛ ኀጢአት በምትካችን እንዲሞት ስለላከው እናመሰግንሀልን። ልጅህም ሞትን አሸንፎ በሦስተኛው ቀን እንደተነሣ በአብ ዘንድ እንደተቀመጠ፥ መንፈስ ቅዱስንም እንደላከ የሚናገረውን የምስራች ወንጌል እናምናለን። የኀጢአታችንን ይቅርታ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ስለሰጠኸን እናመሰግናለን። ቤተ ሰብህ ስላደርግከን፥ እስከፍጻሜውም ድረስ ከእጆችህ ማንም ስለማይነጥቀን በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናመሰግንሀለን። ክብርና ምስጋና ሁሉ ለአንተ ይሁን።

## አስፈላጊ ስሞችና ቃላት (የቃላት መፍቻ)

- ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ቃላት በመጽሐፉ ውስጥ የተብራሩትን ሁሉ ያካተቱ አይደሉም። ጐላ ያሉትና ገደም ባለ ጽሁፍ መልክ የተጻፉት በቃላት መፍቻው ተካተዋል።

**አብርሃም**- በኋላ እስራኤላውያን ወይም አይሁድ በሚል ለተጠሩት ሕዝብ ቅደመ አባት ለመሆን እግዚአብሔር የመረጠው ሰው።

**የሐዋሪያት ስራ**- ስለ መጀመሪያው ክርስቲያኖች ታሪክ የሚዘክር የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ።

**አዳምና ሔዋን**- እግዚአብሔር የፈጠራቸው የመጀመሪያዎቹ የሰው ልጆች።

**መላእክት**-እግዚብሔርን የሚያገለግሉና በኢየሱስ ያመኑትን የሚያግዙ ልዕለ-ተፈጥሯዊ ኃይላት። በአማርኛው መልአክ ተብሎ ከዋናው የዕብራይስጥና የግሪክ ቅጂዎች የተመለሰው ቃል ትርጉም “መልእክተኛ” ማለት ነው። ስለዚህ፥ መልአክ የሚለው ቃል ስራን የሚገልጽ ነው። ቃሉም በእግዚአብሔር ሰማያዊ ግዛት አባል የሆነና ከእግዚአብሔር ወደ ሰው መልእክትን ይዞ የሚመጣን ፍጡር ሥራ ገላጭ ነው። ለበለጠ ማብራርያ “የልእለ ተፈጥሮአዊ ቃላት ማጠቃለያን” ተመልከቱ።

**ሐዋርያ**- በግሪክ “የተላከ” ማለት ነው። በአዲስ ኪዳን የተለያዩ ዓይነት ሐዋርያት አሉ።

**ዕርገት**- ከትንሳኤው በኋላ የክርስቶስ ወደ ሰማይ መመለስ።

**አሦራውያን** - ከሰሜናዊ ሜሶፖታሚያ የመጡ የእስራኤል ታሪካዊ ጠላቶች።

**ባቤል** - በደቡብ ሜሶፖታምያ የነበረች ጥንታዊ የባቢሎን ከተማ (የአሁኗ ዘመን ኢራቅ)።

**ባቢሎናውያን**- ከደቡብ ሜሶፖታሚያ የመጡ የእስራኤል ታሪካዊ ጠላቶች።

**አማኝ** - ወንጌልን የተቀበለ፥ ወይም በወንጌል እምነት የጸና ሰው።

**መጽሐፍ ቅዱስ** - በእግዚአብሔር መግቦታዊ ምሪት በተመሩ ሰዎች የተጻፉ የ66 ቅዱሳት መጻሐፍትን የያዘ መጻሐፍ። የመጀመሪያዎቹ 39 መጻሕፍት “ብሉይ

ኪዳን” ተብለው ሲጠሩ፤ ቀሪዎቹ 27 መጻሕፍት “አዲስ ኪዳን” ተብለው ይጠራሉ።

**ክርስቶስ** -“የተቀባ” የሚል ትርጉም ያለው የግሪክ ቃል፤ “መሲህ” ለሚለው የኢየሱስ መጠሪያ አቻ የሆነ ስም።

**ቃል ኪዳን** - በሁለት አካላት መሃል የሚደረግ ስምምነት። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር ቃል ኪዳን በማድረግ ተስፋዎችንና በረከቶችን አጋርቷል። ቃል ኪዳን ቅድመ-ሁኔታ ሊኖረውም ላይኖረውም ይችላል።

**መስቀል** - ኢየሱስ የተገደለበት መንገድ። የሮማ መስቀል ወንጀለኛው ከተሰቃየ በኋላ ትንፋሽ አጥሮት እንዲሞት ያመች ዘንድ ወደ ግራና ቀኝ የተዘረጉ ጉማዶች ያሉት ቀጥ ያለ እንጨት ነው። በአዲስ ኪዳን “መስቀል” በወንጌል በማመን ለሚገኝ ድነት የኃጢአት ዋጋ የተከፈለበትን ስፍራ ያመለክታል።

**ዳዊት**-እግዚአብሔር የዘላለማዊ ንግስና ኪዳን የሰጠው የእስራኤል ሁለተኛ ንጉስ።

**ውድቀት/ደንካራነት** - ኃጢአትና እኩይን የሚያመለክት፤ በአብዛኛው የእኩይ አስተሳሰብ ጥልቀትና ተደጋጋሚ ተግባር የሚያመለክት መጠሪያ።

**ዲያቢሎስ** - ለሰይጣንና ለእባቡ የተሰጠ ሌላ ስም። ለበለጠ ግንዛቤ “የልእለ ተፈጥሮአዊ ቃላት ማጠቃለያን” ይመልከቱ።

**ደቀመዝሙር** - እንደ መጠሪያ ስም፥ እርሱን በመምሰልና ትዕዛዛቱን በመፈጸም ኢየሱስን የሚከተል ሰው። እንደ ግስ አንድን ሰው “ደቀ መዝሙር ማድረግ” ወይም ኢየሱስን እንዲከተል ማስተማር ማለት ነው።

**ወንጌል ሥርጭት** - በተለያዩ መንገዶች የወንጌልን መልዕክት የማሰራጨት ተግባር።

**ዘፀአት** - 1) የመጽሐፍ ቅዱስ ሁለተኛው መጽሐፍ 2) የጥንት የእስራኤል ሕዝቦች ከግብፅ ባርነት ነፃ መውጣታቸውን የሚገልጽ ቃል።

**እኩይ** - ለእሱም ሆነ ለፍጥረቱ እግዚአብሔር ጽዩፍና አደገኛ ምግባር አድርጎ የፈረጀው የትኛውም ነገር።

**እምነት** - በአንድ ሰው ወይም ነገር ላይ መተማመን ወይም ማመን።

**ውድቀት** - የአዳምና የሔዋን የዔድን ኃጢአትና መዘዙ።

**የኃጢአት ይቅርታ** - እርሱን ያስቆጡትንና የበደሉትን እግዚአብሔር ሲተው። እግዚአብሔር ይቅር ሲል፣ የነበረን ቅጣት ሁሉ ይደመሰሳል። ጸጋ፣ ምሕረትና ድነት ተያያዥነት ያላቸው ሀሳቦች ናቸው።

**የዔድን ገነት** - እግዚአብሔር በፈጠረው ፍጥረት ውስጥ አዳምና ሔዋን ይኖሩበት የነበረው ሥፍራ። እግዚብሔር ራሱ በዔድን ነበር።

**ዘፍጥት** - የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያው መጽሐፍ።

**አሕዛብ** - የእስራኤል ሕዝብ አባል ያልሆነውን ማንኛውንም ሰው የሚያመለክት ቃል፤ ማለትም እስራኤላዊ ያልሆነ።

**አምላክ**- ቃሉ በነጠላ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሲቀመጥ፥ ያለውን ሁሉ ለፈጠረው፥ ሰውን ሁሉ ለሚወደው፥ ልዩና አቻ የሌለውና በባሕርዩ በራሱ ኗሪ የሆነ።

**እግዚአብሔር - ግጸዌ- መለኮት** - አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ከማንም የማይወዳደር አንድ ሥሉስ አምላክ

**ወንጌል** - በክርስቶስ ኢየሱስ የሆነ የድነት መልዕክት።

**ታላቁ ተልዕኮ** - ወንጌልን ያሰራጩ ዘንድ እና ከዓለም ሁሉ ደቀመዝሙርን ያፈሩ ዘንድ ኢየሱስ ለተከታዮቹ የሰጠው ተልዕኮ።

**ዕብራዊ** - የእስራኤላውያን ሌላው መጠሪያ።

**ዕብራይስጥ**- ብሉይ ኪዳን በመጀመሪያ የተጻፈበት ቋንቋ።

**መንፈስ ቅዱስ** - በማንነቱ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል የሆነ የእግዚአብሔር መንፈስ።

**ይስሃቅ** - ከሣራ የተወለደው የአብርሃም ልጅ።

**እስራኤል** - 1) የአብርሃም የልጅ ልጅ የያዕቆብ አዲስ ስም፤ 2) በአብርሃምና ሣራ አማካኝነት እግዚአብሔር የጀመረው የብሉይ ኪዳን ሕዝብ።

**እስራኤላዊያውን** - የአብርሃም ዘር አባላት፤ የእስራኤል ሕዝብ አባል የሆነ ሰው።

**ያዕቆብ** - የአብርሃም የልጅ ልጅ፤ የይስሃቅ ልጅ። በኋላም "እስራኤል"ተብሎ የተጠራ።

**ኢየሱስ** - ከድንግል ማሪያም የተወለደው፤ ምሉእ ሰው፣ ምሉእ አምላክ የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ። የሰው ልጆችን ከኃጢአታቸው ለማዳን በእግዚአብሔር የተወጠነውን ስራ ለመከወን ሰው የሆነ መለኮት።

**አይሁድ**- የአብርሃም ዘር ለሆኑ እስራኤላውያን የተሰጠ ሌላኛው ስም። በጥንት ዘመን ቅሪት ሆነው ለተማረኩት ሁለት ነገዶች በባዕድ የተሰጠ ስም።

**የእግዚአብሔር/የክርስቶስ/የኢየሱስ መንግስት** - እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ባዳናቸው አማኞች አማካኝነት በምድር ያለው አገዛዝ። አዲስ ኪዳን ይኼ መንግስት ወይም አገዛዝ አሁን በምድር ያለና እያደገ የሚሄድ፥ የመጨረሻውን ፍጻሜ እንደሚጠብቅ ይናገራል።

**ምህረት** - እግዚአብሔር የተገባንን ፍርድ ሳይሰጠን ሲቀር።

**መሲህ** - "የተቀባ" የሚል ትርጉም ያለው የዕብራይስጥ መጠሪያ። የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ከኃጢአታቸው አድኖ ከጠላቶቻቸው ነፃ የሚያወጣ ከዳዊት ዘር የሆነን የመጨረሻ ንጉስ የሚያመለክት መጠሪያ። በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ኢየሱስ መሲህ ነው። ለዚህ ቃል የግሪክ አቻው "ክርስቶስ" ሚል መጠሪያ ነው። በመሆኑም፥ "ኢየሱስ ክርስቶስ" "መሲሁ ኢየሱስ" ነው።

**ሙሴ** - እስራኤላውያን በግብፅ ባርነት በነበሩበት ጊዜ ተወልዶ እስራኤልን ከግብፅ ባርነት ነጻ እንዲያወጣ በእግዚአብሔር የተመረጠ ሰው።

**የሲና ተራራ** - እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብፅ ባርነት ነጻ እንዲያወጣ ሙሴን የጠራበትና ለእስራኤል አሥርቱን ትዕዛዛት የሰጠበት ስፍራ ተራራ።

**አዲስ ኪዳን** - ከብሉይ ኪዳን ቀጥሎ ያሉት 27ቱ ቅዱሳት መጻህፍት። የመጻህፍቱ ይዘት ትኩረት የኢየሱስ ሕይወትና አገልግሎት፣ የመጀመሪያዎቹ

ክርስቲያኖች ታሪክ እና በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የክርስትና እምነት መስፋፋት ነው።

**ኖኅ** - በጥፋት ውኃ ዘመን በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሆኖ የተገኘ እና እግዚአብሔር ከታላቁ የጥፋት ውኃ ራሱን፣ ቤተሰቡንና እንስሳትን ያድን ዘንድ መርከብ እንዲሰራ ያዘዘው ሰው።

**ብሉይ ኪዳን** - በይዘታቸው ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረ ታሪክን የሚዘክሩ የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያዎቹ 39 ቅዱሳት መጻፍት።

**ጳውሎስ** - አገልግሎቱን በአሕዛብ ላይ ያደረገ የኢየሱስ ሐዋሪያ።

**ጴጥሮስ** - ከዋናዎቹ የኢየሱስ ደቀመዛሙርት አንዱ።

**የተስፋይቱ ምድር** - እግዚአብሔር ለአብርሃም ዘሮች እንደሚወርሱ ቀድሞ ተስፋ የሰጠውን መልክዓ ምድራዊ የእስራኤል ምድር የሚያለክት መጠሪያ። እስራኤላውያን ሳይወርሱት በፊት በብሉይ ኪዳን “ከነዓን” በሚል መጠሪያ ይታወቃል።

**የጨለማ ኃይላት** - እግዚአብሔር ለአጽናፈ ዓለሙና ለሰው ቤተሰብ በሞላ ያለውን እቅድ ተቃርኖ የቆመ ልዕል-ኃያል ኑባሬ (ለበለጠ ማብራሪያ ከቃላት መፍቻ ቀጥሎ ያለውን “የልዕለ-ተፈጥሯውያን ቃላት ክለሳ” ይመልከቱ።

**ትንሣኤ** - 1) በጥቅሉ ከሞት በኋላ ባለው ዘላለማዊ ሕይወት የሞት ኃይል መሸነፍን ያመለክታል። 2) በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ ክርስቶስ በመሰቀል ከሞተ በኋላ ሞትን ድል አድርጎ በአካለ ትንሳኤ በሦስተኛ ቀን መነሳቱንና ቅዱሳን አማኞች በመጨረሻው ዘመን በአዲስቱ ምድር ለዘላለማዊ ሕይወት ለመኖር እንደሚነሱ ለማመልከት አገልግሎት ላይ የዋለ ቃል።

**ድነት** - በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር የተለየ ሕይወት በወንጌል እውነት በማመን ነጻ መውጣት። በድነት፥ የወንጌልን መልእክት በማመን ኀጢአት ይቅር ይባላል። ድነት አማኝን ወደ እግዚአብሔር ቤተ ሰብ ይቀላቅላል።

**ሣራ** - እግዚአብሔር በመለኮታዊ ኃይሉ ልጅ እንድትጸንስ ያደረጋት የአብርሃም ሚስት።

**ሰይጣን** - አዳምና ሔዋንን በዔድን ላታለለው እባብ የተሰጠ ስም። ከእግዚአብሔር ልዕለ ኃያል ፍጡራን ውስጥ በእግዚአብሔር ላይ የመጀመሪያ አመጸኛ ሰይጣን ነው። ሰይጣን በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ዋና ጠላት ነው (ለበለጠ ማብራሪያ ከቃላት መፍቻ ቀጥሎ ያለውን "የልዕለ-ተፈጥሯውያን ቃላት ክለሳ" ይመልከቱ።
**ሳኦል** - የእስራኤል የመጀመሪያ ንጉስ።

**እባብ** - በዔድን ገነት የአዳምና ሔዋን ጠላት። መጽሐፍ ቅዱስ በኋላ እባብን ዲያብሎስ እና ሰይጣን በማለት ጠርቶታል።

**ኃጢአት** - የእግዚአብሔርን የጽድቅ፥ የባሕርይና የምግባር መለኪያ ላይ የሚያምጽ፥ የሚቃወም ማንኛቸውም ዝንባሌ።

**ሰለሞን** - ከንጉስ ዳዊት ልጆች አንዱ፤ከዳዊት ሞትም በኋላ ዙፋኑን የወረሰ ንጉስ።

**ወልድ (ልጁ)** - በመጽሐፍ ቅዱስ "ወልድ" የሚለው የሥላሴ ሁለተኛ አካል የሆነውን፣ በኋላም ሰው የሆነውን ኢየሱስን ያመለክታል።

**የእግዚአብሔር ልጆች** - በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔርን የሚያለግሉ ወይም በእግዚአብሔር ላይ ያመጹ ልዕለ ኃያል ፍጡራንን ለማመልከት የሚያገለግል መጠሪያ። ለበለጠ ማብራሪያ ከቃላት መፍቻ ቀጥሎ ያለውን "የልዕለ ኃያላን ቃላት ክለሳ" ይመልከቱ።

**የእግዚአብሔር መንፈስ** - የመንፈስ ቅዱስ ሌላው መጠሪያ።

**መንፈሳዊ ውጊያ** - ከኀጢአት ጋር እንዲሁም የታላቁን ተልእኮ ከሚቃወሙ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይላት ጋር የሚደረግ ትግል። ለበለጠ ማብራሪያ ከቃላት መፍቻ ቀጥሎ ያለውን " የልዕለ-ተፈጥሯውያን ቃላት ክለሳ" ይመልከቱ።

**ልዕለ-ተፈጥሯውያን** - የመጠቁ ወይንም ከተፈጥሯዊው አጽናፈ ዓለም ውጭ ያሉ ኃይላትን ለመግለጽ የሚያገለግል መጠሪያ። "ልዕለ ተፈጥሯዊ ኑባሬ" በዓይን የሚታይ አካል ያልለበሰ መንፈሳዊ ኑባሬ ነው።

**አሥርቱ ትዕዛዛት** - እስራኤላውያን ከግብፅ ከወጡ በኋላ ከእግዚአብሔር የተሰጡ የመጀመሪያዎቹ አሥር የምግባር ሕጎች።

**ሥላሴ** - የግፃዌ መለኮት ሦስቱ አካላት። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ከዘላለም በሦስት አካል አንድ አምላክ ሆኖ እንደሚኖር ያስተምረናል።

## የልዕለ-ተፈጥሯውያን ቃላት ማጠቃለያ

መጽሐፍ ቅዱሳችን በመንፈሳዊው ዓለም ያሉትን ልዕለ ተፈጥሯውያን በተለያዩ ስያሜዎች ይጠራቸዋል። ክርስቲያናዊው ትውፊት እነዚህን ስያሜዎች አንድ ላይ በመጨፍለቅ ብዥታን ፈጥሯል። አብዛኛውን የማስተማር ስራዬን በነዚህ ጉዳዮች ላይ አሳልፌያለሁ፥ በመላእክት፥ ሰይጣን እና ክፉ መናፍስት ላይ ለማንበብ ፍላጎት ካላችሁ ከዚህ በታች የተጻፉትን በተገለጸው ቅደም ተከተል ታነቡ ዘንድ እጋብዛለሁ።

- *ልዕለ ተፈጥሮአዊው፡- መጽሐፍ ቅዱስ ስለማይታየው ዓለም የሚያስተመረው አስተምህሮና ፋይዳው* (በትርጉም ላይ ያለ)
- *The unseen Realm: Recovering the Supernatural worldview of the Bible*
- *Angels: What the Bible Really Says About God's Heavenly Host*
- *Demons: What the Bible Really Says About the Powers of Darkness*

ከእነዚህ መጽሐፍት የመጀመሪያው ይህን መጽሐፍ ይመስላል፥ ምሁራዊ ውይይት ለማድረግ የተጻፈ አይደለም። የተቀሩት ሶስቱ ደግሞ በርካታ የግርጌ ማስታዎሻችንና ዝርዝሮችን እንደመያዛቸው መጠን በባህሪያቸው ትምህርታዊ ናቸው። በእነዚህ መጻህፍት ውስጥ የተነሱ ሀሳቦችን ለመደገፍ ከተለያዩ የምሁራን ስራዎች የተወሰዱ በመቶዎች የሚቆጠሩ ማስታወሻዎችና ማጣቃሻዎች አሉ።

ለአሁኑ ግን፣ በዚህ መጽሐፍ ባቀረብነው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ መሰረት የልዕለ-ተፈጥሯውያን ቃለትን ክለሳ ማድረግ ጠቃሚ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የማይታይ የመናፍስት ዓለም ስለመኖሩ ያስተምረናል። እነዚህ ኑባሬዎች አካላዊ ቅርጽ መያዝ ቢችሉም፣ በባህሪያችው አካል የላቸውም። መንፈሳዊው ዓለም "ልዕለ ተፈጥሯዊ" ነው። መንፈሳዊ ዓለም በተፈጥሮው ከሚታየው ዓለም የተለየ ነው፤ ከተፈጥሮአዊው አካላዊ ዓለም የመጠቀ ወይንም ልእልና ያለው ነው።
እግዚአብሔር የመንፈሳዊው ዓለም አካል ቢሆንም፥ ፈጣሪው ስለሆነ ከሁሉ የበላይ ነው። በምናውቀው አካላዊ ወይም ቁሳዊ ዓለም ውስጥ ያለው ሕይወት በሙሉ በእግዚአብሔር እንደተፈጠረ ሁሉ፤ በማይታየው ዓለም ውስጥ ያሉ መንፈሳዊ ፍጥረታት በእግዚአብሔር ተፈጥረዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ የመንፈሳዊውን ዓለም አባላት ለምግለጽ የተለያዩ ቃላት ይጠቀማል (ለምሳሌ፡- ሮሜ 8፥31፤ 1ጴጥ 3፥22)። የተወሰኑትን በዚህ መጽሐፍ አስተዋውቄያለሁኝ። ከእነዚህ መጠሪያዎች የተወሰኑት "የስራ ድርሻ መገለጫ" ናቸው፤ መንፈሳዊ አካላት ምን እንደሚሰሩ የሚያሳዩ። መልአክ አንዱ ምሳሌ ነው። የቃሉ ትርጉም " መልዕክተኛ" ማለት ነው። በአዲስ ኪዳኑ የግሪኮ-ሮማውያን ባህል "መላእክት" የሚለው መጠሪያ በእግዚአብሔር ላይ ያላመፁ የትኞቹንም የሰማይ ሰራዊትን ለመግለጽ ያገለግል ነበር። "አጋንንት" የሚለው መጠሪያ በእግዚአብሔር ላይ በማመጽ የወደቁ አካላትን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ቢውልም፤ በጥንቱ ዓለም የተለያዩ ትርጉሞች አሉት።
"የእግዚአብሔር ልጆች" የሚለው ገላጭ ሐረግ፥ እግዚአብሔር የመንፈሳዊ ፍጡሮች አባት (ፈጣሪ) መሆኑን ያስታውሰናል። ሐረጉን፥ በ "ልእለ-ተፈጥራዊው" እና "unseen realm" በሚለው መጽሐፍ ላይ በጥልቀት ዳስሼዋለሁ። "የእግዚአብሔር ልጆች" በእግዚአብሔር "የሰራተኞች ኃይል" ውስጥ ያለ የላቀ ደረጃን የሚያሳይ ነው። ሐረጉ በጥንቱ ዓለም የነገስታት ልጆች የላቀ የስራ ድርሻ ከሚያገኙበት ቋንቋ የመነጨ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ "የእግዚአብሔር ልጆች" እግዚአብሔር በባቤል በፈረደባቸው ሕዝቦች ላይ እንዲገዙ የተመደቡ ናቸው። ተግባሩ መልዕክት ከማስተላለፍ (ይህ የ "መላእክት" ሥራ ነው) የበለጠ ነው።

በመጀመሪያ መላው የመንፈስ ዓለም አካላት ለእግዚአብሔር ታማኝ ሎሌዎች ነበሩ። ግን ነገሩ እንደነበረ አልቀጠለም። በዚህ መጽሐፍ እንዳነበብነው፣ እግዚአብሔር ለመንፈሳዊ ዓለም አባላት የእርሱን ባህርያት አጋርቷቸው ነበር። ከእነዚህ ብቃቶች አንዱ "ነፃ ፈቃድ" ነው። ከመንፈሳዊ ዓለም የተወሰኑ አባላት በእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር የሰው ቤተ ሰብ ላይ ለማመጽ ነፃነታቸውን ተጠቀሙ። በእግዚአብሔርና ሕዝቡ ላይ ያመፁ መንፈሳዊ አካላት ሁሉ በወል ስም "የጨለማው ኃይላት" ይባላሉ። ነገር ግን፥ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የሰው ቤተ ሰብ እንዲኖረው በፈለገ ጊዜ የተቃወሙትን መንፈሳዊ ጠላቶቹን ለይቶ ያስቀምጣል።
መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ ያሉትን ሦስት አመፆችን ይገልጽልናል። የመጀመሪያው በዔድን ገነት የተከሰተ ነው። ከመንፈሳዊው ዓለም አንዱ የእግዚአብሔርን የሰው ቤተ ሰብ ፍላጐት ለማቃለል ፈለገ። በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ እንደምናየው በእባብ ተመስሎ ሔዋንን አታለላት። በኋላም በመጽሐፍ ቅዱስ ያሉ እንደ "ሰይጣን" (ትርጉሙ ተቃዋሚ ማለት ነው) እና "ዲያብሎስ"( ሸንጋይ) ያሉ ስሞች የቀደመውን አመፀኛ ለመግለጽ ዋሉ።

የኋላ ኋላ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ እንደሚነገርን፥ ሰማያዊ የሆኑ አንዳንድ የእግዚአብሔር ልጆች አመፁ። እነዚህ በመንፈሳዊውና አካላዊው ዓለም መካከል

ያለውን ድንበር ጣሱ። አጭሩ የይሁዳ መጽሐፍ ኃጢአታቸውን " መኖሪያቸውን የተውና የራሳቸውን አለቅነት ያልጠበቁ" በማለት ይገልጻል። የቤተ ክርስቲያን ትውፊት እነዚህን አመፀኛ የእግዚአብሔር ልጆች ከቅድስና መውደቃቸውን ለማመልከት "የወደቁ መላእክት" እንዲሁም ርኩሰታቸውን ለማሳየት "አጋንንት" በማለት መጥራት ተጀመረ (ይህ አጠራር የራሱ ጉድለት አለው)። መጽሐፍ ቅዱስ በዘፍጥ 6፥1-4 ያሉትን አመፀኞች ለመግለጽ "መላእክት" ወይም "አጋንንት" የሚለውን በማይጠቀምበት ሁኔታ ማለት ነው።

በመጨረሻም፥ በባቤል ከተከሰተው የተነሳ፥ የተለያዩ ሀገራት ሕዝቦችን ያስተዳድሩ የነበሩ "እግዚአብሔር ልጆች" በስራቸው ላይ እያሉ ተበላሹ። መዝሙር 82 በእነዚህ ላይ ስለሆነው ፍርድ ያወሳል። እነዚህ በየድንበሩ የተመደቡ ፍጡሮች፥ በዳንኤል 10 ላይ ለተጠቀሱት ልእለ ተፈጥሮአዊ የሀገራ "መስፍኖች" እና ጳውሎስ በተለያዩ ስፍራዎች "ስልጣናት"፥ "ገዢዎች"፥ "ጌትነት" "ዙፋናት" እና "ኀይላት" ለሚላቸው መሰረት ናቸው (ለምሳሌ፦ ኤፌ 6፥ 11-12)። እነዚህ ልዕለ ተፈጥሯዊ መሰረት ያላቸው " ስፍራዊ አካላት" በትንቢተ ዳንኤል ከተገለጸው " አለቃ" ጋር ትስሥር ያላቸው ሲሆን፤ " አለቆች"፣ " ስልጣናት"፣ " መሪዎች"፣ " ዙፋናት" እና " ኃይላት" በማለት ጳውሎስ በተለያዩ ምንባባት ገልጦአቸዋል (ምሳሌ፡- ኤፌ 6፡ 11-12)። እነዚህ መጠሪያዎች መልክአ ምድራዊ አገዛዝን የሚያሳዩ ናቸው፤ ስለዚህም በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ የባቢሎን አመፅን ተከትሎ የመጣውን ክስተት በተገቢ ሁኔታ ይገልጻሉ።